አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

የሶዶ ጉራጌ ተረኮች እና የሴቶች ስርዓተፆታዊ ሚና እና ማህበራዊ ደረጃቸው

በ

ኤልሳቤጥ መንግስቱ

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የሶዶ ጉራጌ ተረኮች እና የሴቶች ስርዓተፆታዊ ሚና እና ማህበራዊ ደረጃቸው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ኤልሳቤጥ መንግስቱ

2005 ዓ.ም.

አማካሪ

ሰላማዊት መካ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂደማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

የሶዶ ጉራጌ ተረኮች እና የሴቶች ስርዓተፆታዊ ሚና እና ማህበራዊ ደረጃቸው

በ

ኤልሳቤጥ መንግስቱ

2005 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም	ፊርማ
.....	.....
የፈታኝ ስም	ፊርማ
.....	.....
.....	.....

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ. ፕ. ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና i

አጠቃሎ ii

የጉራጌ ዞን ካርታ iii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች 3

1.4 የምርምር ጥያቄዎች 3

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት 4

1.6. የጥናቱ ወሰን 4

1.7. የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴ 5

1.8 ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን 6

1.9. በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ እርምጃዎች 7

ምዕራፍ ሁለት

የሶዶ ጉራጌ ማህበረ-ባህላዊና ታሪካዊ ዳራ 8

2.1. የሶዶ ጉራጌዎች ስያሜ፣ አሰፋፈርና ቋንቋ 8

2.2. መልክዓ ምድራዊ ገፅታ 10

2.3. ፍልሰት በሶዶ ጉራጌዎች 11

2.4. በወረዳው የሚኖሩ ሴቶች ዳራ 12

ምዕራፍ ሶስት

የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ 14

3.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 14

3.2. ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ.....21

3.2.1 ተረክ.....21

3.2.2 አፍሪካና ውመኒዝም 23

3.2.3 ስርዓተ ፆታ.....25

3.2.4 ስርዓተ ፆታና ፎክሎር.....30

ምዕራፍ አራት

በሶዶ ጉራጌ የሴቶች ሚና እና ማህበራዊ ደረጃቸው የሚገለፁባቸው ተረኮች ትንተና 34

4.1. ሴቶችና የቤት ውስጥ ስራዎች.....35

4.1.1 ሴቶች በዘወትራዊ የቤት ውስጥ ስራዎች.....36

4.1.2 ሴቶች በክብረ በዓላት/መስቀል.....39

4.2. ሴቶችና ትዳር 43

4.3. ሴቶችና ምግብ 50

4.4. ሴቶች በአደባባይ 57

4.4.1. ሴቶችና የወንዶች አጋርነታቸው 58

4.4.2. ሴቶች፣ የቤት አስተዳደርና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦዋቸው 63

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ 66

ዋቢ ጽሁፎች 68

አባሪ 1፡- የተረኮች ስብስብ

አባሪ 2፡- የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

ምስጋና

ይህ ጥናት አሁን ያለበት እንዲደርስ የበርካታ ሰዎች አስተዋፅኦ አለበት። ከሁሉ አስቀድሜ ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ። በመቀጠል አማካሪዬ ሰላማዊት መካ በጥናቱ ላይ ገንቢ ሃሳቦች፣ አስተያየቶችና ማስተካከያዎችን በመስጠት አመሰግናለሁ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥናቴን እንዳካሂድ የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝ አመሰግናለሁ። አቶ አብርሃም አለሙ በርዕስ መረጣ ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ የሚነበቡ መረጃዎችን በመስጠት አድርጎልኝ ለነበረው ድጋፍ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ሶዶ ወረዳ በሄድኩበት ወቅት በቀናነት መረጃዎችን በመስጠትና መረጃ ሰጪዎችን በማመላከት ለተባበሩኝ ለወረዳው ሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤት እና የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኞች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። በተርጓሚነትና መረጃ አቀባዮች ጋ በመውሰድ አብረውኝ ለነበሩት አዜብና ዳዊት ምስጋናዬን መጋራት ይገባቸዋል። በመስክ ቆይታዬ ማረፊያ በማዘጋጀት ቆታዬን ቀና ላደረገችልኝ ዝናሽ ክንፉ ብድር መላሽ ያድርገኝ ብያለሁ። ቤተሰቦቼ አቶ ኦመንግስቱ ተሰማ፣ ወ/ሮ ገነት በዙ፣ እህቶቼ እየሩስ መንግስቱና መንግስቱና ዮዲት መንግስቱ፣ ጓደኞቼ እሙዬ (እስከዳር)፣ ይርጋ፣ ኢዮቤ፣ ሶፊ፣ ዳኒ እና ሌሎችም በገንዘብም፣ በሃሳብም፣ አስፈላጊ ከመፃህፍት ጀምሮ አስፈላጊ መረጃዎችን በማፈላለግም ጭምር ሽክሜን ስለተጋራችሁኝ እግዜር ይስጥልኝ።


አጠቃሎ

የሶዶ ጉራጌዎች ተረክና የሴቶች ስርዓተ ፆታዊ ሚና እና ማህበራዊ ደረጃቸው በሚል ርዕስ የተሰራው ይህ ጥናት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገሩት ቃላዊ ተረኮች ስለሴቶቹ የሚገልፁትን ጉዳይ የሚመረምር ነው። ለጥናቱም ከሶዶ ወረዳ የተሰበሰቡ ቃላዊ ዝርውና ግጥማዊ ተረኮች አንዲሁም አልፎ አልፎ ሴቶቹ ስለራሳቸው የሚተርኩት የግል ተሞክሮዎች ተካተዋል።

ጥናቱ በወረዳው የሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤት የተጠቆሙትንና በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሁለቱንም ፆታዎች በመረጃ ሰጪነት ያሳተፈ ከእነዚህ ታላሚ መረጃ አቀባዮች ጋር ቃለመጠይቅ ተካሂዷል፤ ተመሳሳይ ልምድ ያላቸውን ሴቶችንም በመሰብሰብ ቡድን ተኮር ውይይት ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ መረጃዎችን ከቤተመፅሀፍትና የተለያዩ ድረ-ገፆችን በመጎብኘትና በመሰብሰብ ለጥናቱ ማዋል ተችሏል።

ጥናቱ የሚያተኩረው የሴቶችን ህይወት በተረኮቹ ውስጥ ማየት በመሆኑ ተረኮቹን ለመተንተን የስርዓተ ፆታና የአፍሪካና ውመኒዝም ንድፈ ሐሳቦች በመደጋገፍ ጥቅም ላይ ውለዋል። ስለ ሶዶ ጉራጌ ሴቶች ስርዓተፆታዊ ሚና እና ደረጃዎች ለመረዳት ማህበረሰቡ ስርዓተፆታን የሚሰራበት መንገድ በጥናቱ የተቃኘ ሲሆን የአፍሪካና ውመኒዝም ንድፈሐሳብ የሚተያኩርባቸው ዋና ዋና መሰረታዊ ጉዳዮች በማህበረሰቡ ሴቶች ውስጥ እንደሚንፀባረቁ በጥናቱ ታይቷል።

የጉራጌ ዞን አስተዳደራዊ ካርታ



የጉራጌ ዞን ካርታ

ምንጭ: http://www.guragezone.gov.et

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በጉራጌ ዞን ውስጥ የሚገኘው የሶዶ ወረዳ በውስጡ 58 ቀበሌዎች አሉት፡፡ በዚህ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩት ማህበረሰቦች እንደማንኛውም ማህበረሰብ እምነታቸው፣ ፍልስፍናቸውና ለህይወት ያላቸው አተያይ የሚገለፁባቸው ፎክሎራዊ ገፅታዎች አሏቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዝርውና ግጥማዊ ተረኮቻቸው ይገኙበታል፡፡

ተረኮቹን የማህበረሰቡ አባላት ከሆኑ ሴቶች ጋር አብሮ የሚመለከተው ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች ተከፍሏል፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎችን፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች እንዲሁም የመስክ ክንውንን የሚገልፅ ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት የማህበረሰቡ ማህበረ ባህላዊና ታሪካዊ ዳራ ተዳሷል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የተዛማጅ ጥናቶች የተቃኙበትና ንድፈ ሀሳባዊ ዳራዎች የተዳሰሱበት ነው፡፡ ምዕራፍ አራት በሶዶ ጉራጌ ዘንድ ከሚነገሩ ተረኮች ውስጥ የሴቶችን ፆታዊ ሚናና ማህበራዊ ደረጃ ለማሳየት የሚያግዝ ትንታኔ የቀረበበት ሲሆን የጥናቱ ውጤት የሚገለፅበት የጥናቱ የማጠቃለያ ክፍል ደግሞ በምዕራፍ አምስት ላይ ቀርቧል፡፡

1.1 የጥናቱ ዳራ

ሴቶች ሴት በመሆናቸው ብቻ የሚጋሯቸውና የሚመለከቷቸው ጉዳዮች የሉም ማለት ባይቻልም እንደየባህሉና እንደየማህበረሰቡ ስሪት ጥያቄዎቻቸው፣ ፍላጎታቸው፣ ምኞታቸው፣ በአጠቃላይ ማህበራዊ ህይወታቸውን በተመለከተ ግድ የሚሏቸው ጉዳዮች እንዲስተናገዱ የሚፈልጉባቸው መንገዶችና ደረጃዎች የተለያዩ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በቀዳሚነት ሴቶችን ማዕከል አድርጎ ተነስቷል የሚባለው የፌሚኒዝም ንቅናቄ እንኳ የሁሉንም ሴቶች ጥያቄዎች የሚያቅፍ አልነበረም፡፡ ለዚህም ነው በውስጡ ርዕዮተ አለምን፣ ባህልን፣ ሃይማኖትን፣ ዘርና ሌሎች ማህበረ-ፖለቲካዊ ዳራዎችን መሰረት የሚያደርጉ መከፋፈሎች የተፈጠሩት፡፡ በመሆኑም በየማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የሴቶችን ህይወት ለመቃኘት

የማህበረሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችና እነዚህ ሁኔታዎች የሚገለፁባቸውን ፎክሎራዊ ገፅታዎች መመርመር አጠቃላይ ድምዳሜ ላለመስጠት ይረዳል።

በቃልም ሆነ በተግባር የሚገለፁ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የማህበረሰቡ አባላት እንደየዕድሜ ደረጃቸውና እንደየፆታቸው እንዴት ማንኛውንም ነገር መተግበር እንዳለባቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚነግሩ ብቻ ሳይሆኑ በተለመደው አካሄድ የሚሄዱት አባላት ከቤተሰባቸውና ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነትና የዕለት ከዕለት መስተጋብር ውስጥ ምን አይነት ሚና መጫወት እንደሚችሉና እንደሚገባቸውም ጭምር ያሳያሉ።

በሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥም በየትኛውም ቤተሰብ ህልውና ውስጥ ሳይነሱ መታለፍ የማይችሉት ሴቶች ያላቸው ሚናና ያንን ሚና በሚጫወቱበት ወቅት የሚኖራቸውን ብቃት የሚያሳዩ፣ የሚገመግሙ፣ ገምግመው ደግሞ የሚተቹና የሚያወድሱ ተረኮች በዝርውም ሆነ በግጥም አሉ። በእነዚህ ተረኮች ውስጥ የማህበረሰቡን ያልተፃፉ ህጎችና ህጎቹን መተላለፍ የሚያደርሰውን ቅጣት ጭምር ማየት ይቻላል። ይህ የጥናት ወረቀት እነዚህን የፎክሎር ገፅታዎችና በዚያ ውስጥ ሴቶች በምን መልኩ እንደሚታዩ ይዳስሳል።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በክስታኒኛ የሚነገሩ ተረቶችንና አባባሎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከአያቴ ስሰማ ነው ያደግሁት። በእነዚህ ቃላዊ ተረኮች ውስጥ አግራሞትንና ሳቅን የሚጭሩ፣ የሚያመራምሩና ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው የሚነሳ ፍልስፍናቸውን ለማየት ችያለሁ። ምንም እንኳ ቋንቋውን ጥርት አድርጌ ባላውቅም አባባሎቹን ለመረዳት ሁልጊዜ እጠይቅ ነበር። በተለያዩ አጋጣሚዎች ከአካባቢው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ከማገኛቸው የወረዳው ነዋሪዎች ጋር በተለይም ከሴቶቹ ጋር አደርገው የነበረው ጨዋታ ስለኑሯቸውና ስለህይወታቸው ጠለቅ ብዬ እንድረዳ ፍላጎትን አሳድሮብኛል።

ከዚህ በኋላ ደግሞ የተለያዩ የጥናት ወረቀቶችን ስመረምር በተለያዩ ማህበረሰቦች በተለይ በቃል ተረኮች ውስጥ ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ የተሰሩ ጥቂት ጥናቶችን ማግኘት ችዬ ነበር። የጉራጌ ማህበረሰብን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርመር ተቋም የተሰሩ

ጥናቶችን ስመረምር ያገኘኋቸው ጥናቶች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በሰባት ቤት ጉራጌ ላይ እንደሆነ ተረድቻለሁ። ከሶዶ ጉራጌዎችም ጋር በተያያዘ በተለይም ደግሞ ከስነልሳን አኳያ የተሰሩ ጥናቶች አግኝቻለሁ። ነገር ግን ከሴቶቹ ጋር ተያይዞ የተሰራ ጥናት ማግኘት አልቻልኩም ነበር። በመሆኑም ከሶዶ ጉራጌ (ክስታኔ) ፎክሎር ውስጥ በዝርውም ሆነ በግጥም የሚተረኩ ተረኮችን በመመርመር የሴቶቹ ህይወት ምን እንደሚመስል ለማየት እንደሚያስችል በማመን ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳሁ።

1.3. የጥናቱ አላማዎች

1.3.1. <u>አጠቃላይ አላማ</u>

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሶዶ ጉራጌ ሴቶች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሯቸውን ሚናዎችና ደረጃዎች በዝርውም ሆነ በግጥም በሚነገሩ ተረኮች ውስጥ ምን እንደሚመስሉ ማሳየት ነው።

1.3.2. <u>ዝርዝር አላማዎች</u>

- የሶዶ ጉራጌ ሴቶች በተረኮቹ ውስጥ ከሌላው የማህበረሰቡ ክፍል ጋር ያላቸውን ግንኙነት መሰረት በማድረግ ምን አይነት ሚና እንዳላቸው ማሳየት
- በማህበረሰቡ ውስጥ ተረኮቹ የሚነገሩበት ምክንያትና ፋይዳ ምን እንደሆነ ማሳየት
- በሶዶ ጉራጌዎች ውስጥ የሴቶችን ማህበራዊ ደረጃና ማህበረሰቡ ከእነሱ ምን እንደሚጠብቅ ማሳየት
- ሴቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከወንዶች ጋር አወዳድረው ያታዊ ሚናቸውን በማሳየት ይገባኛል የሚሉትን ማህበራዊ ደረጃ የሚያሳዩ ተረኮችን ከነትንታኔያቸው ማስቀመጥ የሚሉ ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል።

1.4. የምርምር ጥያቄዎች

የጥናቱን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉት የምርምር ጥያቄዎች ይኖሩታል።

- በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ በዝርውም ሆነ በግጥም በሚተረኩ ተረኮች ውስጥ የሴቶች ስርዓተ ፆታዊ ሚና እና ደረጃ ምን ይመስላል?
- የሶዶ ጉራጌ ሴቶች በማህበረሰባቸው ውስጥ እንደሴት ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ዕውቅና እንዲያገኙ ምን አይነት ፆታዊ ሚናዎች እንዲወጡ ይጠበቅባቸዋል?
- ተረኮቹ የሚነገሩበት ምክንያትና ፋይዳ ምድነው?
- ሴቶቹስ ፆታዊ ሚናቸውን እንዴት ይቀበሉታል? የሚሉ ናቸው።

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል የሚል እምነት አለኝ። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋና የምላቸው፡

- በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ በሚነገሩ ተረኮች ውስጥ ሴቶች በምን መልኩ እንደተሳሉና ማህበራዊ ደረጃዎቻቸውን ለመረዳት ያግዛል።
- በማህበረሰቡ ውስጥ ከሴቶች ጋር ተያይዞ ዋጋ የሚሰጣቸውን ባህላዊ እሴቶች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ያስችላል
- የሶዶ ጉራጌ ተረኮችን በከፊል ለማሳየት ያስችላል
- በተረኮቹ ውስጥ የሴቶችን ስርዓተ ፆታዊ ሚና ለማየት ያግዛል
- በአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ፎክሎር ጥናት ውስጥ አንድ ግብዓት መሆን ይችላል
- ይህንን መሰረት አድርገው ከሶዶ ጉራጌ ሴቶች ጋር የተያያዙ ሌሎች ጥናቶ ለማካሄድ ለሚነሱ ተመራማሪዎች እንደ አንድ ግብዓት ሊያገለግል ይችላል የሚሉት ናቸው።

1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ቦታዎች በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ በጉራጌ ዞን በሶዶ ወረዳ የሚገኘው የወረዳው ዋና ከተማ የሆነው ቡኢ፣ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የሚገኙት ኑረና፣ አናቲ፣ አይመለል እና ፍርሽና አሮና የሚሰኙ

ቀበሌዎች ናቸው። እነዚህ ቦታዎች ሙሉ ለሙሉ ማለት ባይቻልም አብዛኛውን የሶዶ ጉራጌ ሴቶች የህይወት ገፅታ ማሳያ መሆን ይችላሉ በሚል የተመረጡ ናቸው። ቦታዎቹ የተመረጡበት ምክንያ ቡኢ ከተማውን መወከል ስለሚችል፣ ኑረና እና አይመለል ራቅ ብለው ስለሚገኙና ቀሪዎቹ ለከተማው በአማካይ ቀረብ ያሉ ቀበሌዎች በመሆናቸው ሲሆን አመራረጡ ከተማውን፣ በጣም ገጠር የሆነውን እንዲሁም በከተማውና በገጠሩ መሃከል ያሉትን ቦታዎች ለመወከል ታስቦ ነው። ከእነዚህ የተመረጡ ቦታዎች የሶዶ ጉራጌ ሴቶች በማህበረሰባቸው ውስጥ ተሰጣቸውም ይሁን የፈጠሩት ደረጃና የሚጠበቅባቸው ሚና የሚገለጹባቸው ዝርውና ግጥማዊ ተረኮች ላይ ብቻ ያተኩራል። ተረኮቹ በራሳቸው በሴቶቹም ሆነ በሌላው የማህበረሰቡ አባላት የሚተረኩ ናቸው። መረጃዎቹን ለመተንተን ሁለት ንድፈ ሐሳቦችን ተጠቅሜያለሁ። እነዚህም የስርዓተ ፆታ/Gender/ እና የአፍሪካና ውመኒዝም/Africana Womanism/ ንድፈ ሐሳቦች ናቸው።

1.7. የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴ

ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በሶዶ ወረዳ በሚገኙ የተመረጡ አምስት ቀበሌዎች ውስጥ ሲሆን የናሙና አመራረጡም ታላሚ የናሙና አመራረጥ ስልትን የተከተለ ነው። በዚህ ዘዴም ከተመረጡ መረጃ ሰጪዎች ጋር የግል ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ተደርጓል። ጠቅለል ያለ የህይወታቸውን ገፅታ ለመረዳትም ተጨማሪ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። ይህም የተደረገው ተረኮቹ ሲተረኩ ክዋኔውን የመመልከት ዕድሉ ስላልነበረኝና ብዙዎቹ ተረኮች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ እንደጨዋታ ጣል የሚደረጉ ስለሆኑም ጭምር ነው። የድምፅና ምስል ሰነዶችም በመቅረፀ ድምፅና በፎቶግራፍ የተያዙ ሲሆን የተሰበሰቡት መረጃዎች ገላጭ ትንታኔ ይሰጥባቸዋል።

የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የተጠቀምኩበት ማጠንጠኛ የስርዓተ ፆታና የአፍሪካና ውመኒዝም ንድፈ ሃሳብ ነው። ንድፈ ሐሳቦቹ ስርዓተ ፆታ ማህበራዊ ስሪት መሆኑ ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን፣ የተጠኚውን ህብረተሰብ ማህበራዊ እሴቶች ለማሳየት አግባብ ናቸው በሚል የተመረጡ ናቸው። በመሆኑም ጥናቱ ትኩረት የሚያደርግበትን የሶዶ ጉራጌ

ሴቶችን ህይወት የሚያሳየው የማህበረሰቡን ገፅታ ለማግኘት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚነገሩ ዝርውም ሆኑ ግጥማዊ ተረኮች በንድፈ ሐሳቦቹ የሚቃኙ ይሆናል።

1.8. ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

የዚህ ጥናት ርዕስ ፀድቆ ጥናቱን ማከናወን እንደምችል ከተነገረኝ በኋላ በቅድሚያ ስለአካባቢው መረጃ መሰብሰብ ጀመርኩ። በተለይም ከማህበረሰቡ ጋር ተያይዞ የተሰሩ ልዩ ልዩ ጥናቶችን ተመልክቻለሁ። ወደ መስክ ለመውጣት ስዘጋጅም የት አካባቢ መሄድ እንደምችልና የምሄድበት አካባቢ ከአዲስ አበባ ምን ያህል ርቀት ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች ካገኘሁ በኋላ ጥናቱን ለመሰብሰብ የሚረዱኝን ቁሶች ማለትም የፎቶግራፍ ካሜራና መቅረፀ ድምፅ አዘጋጀሁ።

በመቀጠልም ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ለመተዋወቅና መረጃ የሚሰጡኝን ሰዎች ለማፈላለግ የመጀመሪያ ጉዞዬን አደረኩ። በዚህ ወቅት ቡሷ ላሉት የወረዳው የሴቶችና ህፃናት እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች ጋር ከትምህርት ክፍሌ የተፃፈልኝን ደብዳቤ በማሳየት ራሴንና ለምን እንደመጣሁ አስተዋወቅሁ። በምን መልኩ ሊረዱኝ እንደሚችሉም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተወያየሁ። ሁለቱም ጽ/ቤቶች ጥናቱን እንዳከናውን ማድረግ የሚችሉትን ያህል እንደሚረዱኝ ቃል ገቡልኝ። የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ስለአካባቢው ሁኔታ በመግለፅና በቢሮው የተዘጋጀ አመታዊ የፅሁፍ መረጃ በመስጠት ሲተባበረኝ የሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤት በአካባቢው ጥሩ ተራኪ የሚባሉ ሴቶችን ስምና አድራሻ እንዲሁም አብራኝ ልትሰራ የምትችል መረጃ ሰብሳቢና አስተርጓሚ መደበልኝ። ይህ ነገሮችን ቀለል አድርጎልኝ ነበር።

በሁለተኛው ጉዞዬ በቀጥታ አድራሻዎቻቸው ከሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤት የተሰጡኝን መረጃ ሰጪዎች አፈላልጎ በማግኘትና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ተረኮቹን መሰብሰብ ጀመርኩ። ቃለ መጠይቆቹም በየመረጃ ሰጪዎች የመኖሪያ ቤቶችና በመዝናኛ ቦታዎች የተካሄዱ ሲሆን አጠቃላይ ህይወታቸውን ለመዳሰስ የተሞከረባቸው ቡድን ተኮር ውይይቶች ደግሞ ፈቃደኛ በሆኑ ሴቶች ቤት ውስጥ ተካሂደዋል። ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ የሰበሰብኳቸውን

መረጃዎች በፅሁፍ ከተገለበጡ በኋላ ለጥናቴ በቂ ሆነው አልተገኙም። በመሆኑም ከአማካሪዬ ጋር በመወያየት ሶስተኛ ጉዞ አድርጌያለሁ።

በሶስተኛው ጉዞ ወቅት ቅድሚያ ከነበሩት በተጨማሪ ሌሎች መረጃ ሰጪዎችን በማፈላለግ የተጠናከሩ መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ። ተጨማሪ መረጃ አቀባዮችን በማፈላለግ ረገድ አስተርጓሚዎቼ እጅጉን ረድተውኛል።

1.9 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች

ጥናቱን በማካሂድበት ወቅት (መረጃውን በመሰብሰብና ወደፅሁፍ በመገልበጥ) ወቅት ካጋጠመኝ ችግሮች አንዱ ቋንቋ ነበር። ምንም እንኳ ክስታኒኛ የማውቅ ቢሆንም ተወላጆቹ በተለይም ደግሞ በዕድሜ ከፍ ያሉት የሚጠቀሙት ቋንቋ ውስጥ ጠጠር ያሉና እኔ በቀላሉ የማልረዳቸው ቃላት ነበሩበት።

ይህንን ችግር ለመፍታት ረዳት መረጃ ሰብሳቢዬን ተጠቀሜያለሁ። ረዳት መረጃ ሰብሳቢዋ የአካባቢው ተወላጅ በመሆኗና ክስታንኛም የመጀመሪያ ቋንቋዋ በመሆኑ በቃለመጠይቁ ወቅት በመሃከል የቃላቱን ትርጉም እየነገረችኝ ችግሩን ለማቃለል ችያለሁ። በተጨማሪም አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች አማርኛ መናገር የሚችሉ በመሆኑ አንዳንዴ ተረኩን በአማርኛ አንዳንዴ ደግሞ ሁለቱን ቋንቋዎች እየተጠቀሙ ስለነገሩኝ የቋንቋ ችግሩን ማቃለል ተችሏል።

ሌላው ችግር በሁለተኛው ጉዞ የተሰበሰበው መረጃ በቁጥርም ሆነ በይዘት የተጠበቀውን ያህል አለመሆኑ ነው። በተለይ መረጃው ወደፅሁፍ ተገልብጦ ለትንታኔ ሲዘጋጅ ለመመደብ የሚያስቸግር ነበር። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሶስተኛ ጉዞ ማድረግ ያስፈልግ ነበር። በሶስተኛው ጎዞዬ በረዳት መረጃ ሰብሳቢዬ አማካይነት ተጨማሪ መረጃ ሰጪዎችን (ወንድም ሴትም) ያገኘሁ ሲሆን የተሻሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። ይሁንና በዚህም ወቅት ያገኘኋቸው ዝርው ተረኮች አነስተኛ በመሆናቸው ቃላዊ ግጥሞችንም በመጨመር መረጃዎቹን ለማጠናከር ሞክሬያለሁ።

ምዕራፍ ሁለት

የሶዶ ጉራጌ ማህበረ-ህላዊና ታሪካዊ ዳራ

የጉራጌ ዞን በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር ከሚተዳደሩት ዞኖችና 4 ልዩ ወረዳዎች አንዱ እንደሆነ የክልሉ ድረገፅ ይገልፃል። ዞኑን በዋናነት ሶስት ብሔረሰቦች ማለትም፣ የጉራጌ፣ የቀቤና፣ እና የማረቆ ብሔረሰቦች የመሰረቱት ሲሆን በውስጡ ሌሎች ብሔረሰቦች ማለትም አማራ፣ ከንባታ፣ ኦሮሞ ወዘተ በጋራ የሚኖሩበት ነው። (www.guragezone.gov.et.)። በ 1999 ተጠንቶ በ 2000 ዓ.ም. ይፋ የሆነው ሶስተኛው አገር አቀፍ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት የጉራጌ ህዝብ አጠቃላይ ቁጥር 1,859,831 እንደሆነ ያመለክታል። ከእነዚህም ውስጥ ወንዶች 919,219 ሲሆኑ የሴቶቹ ቁጥር ደግሞ 940,612 ነው። የሶዶ ወረዳም በጉራጌ ዞን ካሉት ወረዳዎች አንዱ ነው።

የሶዶ ጉራጌ ከአሰፋፈር፣ ከቋንቋ፣ ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአኗኗር ዘይቤ አኳያ የሚገለፀው ማህበረ-ባህላዊና ታሪካዊ ዳራ ያለው ህዝብ ሲሆን እነዚህ ስለማህበረሰቡ የተወሰነ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ገፅታዎች ከተለያዩ የህትመት ውጤቶች፣ ጥናቶችና ከዞኑ ድረ-ገፅ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

2.1 የሶዶ ጉራጌዎች ስያሜ፣አሰፋፈርና ቋንቋ

‹‹ጉራጌ ማለት የጉርዓ ሰዎች ሰብዓ ጉራጌ ማለት ነው። ይህም ጥንተ ስሙ ጉራዕ ሲሆን ጎንደር ጎንደሬ፣ ወሎ ወሎዬ እንደሚባለው ጉራዕ ጉራጌ ተባለ›› (ተስፋ፣1987፣XV) ይህ ጉራጌ የሚለው ጥሪ ጎንደሬና ወሎዬ ከሚሉት ጋር ያለውን አቻነት የሚያሳይ አገላለፅ እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ትርጉም አለው የሚሉት አለቃ ታዬ ደግሞ ከንጉሱ ሰፈር በግራ በኩል ስለሰፈሩ ግራጌ እንደተባሉና ከጊዜ ብዛት ስማቸው ተቀይሮ ጉራጌ እንደተባለ ይገልፃሉ። (ታዬ፣ 1920፣74)

የጉራጌ ህዝብ በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት በ14ኛው ክፍለ ዘመን ከሰሜናዊው ኢትዮጵያ ጉራዕ ከተሰኘ ቦታ ተነስቶ አሁን ያለበት ቦታ እንደሰፈረ የህዝቡን ታሪክ መሰረት ያደረጉ የተለያዩ የታሪክ ምንጮች የሚገልፁ ሲሆን (ታዬ፣ 1964፣ 73፣ Bahiru; 1972,

57፣ ተስፋ፤ 1987፣ 1-2) አሰፋፈሩን በተመለከተ አለቃ ታዬ በ1327 ዓ.ም. ገደማ በአዝማች ስብሃት መሪነት ከአካለ ጉዛይ አውራጃ ከጉራዕ ቀበሌ ተነስቶ የንጉሱ ጦር አይመለል በተባለው ስፍራ እንደሰፈረ ይተርካሉ። (ታዬ፤ 1920፣73)

ተስፋ ገብረየስ ስለሶዶ ጉራጌዎች (የአይመለል ህዝብ) ባህልና ታሪክ በዓፉበት አይመለል (1987) የተሰኘ መፅሀፍ ውስጥ እንደገለፁት ጉራጌ የነገዱ ስም ሲሆን አሁን የሰፈሩበት ቦታ ቀደም ሲል አይመለል ይሰኝ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን አይመለል በሶዶ ወረዳ ውስጥ ካሉት ቀበሌዎች የአንዱ ብቻ መጠሪያ ሆኖ ቀርቷል። ነገደ ጉራጌ በአይመለል የሰፈረው በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት ቢሆንም ጉራጌ የሚለው ስያሜ ከዚያም በፊት የነበረና ኋላ ከመጡት ጋር ተቀላቅሎ ቃሉን እንደሚጠራበት ተስፋ ገብረየስ በመፅሐፋቸው ላይ ይገልፃሉ። (ተስፋ፤ 1987፣ 2)

ስለሶዶና ጉራጌ ጥምረትና አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ ስላላቸው ሚና በመፅሀፉ ውስጥ

> የሶዶ ሕዝብ ከነገደ ኦሮሞ የቦረና ልጅ ነው። አንዳንድ ታሪክ ሶዶን ከበርቱማ የወረንሻ ልጅ ያደርገዋል። የሶዶ ልጆች ግን ከቦረና የወረዱ የዳጪ ልጆች እንደሆኑ ይተርካሉ። የሶዶ ልጆች ከግራኝ ወረራ በኋላ በገላን ዞረው በጨቦና በአይመለል መሀከል በሰባት ቤት ጉራጌ ምሥራቅ ሰሜን ገቡ። ሰዬን ሶዶ ተብለው ይጠራሉ። ይህም ሶስቱ ሶዶ ማለት ነው። እነሱም ቱምኤ ሊበንና ኦዲቱ ናቸው። .... እስከ ዓፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ድረስ በሶዶና በጎርደና መሀከል ፀብ እንደሆነ ቆይቶ አፄ ምኒሊክ አንድ አድርገው ዳኙት። ከዚሁ ተያይዞ ጎርደናና ሶዶ በጋብቻና በዘር ተቀለቀሉ። በፍቅርና በሃይማኖትም አንድ ሆኑ። በአጠራርም ጉራጌ ሶዶ፣ ሶዶ ጉራጌ ተባሉ።›› (ተስፋ፤ 1987፣14)

በማለት ተገልጿል።

በሰሜናዊው ጉራጌ የሚገኙት ህዝቦች ክስታኔ፣ አይመለል፣ ጎርደና ወይም ሶዶ በሚል በተቀያያሪነት የሚጠሩ ሲሆን (ሽመልስ፤2001፣174) እነዚህ ህዝቦች በዋናነት ሁለት ቋንቋዎች ይናገራሉ። በአብዛኛው የሚናገሩት ክስታኒኛ (የአይመለል ጉራጊኛ) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኦሮምኛ ቋንቋ ነው። (ተስፋ፤ 1987፣ XVII) ትዕግስት በርሄ እና ኤፍሬም በለጠ በስነልሳን ትምህርት ክፍል በማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ፅሑፋቸው ላይ አር. ሂትዞርን እና ቤንደርን ጠቅሰው እንደገለፁት ክስታኔዎች ከሴም ቋንቋዎች ውስጥ

አማርኛና ክስታኒኛ ቋንቋን የሚናገሩ ሲሆን ሂትዞር ከእነዚህ በተጨማሪ ከኩሽ ቋንቋዎች ደግሞ ኦሮምኛን እንደሚናገሩ ይገልፃል። (ትዕግስት፤2008፣2፣ ኤፍሬም፤ 2011፣ 3).

2.2. መልክዓምድራዊ ገፅታ

የእንስት ባህል አላቸው ከሚባሉት ከደቡብ ምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ውስጥ የሚመደበው የሶዶ ጉራጌ (ክስታኔ) ህዝብ (ሽመልስ፤ 2001፣ 174፣ ባህሩ፤ 1972፣75) በአጠቃላይ የሚይዘው መልክዓ ምድራዊ ገፅታ በተለያዩ ጥናቶች ውስጥ የተገለፀ ሲሆን አጠቃላይ መጠሪያው በደቡብ ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ በደቡብ ምዕራብ ክፍል ለሚገኙትና በምዕራብ በኩል በኦሞ ወንዝ፣ በሰሜን በአዋሽ ወንዝ፣ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ በሲዳማ ለተካለሉት ህዝቦች እንደሚውል ጃክ ፌልማን (Jack Fellman) ይገልፃል። ‹‹ሰሜናዊው ጉራጌ ሶዶንና ጎጎትን፣ ምስራቃዊው ጉራጌ ስልጢን፣ ወለኒን እና ዝዋይን እንዲሁም ምዕራባዊው ጉራጌ ሙኸርን፣ መስቃንን፣ ቸሃን፣ እገርን፣ ጌይቶን፣ እነሞርንና እንደገንን ያካትታል።›› (Fellman; 1984, 673) ሶዶ ጉራጌ ተብሎ የሚጠራው ህዝብ ደግሞ በሰሜናዊው ጉራጌ የሚገኝ ነው።

ሶዶ ጉራጌዎች በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ ውስጥ ይገኛሉ። የሶዶ ወረዳ ርዕሰ ከተማ የሆነው ቡዲ ከጉራጌ ዞን ርዕሰ ከተማ ከወልቂጤ በ261 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት በ2003 ዓ.ም. ላይ ባወጣው መረጃ መሰረት ወረዳው በሰሜን፣ በምዕራብና በምስራቅ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ሲዋሰን በስተደቡብ ምዕራብ ከመስቃን ወረዳ ጋር ይዋሰናል። ወረዳው በ58 የአስተዳደር እርከኖች የተከፋፈለ ሲሆን አራቱ ከተሞች፣ ሃምሳ አራቱ ደግሞ የገጠር ቀበሌዎች ናቸው። የወረዳው ርዕሰ ከተማ ቡኢ በ2007 እ.አ.አ. የሪፎርም ከተሞች ተብለው ከተያዙት የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከተሞች አንዱ ነው።

ወረዳው በጥቅሉ 88,553.3 ኪሎ ሜትር ስኩዌር የቆዳ ስፋት ሲኖረው በአጠቃላይ የወረዳው 90.6 ከመቶ የሚሆነው ህዝብ በገጠሩ የወረዳው ክፍል፣ ቀሪው 9.4 ከመቶ የሚሆነው ደግሞ በከተማው ክፍል ይኖራል። በኢኮኖሚ ረገድም ግብርና ከፍተኛውን ድርሻ

የሚወስድ ሲሆን ከወረዳው ነዋሪዎች ውስጥ በግብርና የሚተዳደረው ህዝብ ከአጠቃላዩ 90.6 % እንደሆነ የወረዳው ቡክለት ይገልፃል።

2.3 ፍልሰት በሶዶ ጉራጌዎች

ከ19ኛው ክፍለዘመን ማብቂያ ጀምሮ የክስታኔ ህዝብ ከሚገጥሙት ተግዳሮቶች ዋነኛው ፍልሰት ነው። (ሽመልስ፤ 2001፣ 174) ሽመልስ በጥናቱ እንደሚገልፀው በ1890ዎቹና በ1970ዎቹ መጀመሪያ መካከል ባሉት ዓመታት አንድ መቶ ሺህ የሚሆኑ ክስታኔዎች አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች በቋሚነት ሰፍረዋል። እስከ እ.አ.አ. 1974 ድረስ ለፍልሰቱ እንደ ምክንያት የሚነሱ ጉዳዮች በየጊዜው እንደሚቀያየሩ ገልፆ እነዚህንም በአራት ዘመናት ከፍሎ አስቀምጧቸዋል።

ከ1875 እ.አ.አ. በፊት መሬታቸው በኦሮሞዎች መወሰዱ፣ ከ1875-1935 ድረስ በተለይ በምኒሊክ ዘመነ መንግስት ንጉሱ ዘመናዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት ባደረጉት የግዛት ማስፋፋት ምክንያት የቀደመው የክስታኔ መዋቅር በመነካቱ፣ ከ1935-41ድረስ ጣሊያን በኢትዮጵያ በነበራት ቆይታ በመስፋፋቱ ወቅት የመሬት መብት ያልነበራቸው ክስታኔዎች ጣሊያን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባደረገችው የዳግም ማዋቀር ስራ ከተማ ውስጥ ቤት እንዲሰሩ ስለፈቀደላቸውና ከከተማ ገጠር የነበረው የንግድ ግንኙነት የወጣት ክስታኔዎችን ቀልብ በመሳቡ፣ እንዲሁም ከ1941-1974 ባለው ጊዜ ጣሊያን ኢትዮጵያን ከለቀቀ በኃላ በነበረው ነፃነት የክስታኔ የተናጠል ፍልሰት ከመሆን አልፎ በከተማዎች ውስጥ የራሳቸውን ማህበረሰብ እንዲመሰርቱ አድርጓቸዋል። የሽመልስ ጥናት እንደሚያሳየው (2001፣182) በ1950ዎቹ እ.አ.አ. የጉራጌ ማህበረሰብ ከክስታኔ መሬት ውጪ ባሉ 45 የሚሆኑ የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ከአንድ እስከ ሶስተኛ ደረጃ የሚደርስ የህዝብ ቁጥር ነበራቸው። እንዲሁም ከ1964-1968 እ.አ.አ. ተካሂዶ በነበረው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ከ201 የከተማ ማዕከላት ውስጥ በ103ቱ ውስጥ ክስታኒኛ ተናጋሪዎች ተገኝተው ነበር።

የፍልሰት ጉዳይ ዛሬም በሶዶ ወረዳ ከሚነሱ የስነህዝብ ችግሮች እንደ አንዱ ይታያል። በአካባበው ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የስራ ዕድል የሚፈጥሩ የስራ መስኮች ባለመኖራቸውና በተለይም በደጋማው የወረዳው ክፍል የእርሻ መሬት ጥበትና

የምርታማነት ማነስ በስፋት በመኖሩ በተለይ ወጣቶች ወደከተማ እንደሚሰደዱ የሶዶ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያወጣው ቡክሌት ያመለክታል።

2.4. በወረዳው የሚኖሩ ሴቶች ዳራ

የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ያወጣው መረጃ ላይ በወረዳው የሚገኙ ሴቶች የትምህርት፣ የጤናና የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲገልፅ በሴቶች ዙሪያ ያሉ አንኳር የስነህዝብ ችግሮች ዝቅተኛ የትምህርት ተሳትፎ፣ ከፍተኛ የቤተሰብ ሃላፊነትና የስራ ጫና፣ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም፣ ዝቅተኛ የንብረት ባለቤትነት፣ ዝቅተኛ ውሳኔ ሰጪነት ሚና፣ ከፍተኛ ለኤች. አይ.ቪ ተጋላጭነትና የመሳሰሉት ማህበራዊ ችግሮች እንደሆኑ ይገልፃል፡

ሴቶች በወረዳው ውስጥ ያላቸውን የትምህርት ሁኔታ በተመለከተ የወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት የወረዳውን ትምህርት ፅ/ቤት መረጃ መሰረት ያደረገው ቡክሌት እንደሚገልፀው በወረዳው ያለው የትምህርት ሁኔታ ሲታይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ ላቅ ብሎ ይታያል። ነገር ግን ከዚያ አለፍ ሲል ቁጥራቸው እየተመናመነ የሚመጣ ሲሆን ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሱት በአቅራቢያቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማይገኙ ከሆኑ ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ራቅ ወዳለ ቦታ መላክ ስለሚፈሩ ወይም ደግሞ ልከው የሚያስተምሩበት አቅም ስለማይኖራቸው፣ በስነተዋልዶ ጤና ያላቸው ግንዛቤ ማነስ ላልተፈለገ እርግዝና ሲያጋልጣቸው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ስለሚገደዱ፣ የቤት ውስጥ ስራ ጫና ስለሚበዛባቸው በአግባቡ ትምህርታቸውን መከታተል ስለማይችሉና የመሳሰሉት ናቸው። ይህንንም ቡክሌቱ በስታትስቲክስ ሲያስቀምጠው በ2000 ዓ.ም. የሴቶች የትምህርት ሽፋን የአንደኛ ደረጃ 112፣ የሁለተኛ ደረጃ ደግሞ 12፣ በ2001ዓ.ም. የአንደኛ ደረጃ 113.6፣ የሁለተኛ ደረጃ 13.4፣ በ2003 ዓ.ም. የአንደኛ ደረጃ ሽፋን 114.3 እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ 19.3 እንደነበር የወረዳው ትምህርት ፅ/ቤት ያወጣው መረጃ ይገልፃል።

በ1999 ዓ.ም. ከተካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ወላጆቻውን ካጡ ልጆች ውስጥ በአባታቸው ብቻ ከሚተዳደሩት ይልቅ በእናት ብቻ የሚተዳደሩት በቁጥር ላቅ ያሉ ናቸው። አንድ ወላጃቸውን ካጡት 5301 ህፃናት መካከል

356 ያህሉ አባት ብቻ ያላቸው ሲሆኑ 4945 ያህሉ ደግሞ እናት ብቻ ያላቸው ናቸው። ለዚህም እንደምክንያት የተነሳው አንድ አባወራ የሚያስተዳድረው ቤት ከአንድ በላይ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ስለሆነና ሲሞት ከአንድ በላይ ቤተሰብ ትቶ ስለሚሄድ ነው።

በኢኮኖሚ ረገድ በሴቶች ላይ ጫና ፈጥሮ የኖረው ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ ዛሬም ድረስ ባለመጥፋቱ በወረዳው የሚገኙ ሴቶች የሚሳተፉባቸው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እምብዛም እንደሆኑ መረጃው ይገልፃል። ለምሳሌ ያህል በመንግስት ስራ ውስጥ ከተሰማሩት የወረዳው ነዋሪዎች ውስጥ ሴቶች 36.7 በመቶ ብቻ ናቸው። በንግድም ቢሆን የሚሳተፉት ጥቃቅን በሆኑ ንግዶች ውስጥ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው አናሳ ነው።

በወረዳው ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት መረጃ መሰረት በአጠቃላይ የስርዓተ ፆታ ሁኔታ እንደብዙዎቹ የሀገራችን ክፍሎች ሁሉ በሶዶ ወረዳም ያልዳበረ በመሆኑ በሴቶች ላይ ጫና ያበዛል። ይህም ሴቶች በብዙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ውስጥ በስፋት እንዳይሳተፉ አድርጓቸዋል።

ምዕራፍ ሶስት

የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ጥናት የማደርግበትን ማህበረሰብ ትኩረት አድርገው የተሰሩ ጥናቶችን የምቃኝ ሲሆን የሰበሰብኳቸው መረጃዎች የሚተነተኑበት ንድፈሐሳባዊ ዳራ የሚመለከቱ የተለያዩ ስራዎችን እዳስሳለሁ።

3.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከተሰሩት ውስጥ በቃል በሚተላለፉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ውስጥ እንደ ተረትና ምሳሌ፣ ተረቶችና አባባሎች ውስጥ ሴቶች እንዴት እንደሚሳሉ የሚተነትኑ የተወሰኑ ጥናቶች አግኝቻለሁ። በተለይ ደግሞ በኦሮምኛ በሚነገሩ ፎክሎሮች ውስጥ ብርሃኑ በቀለ (2008)፣ ሴና ጎንፋ (2008) ለውጭ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የሰሩትን ጥናት ማንሳት ይቻላል። እነዚህ ጥናቶች ምንም እንኳን የእኔ ጥናት ትኩረት የሚያደርግበትን ማህበረሰብና ቋንቋ ባይመለከቱም በቀጥታ ሴቶችና ተረክን የሚያነሱ በመሆናቸው ጠለቅ ብዬ እመለከታቸዋለሁ።

ከሴቶች ጋር ተያይዘው በሚቀርቡ ቃላዊ ተረኮች ላይ ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ ብርሃኑ በቀለ በ2008 እ.አ.አ. "the Portrayal of women in folktales and popular sayings of the Oromo of East Wellega"፣ በሚል ርዕስ የሰራው ጥናት ይገኛል። ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ይህ ጥናት ውስጥ ብዙዎቹ ተረቶች ሴቶች በማህበረሰባቸው ውስጥ ያላቸውን ሚና ዝቅ የሚያደርጉ ናቸው በሚል የተነሳ ነው። ተረቶቹ ወንዶቹ ከሚፈፅሙት በበለጠ የሴቶችን ስህተት የሚያራግቡ ናቸው ይላል ጥናቱ። በአሁኑ ጊዜ ግን ለሴቶች መብት በሚሟገቱ ሴቶች ዘንድ ተቀባይነትን እያጣ ያለ ቢሆንም አንዳንድ ወንዶች የሴቶችን እኩልነት ለመቀበል አሁንም ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ይገልፃል። ጥናቱ ወንዶችንና ሴቶችን በገፀባህሪነት የሚጠቀሙ ተረቶችን መሰብሰብ፣ መተንተንና፣ ማቆየት፣ በተረቶቹና አባባሎቹ ውስጥ ሴቶች የሚገለፁበት ስቴሪዮታይፕ/ፍረጃ አንድ

መሆን አለመሆኑን መለየት እንዲሁም በአካባቢው ባለው ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶች የሚሳሉበትን መንገድ ማሳየትን አላማው አድርጎ የተነሳ ነው።

ብርሃኑ ለጥናቱ የተጠቀመው የአጠናን ዘዴ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ነው። ጥናቱ በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን ተረቶቹንና አባባሎቹን የተተነተነበት ምዕራፍ ሶስት ውስጥ ሴቶችን በአዎንታዊ መልኩ የሳሉ ተረቶችና አባባሎች እንዲሁም የሴቶችን አሉታዊ ገፅታዎች የሚያነሱ ተረቶችና አባባሎች በሚሉ ሁለት አበይት ርዕሶች ተከፍሏል። በእነዚህ ሁለት ርዕሶች ውስጥም የሴቶችን በጎና እኩይ ገፅታዎች ያሳያሉ የተባሉ ተረቶችና አባባሎች ተተንትነዋል። ከትንታኔው በኋላ አጥኚው ሴቶችን በአዎንታዊ ገፅታቸው ከሚስሉት ይልቅ አሉታዊ ገፅታቸውን የሚያነሱ ተረቶችና አባባሎች በዛ ብለው ይገኛሉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። አዎንታዊ ገፅታቸው ከተነሳም በተናጠል ሲነሱ ማለትም እናት ወይም ሚስት ሆነው ሲሳሉ እንጂ በጋራ ‹‹ሴቶች›› ተብለው ሲጠሩ እኩይ ገፅታቸው ደምቆ እንደሚሳል ማጠቃለያው ላይ አስቀምጧል። ጥናቱ በዚህ ማህበረሰብ ያገኛቸው ተረቶችና አባባሎች የሴቶችን ትክክለኛ ገፅታ የሚያደበዝዙ ወይም የሚያበላሹ ሆነው ነው የተሳሉት ባይ ነው።

ሌላው ጥናት ሴና ጎንፋ ቱሉ በ2008 እ.አ.አ. “The images of women in the proverbs and sayings of the Oromo: The Case of west Arsi Zone” በሚል ርዕስ የሰራው የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጥናት ነው። የዚህ ጥናት አላማ በተረትና ምሳሌዎችና አባባሎች ውስጥ ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ መመርመር፣ ስለሴቶች የሚናገሩት ተረትና ምሳሌዎቹና አበባሎቹ ተፅዕኖ ላይ ህብረተሰቡ ያለውን ግንዛቤ መመርመር፣ የተረትና ምሳሌዎቹ እና የአባባሎቹ መተላለፍ አሁን ያለውን የሴቶች ምስል ለመጪው ትውልድ እንዲቀጥል የሚያመቻች መሆኑን መመርመር፣ በተረትና ምሳሌዎቹና በአባባሎቹ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙ ፆታዊ ሚናዎችና የማህበረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ አመለካከቶች ካሉ መመርመር፣ እንዲሁም ለተነሱት ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ የሚጠቁም አስተያየት መስጠት ነው።

በትንታኔው ውስጥ የምዕራብ አርሲ ኦሮሞዎች ስለተረትና ምሳሌዎች ያላቸውን ጽንሰ ሃሳባዊ እይታና የተረትና ምሳሌዎቹን ተግባር ለማየትና ምሳሌዎቹ በብዛት በማን

እንደሚነገሩ፣ በተረትና ምሳሌዎቹና በተረቶቹ ውስጥ የሚታየው ሴቶች ምስል ከሴቶቹ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ሞክሮዋል። የቤተመፃህፍት ንባብና የመስክ ስራ ይህንን ጥናት ለማካሄድ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች ናቸው።

ከላይ የተገለፁት ሁለቱም ተመራማሪዎች ፎክሎራዊ ገፅታ ባላቸውና ጥናቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ባሉ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚነገሩት ተረቶችና አባባሎች ያላቸውን ተዕዕኖ አሉታዊነት በማመን ለጥናት የተነሱ ይመስላሉ። የሴና ጎንፋ ጥናት ወንዶችና ሴቶች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ በእኩል መንገድ መታየት እንዳለባቸውና የማህበረሰቡ አባላት ከቋንቋ አጠቃቀም ጀምሮ የፆታን እኩልነት እየተማሩ ማደግ እንዳለባቸው ይገልፃል። በባህል ጥናት ውስጥ የአንድን ማህበረሰብ ፎክሎራዊ ገፅታ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ የመዳኘትና ግለሰባዊ አስተያየቱን የማንፀባረቅ ስልጣን አለው ብዬ አላምንም። ማህበረሰቡ ልክ ነው ብሎ የሚያምንበት ጉዳይ አባላቱን እኩል አያይም ብሎ ሶስተኛው ወገን ቢያምን እንኳ ያንን የጥናቱ ትንታኔና ውጤት እንዲያሳየው ማድረግ እንጂ እንደግለሰብ አስተያየት መስጠት በፎክሎር ጥናት ውስጥ ምሁራዊ አካሄድ አይደለም። ብርሃኑም የተነሳበት አላማና መጨረሻ ላይ የሚሰጠው ማጠቃለያ የሚጋጩ ናቸው። ተረቶቹና አባባሎቹ ትክክል አይደሉም ብሎ ካሰበ እነዚህን ተረቶች ማቆየት የሚለው የጥናቱ አላማ ያለውን ፋይዳ መግለፅ ይገባው ነበር።

ከመመረቂያ ስራዎች ውጪ በልዩ ልዩ ህትመቶች ውስጥ ሴቶችንና ተረኮችን መሰረት አድረገው የወጡ ጥናቶች አሉ። አብርሃም አለሙ Oral narrative as ideological weapon for subordinating women: the case of Jimma Oromo (2007) በሚል ርዕስ የፃፈው ጥናት አንዱ ነው። አብርሃም የስርዓተ ፆታ ኢ-እኩልነት (Gender Inequality) ማህበረሰቡ በሚጋራው እምነት፣ ልማድና ተግባሮች ውስጥ የሚተክልና የማህበረ-ባህል ስሪት ውጤት እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ይገልፃል። የስርዓተ ፆታ ጎራ በአብዛኛው ለወንዶችና መገለጫዎቻቸው አዎንታዊ ዋጋ የሚሰጡ፣ በተቃራኒው የሴቶቹን ደግሞ የሚያሳንሱ ተደርገው እንደሚደዘጋጁ ይገልፃል። እንደጅማ ኦሮሞ ባሉ የቃላዊ ባህል ማህበረሰቦች ውስጥ ብዙዎቹ የስርዓተ ፆታ ስርዓት (Gender System) ላይ ትኩረት የሚያደረጉ እሳቤዎችና ልማዶች በተለያዩ የፎክሎር ቅርፆች ይገለፃሉ። ከእነዚህ

ውስጥ ሚት፣ ታሪካዊ ተረኮች እና የመሳሰሉት ሴቶች ከወንዶች እንደሚያንሱ ለመግለፅና ያንንም ለማቆየት ላቅ ያለ ሚና እንዳላቸው ይገልፃል።

አብርሃም በጥናቱ ውስጥ የጅማ ኦሮሞ ሴቶች በማህራዊ፣ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ መሪነትን፣ ለውሳኔ ሰጪነት ወይም ደግሞ ለአማካሪነት ሴቶችን ማሰብ የማይቻል መሆኑን ይገልፃል። ይህም በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የማህበረ-ፖለቲካ ተቋም የሆነው የገዳ ስርዓት በውስጡ የሴቶች ሃላፊነት ላይ ቦታ አለመኖሩን መጥቀስ ይቻላል። ከዚህም የተነሳ ይመስላል በቋንቋው ንግስት ወይም ልዕልት የሚል ቃል አለመኖሩን ይገልፃል። ቃላዊ ተረኮች ለሴቶች የበታችነት ማረጋገጫነት ትልቅ ሚና የሚጫወቱ መሆኑን ጥናቱ ገልፆ በተለይ በተረኮቹ ውስጥ የምትነሳው ‹‹መካ ወሬ›› የምትባል ሴት በመሪነት የነበራትን ሃላፊነት የግል ስሜቷን ለማስተናገድ ስትል በአግባቡ አለመወጣቷ ሴቶች የአመራር ሃላፊነትን ለመሸከም የሚያስችል ጫንቃ እንደሌላቸው ለማሳየት ከሚጠቀሙባቸው ተረኮች አንዱ እንደሆነ ይገልፃል።

አብርሃም ከአካባቢው የሰበሰባቸውን ተረኮች ‹‹ሴና›› እና ‹‹አዱ ዱብሪ›› በሚል በአካባቢው የአከፋፈል ዘዴ ተጠቅሞ የከፋፈላቸው ሲሆን የመጀመሪያው እውነትና የማህበረሰቡ ታሪክ ናቸው ተብለው የሚታሰቡት የሚወሩበት፣ ሁለተኛው ደግሞ በቀልድና በጨዋታ የሴቶች ስቴሪዮታይፕ የሚገለፁባቸው እንደሆኑ ይገልፃል።

አብርሃም የጥናቱን ድምዳሜ ሲያስቀምጥ ብዙዎቹ ቃላዊ ተረኮች የሚነገሩት በወንዶች ቢሆኑም የወንዶችን አስተሳሰብ፣ የወንዶችን የበላይነትና በሴቶች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ፈጣሪነት ከማንፀባረቅ ይልቅ የአጠቃላይ ማህበረሰቡን ርዕየተዓለምና እምነት የሚያንፀባርቁ ተደርገው ይታሰባሉ ባይ ነው። ብዙዎቹ ተረኮች ሴቶችን በተፈጥሮ በወንዶች ቁጥጥር ስር መሆን የሚገባቸውና ከወንዶች ያነሱ መሆናቸውን የሚገልፁ ናቸው። አካላዊና አእምሮአዊ ጥንካሬ ስለሚጎድላቸውም ለከፍተኛ ሃላፊነት እንደማይበቁ የሚያስተምሩና በተጨባጭ ለስርዓተ ፆታ ያለውን ማህበረአቋም የሚያጠናክሩ ናቸው ብሎ ይደመድማል።

ሌላው ጥናት መስፍን መሰለ‹‹ስለሴቶች በተቃርኖ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች››፣1991፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዘጠነኛ አመታዊ ጉባኤ ላይ ያቀረበው ጥናት ነው። የዚህ ጥናት አላማ ሴቶችን በሚመለከት በአማርኛ ምሳሌያው ንግግሮች የተገለፀው የህብረተሰብ

አመለካከት ምን እንደሆነ ማጤን፣ ስለሴቶች በምሳሌያዊ ንግግሮች የተንፀባረቀው አመለካከት ምንጭ ምን እንደሆነ መመርመር እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ስር ሰደው ያሉት ተሳሳቱ ግንዛቤዎች የሚቃኑበትን መንገድ ለመጠቆም መሞከር ናቸው።

ጥናቱ በአማራው ህብረተሰብ (አፅንኦት የራሴ) ውስጥ ሴቶች የተሰጣቸውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቦታ ለማወቅ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ እንደሚታመን አጥኚው ገልፆ ለጥናቱ የመረጣቸውን ተረትና ምሳሌዎች ‹‹የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች›› ከሚል መፅሀፍና ‹‹ምሳሌና መስተዋቱ›› ከሚል ጥራዝ መሆኑን ይገልፃል። የሴቶችን አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በጥናቱ ውስጥ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

በጥናቱ ያጋጠሙትን ችግሮች ሲገልፅ

> አንድ ምሳሌያዊ ንግግር የያዘውን መልዕክት ለመረዳት ምሳሌያዊ ንግግሩ የተነገረበትን ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ማወቅ ይጠይቃል። ከዚህም ሌላ አንዳንዶቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች ከአማርኛ ቋንቋ የሰዋሰው ስርዓትና የአረፍተ ነገር አሰካክም ያፈነገጡ በመሆናቸው የያዙትን መልዕክት በትክክል ለመረዳት አስቸጋሪ ነበሩ። ሆኖም በተቻለ መጠን አብዛኛውን የአማርኛ ተናጋሪ ህብረተሰብ (አፅንኦት የራሴ) ሊያግባባ ይችላል ተብሎ የታመነበትን መልዕክት መሰረት በማድረግ ትንተና ለመስጠት ተሞክሯል። (መስፍን መሰለ፣ 1991፣ 2)

ተብሎ የተገለፀ ቢሆንም ምሳሌያዊ ንግግሮቹ የአማራውን ህብረተሰብ የሚገልፁ መሆኑን በተደጋጋሚ መግለፁ የሃሳብ ግጭት ይፈጥራል። በአማርኛ ስለተነገሩ የአማራውን ማህበረሰብ ብቻ የሚወክሉ ናቸው ብሎ መደምደም አይቻልም። ከማህበረሰቡ ውጪ ያሉ አማርኛን ቋንቋ የሚጠቀሙ ሌሎች ብሄረሰቦች ሊገለገሉባቸው ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በባህል መወራረስ ምክንያት ከሌሎች ብሄረሰቦች የተገኙም ሊሆኑ ስለሚችል ትክክለኛ ምንጫቸው የአማራው ህብረተሰብ ላይሆን ይችላል። በመሆኑም ‹በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ የሚነገሩ› ብሎ ቢያልፋቸው ከግራ መጋባትን ማጥራት ይቻል ነበር የሚል እምነት አለኝ። እንደ ሌና ጎንፋ ሁሉ መስፍን መሰለም አሉታዊ ገፅታዎችን የሚያንፀባርቁ ምሳሌያዊ ንግግሮች ምንም ፋይዳ ስለሌላቸው

አገልግሎት ላይ መዋል እንደማይገባቸው የሚገልፅ አስተያየት በማጠቃለያው ላይ ሰጥቷል።

ሌላው ሽመልስ ግዛው (1992) ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዓውደ ጥናት ያቀረበው ‹‹የሲዳማ ሴቶች ማህበራዊ ቦታና የስነቃል ችሎታ›› የሚል ርዕስ ያለው ጥናት ነው። ጥናቱ በሀዬ/እሹሩሩ ግጥሞች ከሚነገሩ መረጃዎች ይዘት በመነሳት የሲዳማ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታና የስነቃል ግጥም ችሎታ መመርመርና ስነቃሉ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ የሚያደርጉበትን መንገድ ማጤን ነው። በዚህ ወረቀት ላይ የቀረቡት የእሹሩሩ ግጥሞች ከሲዳማ ዞን ተሰብስበው ወደአማርኛ ተመልሰው የተፃፉ ሲሆኑ በዚህ ወቅት አንዳንዶቹ ጥቂት ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል። አጥኚው ትርጉሙን የሰራው ማን እንደሆነ (ራሱ የቋንቋው ተናጋሪ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ሌሎች ቋንቋውን የሚያውቁ ባለሙያዎች እንደረዱት) የሚገልፀው ነገር የለም።

ጥናቱ እንደሚለው ሃዬን የሚያዜሙት ሴቶች ብቻ ሲሆኑ እናት የሆኑም ያልሆኑም ሊሆኑ ይችላሉ። ግጥሞቹ አሁን ያለው ትውልድ ድረስ እንዲደርሱ የሚነገርበት ቋንቋ ውበት፣ በግጥሞቹ ውስጥ የሚጠቀሱት ሃሳቦችና መልዕክቶች፣ እንዲሁም ግጥሞቹ የሚደረደሩበት ዜማ ማራኪነት እንደሆነ ገልፆ በዚህ ረገድ የሲዳማ ሴቶች ያላቸው የማስታወስ ብቃትና ላቅ ያለ የግጥም ችሎታ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ይገልፃል።

በማህበረሰቡ ውስጥ ልጅ እንደትልቅ ፀጋ ስለሚታይ ያንን ፀጋ እውን የምታደርገውን ሴት ልጅ ትልቅ ክብር እንዲሰጣት እንደሚያደርጋት በእሹሩሩ ግጥሞቹ ውስጥ ይገለፃል። የሴቶቹ ማህበራዊ ህይወት በተለይም በልጆችና በወላጆቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት፣ ሴቶች በትዳራቸው ውስጥ የሚሰማቸው ጥሩም ሆነ መጥፎ ስሜት፣ ለትዳር፣ ለቤተሰብና ለዘር የሚሰጠው ክብርና ሙገሳ በግጥሞቹ ውስጥ ይንጸባረቃሉ። በሲዳማ ታሪክ ውስጥ የምትታወቀው ንግስት ፋራ ሴቶቹ በሀዬ ውስጥ የሚያነሱት ሲሆን እሷ የተወችላቸውንና ሴቶች አሁን አግኝተነዋል ብለው የሚመምኗቸውን ፀጋዎች የእሷን ስም በመጥራት ያሞግሳሉ።

ምንም እንኳ ሀዬ እንደሌሎች የስነቃል አይነቶች በቃል የሚነገር ቢሆንም፣ የሚነገርበት ቋንቋ ሌሎቹ የስነቃል አይነቶች ከሚነገሩበት ቋንቋ የበለጠ ጥዑም የሆነና የሰርክ መጠቀሚያ ያልሆነ እንደሆነ ጥናቱ ይገልፃል።

ከላይ የተመለከትኳቸው ጥናቶች ትኩረት ያደረጉባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ከእኔ ትኩረት አቅጣጫ ጋር በእጅጉ ይቀራረባሉ። ጥናቶቹ በቃል በሚተላለፉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ውስጥ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሴቶችን ህይወት ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚቃኙ ናቸው። የእኔም ጥናት እንዲሁ የሶዶ ጉራጌ ሴቶች በማህበረሰባቸው ውስጥ በሚነገሩ የቃል ተረኮች ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና መግለፁ ላይ የሚያተኩር ነው። ይህም ከእኔ ጥናት ጋር ተዛምዶ እንዲኖራቸው አድርጓል። ነገር ግን ትኩረት ያደረጉበት ማህበረሰብና ቋንቋ የተለያየ መሆኑ ጥናቶቹ ከእኔ ጥናት ጋር ልዩነት እንዲኖራቸው አድርጓል።

በሶዶ ጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የተሰሩ ጥናቶች በርከት ብለው ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ የኔዓለም አረዶ፣ "የጥያ አካባቢ ሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች ይዘት ትንተና"(1997)፣ ተስፋዬ በሪ "የመስቀል አከባበር በክስታኔ ብሔረሰብ"(1997)፣ ሙሉነህ ጉግሳ፣ "የክስታኔ ተረቶች"(1993)፣ ሰውነት አየለ፣ " የክስታኔ የውንቂት / እንቆቅልሽ/ የቅርፅና የይዘት ትንተና"(1992)፣ መንግስቱ ተፈራ፣ "የአማርኛና የክስታንኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተመሳስሎ ንፅፅራዊ ጥናት" (1986)፣ እንግዳ ሐብቴ "በሶዶ ብሔረሰብ የጋብቻ ትውፊታዊ ድራማ" (1984)፣ አዳነ በየነ፣ "ምርቃንና እርግማን በክስታንኛ ተናጋሪዎች ዘንድ"(1981)፣ ጣሰው ተክሌ፣ "የክስታኔ ሃገረሰብ የሰርግ ባህላዊ ስርዓትና ግጥሞች"(1974)፣ ሐረገወይን ድፋባቸው፣ "የክስታንኛ የልቅሶ ግጥሞች" (1974)፣ ክንፉ ፈይሳ፣ "የክስታንኛ ተረትና ምሳሌዎች" (1964)፣ አስራት ጋሻው፣ "የክስታንኛ ግጥሞች"(1964)ን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ጥናቶች ንድፈሃሳባዊ ዳራ ቢጎድላቸውም በቋንቋው የሚነገሩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በማስተዋወቅና ሰንዶ በማስቀመጥም ረገድ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

3.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

እንደተረክ ያሉ የፎክሎር ጉዳዮች የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ይሰጥባቸዋል። ንድፈ ሃሳቦቹ የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ጉዳዮች የሚተነተኑባቸው አሊያም ደግሞ አንድ የተለየ ባህልን ወይም የአኗኗር መንገድን መሰረት ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ በዋነኛነት የስነፆታ ንድፈሃሳብን እንደቅንብብ የምጠቀም ሲሆን አፍሪካና ኦማኒዝምንም በጥቂቱ አያለሁ። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት የሚደረግባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ምንነት ማወቅ የሚያስችሉ ፅንሰሐሳቦችን እዳስሳለሁ። ጥናቱ በሶዶ ጉራጌዎች ውስጥ የሚነገሩ ተረኮች ላይ ስለሚያተኩር ተረክ ስንል ምን ለማለት እንደተፈለገና ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት ለመዳሰስ እሞክራለሁ። ስለ አፍሪካና ኦማኒዝም ዋና ዋና የሚባሉ ነጥቦችን ካነሳሁ በኋላ በይበልጥ ደግሞ ጥናቱ በተረኮቹ ውስጥ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው ስርዓተ ፆታ ሚናና ማህበራዊ ደረጃ ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተካሄደ በመሆኑ ጥናቱ የሚቃኝበትን ሌላኛው ንድፈሐሳብ ማለትም የስርዓተ ፆታ ንድፈ ሐሳብና ይህ የማጥኛ ቅንብብ ስላለው አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ፋይዳ የተሰጡ ሃሳቦችን አሳያለሁ። በመጨረሻም ፎክሎርና ስርዓተ ፆታ ስላላቸው ተዛምዶ አሳያለሁ።

3.2.1 ተረክ

በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የማህበረሰቡ አባላት ያላቸውንና ይገባችኋል የሚባሉትን ደረጃ (position) በሚነገሩና በሚከወኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮች እንዲያውቁት ይደረጋል። ከእነዚህ ጉዳዮች

አንዱ ተረክ ነው።።።

ተረክ በዝርው ወይም በስንኝ የሚነገር ታሪክ ሆኖ በውስጡ ሁነቶችን፣ ገፀባህሪያትንና ገፀባህሪያቱ የሚናገሩትንና የሚከውኑትን ጉዳይ የሚያካትት ነው:: (Abrams;1999,173) ቴዎድሮስ እንደሚለው ደግሞ ተረክ በሰፊ አገባቡ በቃል ወይም በፅሁፍ ሊቀርብ፣ በግጥም ወይም በዝርው ሊተረክ ይችላል። ከዚህም አልፎ ሊዘፈን፣ ሊደነስ፣ ሊሳል፣ ሊቀረፅ፣ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችልም ቅርፅ ነው። (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 259-260)

ተረክ በሰው ልጆች ህይወትና ታሪክ ውስጥ የሚሰጠው ቦታ ከፍተኛ ሲሆን የተረኮቹ አመጣጥ መንገድ እነደየርዕዮተ ዓለሙ በየዘመናቱ ቢቀያየርም የሰው ልጆች ራሳቸው ያለእሱ መኖር እንደማይችሉ ሉክ ሽርማንና ባረት ቬርቬክ (Luc Herman and Bart Vervaeck) እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> No single period or society can do without narratives. And, a good number of contemporary thinkers hasten to add; whatever you say and think about a certain time or place becomes a narrative in its own right. From the oldest myths and legends to postmodern fabulation, narration has always been central. Postmodern philosophers may submit that there are no longer any grand, encompassing narratives, but they also contend that everything amounts to a narrative, including the world and the self. (ሽርማንና ቬርቬክ፤ 2005፣ 1)

ተረክ ዕለት ተዕለታዊና በማንኛውም የሰው ልጆች እንቅስቃሴ ውስጥ የሚከወን ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ ሃሳቡንና እምነቱን የሚገልጽበት መሳሪያም ጭምር ነው፡፡ ሾሻና ብሉም ኩልካ (Soshana Blum-Kulka) የተረክን ዘወትራዊነት ስትገልጸው ‹‹በሚቀራረቡ ሰዎች መሃል በሚደረግ ተራ ንግግር ውስጥ ያለ ታሪክ ነገራ ከተለመዱት የተረክ ሀቲት መተላለፊያዎችና ክዋኔዎች መካከል አንዱ ነው፡›› (ብሉም-ኩልካ፤1993፣361) ትላለች፡፡ አንዳችን ለሌላኛው ታሪክ ስንነግር በውስጡ ከቋንቋም ሆነ ከስሜት አኳያ ተያያዥ በሆነ መንገድ እንደ ልምድና ገጠመኝን ማጨቂያ መንገድ እናደርገዋለን፡፡ ተረክ በአፈንጋጩና በተራው (Exceptional and Ordinary) መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት የተሰመረውን መስመር ለመመርመር እንደምንገለገልበትም ኩልካ ትገልፃለች፡፡

ይህ ጥናት የሶዶ ጉራጌ ሴቶችን ህይወት መረዳት ከሚያስችሉ የማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ገፅታዎች ውስጥ ተረክ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ተረክ በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ እሴቶች ከሚገለፁባቸው መንገዶች አንዱ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፁትን የተረክ ንድፈ ሐሳቦች በመያዝ ትኩረት ከተደረገበት ማህበረሰብ የተገኙ ተረኮች በጥናቱ ውስጥ በምዕራፍ አራት ውስጥ የሚካተቱና የሚተነተኑ ይሆናል፡፡

3.2.2. አፍሪካና ውመኒዝም

ሁሉን አቀፍ የምንላቸውን ንድፈ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የተለያዩ የጥናት ዘርፎች በየራሳቸው አረዳድ የተለያዩ ትርጉም የሚሰጡባቸው እንደ ስርዓተ ፆታ ያሉ አለምአቀፋዊ ጉዳዮች አሉ። ነገር ግን እነዚህ ንድፈሃሳቦች ሁልጊዜ ለሁሉም ማህበረሰብ እኩል ይሰራሉ ወይም የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አይደለም። እንደፎክሎር ያሉትን የውስን ማህበረሰብን መገለጫ ብቻ ሊይዙ የሚችሉ አካባቢያዊ ወይም ባህላዊ ጉዳዮችን ለመተንተንና የራሳቸውን ትርጓሜዎች የምንረዳበትን ቅንብብ ለመስራት የምንገለገልባቸው ንድፈሃሳቦች በተቻለ መጠን ባህሉን መሰረት ያደረጉ ቢሆኑ የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በተሻለ መንገድ ለመረዳት የሚያስችሉ ይሆናሉ። ይህ ማለት ግን የትኛውም ዕውቀት ዘርፍ የየራሱን መንገድ ይዞ እንዳይሄድ መገደብ አለበት ማለት አይደለም። ነገር ግን ስለማህበረሰቡ ስናወራ የምንደርስበት ድምዳሜ የተዛባ ወይም ደግም ያንን ማህበረሰብ የማይገልፅ እንዳይሆን ያግዛል።

የሴቶችን ህይወት ስናጠና ጥያቄያቸው አንድ አይነት ይሆናል የሚል ቅድመ እሳቤ ልክ አለመሆኑን የሚገልፁ የተለያዩ ምሁራን እንደምሳሌ የሚያነሱት የስነእንስት (Feminism) ንድፈሃሰብን ሲሆን የምዕራባዊያንን አስተሳሰብ፣ ልምድና ጥያቄዎች የሚንፀባርቀውን ይህንን ንድፈሃሳብ ይዞ ለአፍሪካዊያን ሴቶች ህይወት መመርመሪያነት መጠቀም ተገቢ አይደለም ባይ ናቸው። ምንም እንኳ ማህበራዊ ዳራቸው የተለያየ ቢሆን በመልክዓምድራቸው አንድ ቦታ የነበሩ ነጭና ጥቁር ሴቶች እንኳ ስነእንስታዊ አስተሳሰብ የሚቀበሉበት መንገድ የተለያየ መሆኑን አንድ ንድፈ ሃሳብ ለሁሉም ማህበረሰብ እንደማይሰራ ያሳያል። የጥቁሮችን የነፃነት ትግል እግረመንገዱን የሚደግፈው ስነእስነስታዊ ንቅናቄ ከነጭ ሴቶች ቀድሞ ለጥቁር ወንዶች የመምረጥ መብት ሲሰጥ ነጭ ሴቶች የተቃወሙ ሲሆን ጥ ቁርነታቸው የማንነታቸው አካል ለሆነው ለጥቁር ሴቶች ግን የነፃነታቸው ትግል አንድ ውጤት አድረገው ይቆጥሩት ስለነበር ከነጮቹ በተቃራኒ ደስተኞች ነበሩ። ከዚህም አልፎ የስነእንስታዊነት ንቅናቄ በተለይ የሚያተኩረው በሴቶች ግለሰባዊነት በመሆኑ ቤተሰባዊና ማህበራዊ እሴቶች በሚከበሩባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ተቀባይነቱ እምብዛም ነው። ለእነሱ ፌሚኒዝም ማለት ሂደድሰን ዊምስ የአማ አታ አይዶን

(Ama Ata Aidoo)ን ሐሳብ ባሰፈረችበት "Africana Womanism (1993)" ፅሁፏና ይህ ፅሁፍ ድጋሚ በታተመበት በ"The Womanist Reader" ላይ ተገልጿል። አይዶ እንዳለችው ‹‹ፊሚኒዝም መልካሙን አፍሪካዊ ቤተሰብ ለማጥፋት በተለይ ከአሜሪካዊያን የመጣ አሳፋሪ የምዕራባዊያን ፍልስፍና ነው›› (ፊሊፕስ፣ 2006: 44)።

የስነእንስታዊነት ሃሳብ አፍሪካ አሜሪካዊያንን ብዙም አይመለከትም በሚል የውመኒዝምን ሃሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያነሳቸው ጥቁር አሜሪካዊቷ ደራሲ አሊስ ዎከር (Alice Walker:), "In search of our mothers' gardens (1993)" በሚለው የመጣጥፎች ስብስብ ውስጥ ነው። ነገር ግን የውመኒዝም ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ አፍሪካዊያንን እንዲወክል አፍሪካና ውመኒዝም የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ያመጣችው ክሌኖራ ሂዩድሰን-ዊምስ (Clenora Hudson-Weems) ናት። ዊምስ በአፍሪካና ውመኒዝም አስፈላጊነት ላይ በርከት ያሉ ፅሁፎችን በጆርናሎች ላይ ጽፋለች ፣ መፃህፍ ትንም አሳትማ ለች። ከእነዚ ህም ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሃሳቡን ያነሳችባቸው "Cultural and Agenda Conflicts in Academia: Critical Issues for Africana Women's Studies" (1989) እና "Africana Womanism" (1993) የተሰኙ ፅሁፎቿ እንደሆኑ የሴቶች ጥናት ላይ ያተኮሩ ፅሁፎችን በመሰብሰብ በአርታኢነት The Womanist Reader (2006) በሚል ያሳተመችው ላይሊ ፊሊፕስ (Layli Phillips) ትገልፃለች። (ፊሊፕስ፤ 2006፣ xlii)

ዊምስ አፍሪካና ውመኒስት የሚከተሉት አስራ ስምንት መገለጫዎች እንዳሏት በተለያዩ ንድፈ ሐሳቡን በሚያነሱ ፅሁፎች ውስጥ ተገልጿል።

> self-naming, self-definition, role flexibility, family-centeredness, struggling with males against oppression, adaptability, Black female sisterhood, wholeness, authenticity, strength, male compatibility, respect, recognition, respect for elders, ambition, mothering, nurturing, and spirituality. (ስቴፈንስ፣ኬቨኒ እና ፓተን፤ 2002፣ 470፣ ፍሎይድና ሲመን፤ 2006፣ 69)

እነ እስቴፈን ዊምስ ያወጣቻቸው አስራ ስምንት የአፍሪካና ውመኒስት መገለጫዎች በስድስት ዋና ዋና ፅንሰ ሐሳቦች ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ ይገልፃሉ። ከእነዚህም ማንነት፣ ለቤተሰብና ለእናትነት የምትሰጠው ክፍ ያለ ዋጋ፣ የማህበረሰብ ጉዳይ፣ መንፈሳዊነት፣ ለታላላቅ (elders) የማህበረሰቧ አባላት የምትሰጠው ክብር እና ለሴቶች በሚሰጠው ደረጃ

ምንም ይሁን ምን ከዚያ ጋር ራሷን አስማምታ የመኖር አቅሟ ናቸው (እነ ስቱፈን፡ 2002፣ 470-471)::

እነዚህ የአፍሪካና ውመኒስት መገለጫዎች ብዙዎቹ ጥናት ባደረኩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች ላይ የሚታዩና የሚጋሯቸው ባህሪያት በመሆናቸው ይህ ንድፈ ሐሳብ በዚህ ጥናት ውስጥ ተካቷል::

3.2.3 ስርዓተ ፆታ

በዘመናዊው የስነሰብዕ ጥናት ውስጥ ተመራማሪዎች ከሚያተኩሩባቸው ማህበረሰባዊ ጉዳዮች አንዱ ስርዓተ ፆታ ሲሆን የዘርፉ ተመራማሪዎች በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ተደጋጋፊም ተቃራኒም ሃሳቦችን ሲያነሱ ቆይተዋል፣ እያነሱም ነው:: ስርዓተ ፆታ ከሰዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ጋር የማይነጣጠል ቁርኝት አለው::

ስርዓተ ፆታ የማህበረሰቡን እምነት፣ አመለካከትና ባህል ተንተርሶ የሚሰራ በመሆኑም የማህበረሰቡ አባላት ፆታቸው የትኛው ስርዓተ ፆታ ውስጥ እንደሚያስመድባቸው፣ በተመደቡበት ስርዓተ ፆታ ውስጥም እንዴት መሆንና ማድረግ እንደሚገባቸው እንዲሁም ከሌላኛው ስርዓተ ፆታ አባል ምን እንደሚለያቸው የሚረዱበትን ስርዓተ ፆታዊ ህግጋት በህይወት ሂደታቸው የሚማሩበት ነው::

የማህበረሰብ ሳይንስ ለስርዓተ ፆታ የሚሰጠው ብያኔ ሶስት ዕንሰ ሐሳቦችን መሰረት እንደሚያደርግ የሚገልፀው ሪቻርድ ኡድሪ (Richard Udry) ነው:: (ኡድሪ፣ 1994፣ 563):: እነዚህም ዕንሰ ሐሳቦች ስርዓተ ፆታዊ ሚና፣ ማህበራዊ ግንኙነት እና ዕጣፈንታዊ መዋቅር ናቸው:: ኡድሪ ስለእነዚህ ዕንሰ ሐሳቦች ትስስር ሲያስረዳ ስርዓተ ፆታዊ ሚና በስርዓተ ፆታ ልማዶች ተቀባይነት ያለው ባህሪ እንደሆነ፣ ይህ ተቀባይነት ያለው ባህሪ የሚወሰነው ወይም ድንበር የሚበጅለት ደግሞ ፆታን መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህንን ድንበር መጣስ ቅጣት እንደሚያስከትልና ዕጣ ፈንታዊው መዋቅር ላይ ችግር እንደሚፈጥር ይገልፃል::

የስነማህበረሰብ ባለሙያዋ ሜሪ ሆልምስ (Mery Holmes) Gender and Every Day Life (2009) በሚለው መፅሀፏ እንደምትለው በዘመነኛው ማበረሰብ የተለያዩ ወንዶችና

ሴቶች ስርዓተ ፆታቸውን በተለያየ መንገድ ይማሩታል፤ ይከውኑታልም። የስነማህበረሰብ ተማራማሪዎች ግን የተወሰኑ ቡድኖች ስራተፆታን ለምን በተመሳሳይ መንገድ ሊማሩ እንደቻሉ ማወቅ የሚያስችሏቸውን ቅጦች (Patterns) ይፈልጋሉ። ሆልምስ ሰዎች ስርዓተ ፆታን የሚከውኑበት መንገድ ባሉበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰባቸው በሚኖርበት አካባቢም ጭምር ይወሰናል ትላለች። (ሆልምስ፣ 2009፣ 43)

ሆልምስ ከላይ በተጠቀሰው መፅሃፏ ውስጥ ስርዓተ ፆታን በተለያየ መንገድ የሚመለከቱ ምሁራንን ሃሳቦች አሳይታለች። በተለይ ስርዓተ ፆታ ከቀደመው ፆታን ከስነተፈጥሮ ጋር አያይዞ ትርጓሜ ከመስጠት አስተሳሰብ ባለፈ ከሰዎች ማህበራዊ ግንኙነት አኳያ የተቃኙ ሃሳችቦችን ያነሱ ምሁራንን ሃሳብ በዝርዝር አሳይታለች።

ሆልምስ ከጠቀሰቻቸው ምሁራን መካከል አንዷ የስነማህበረሰብ ተመራማሪዋ አን ኦክሌይ (Ann Oakley) ናት። ኦክሌይ እንደምትለው ሰዎች መደበኛውን ሴታዊና ወንዳዊ ባህሪያትን እንዲከውኑ የሚማሩት በማህበራዊ ግንኙነታቸው ሂደት ውስጥ ነው። በተለይ በቤተሰብ ውስጥ በልጅነት ዘመን የሚደረገው ማህበራዊ ተራክቦ እንደየስርዓተ ፆታቸው እንዴት መሆንና ማድረግ እንደሚገባቸው ለማስተማር ወሳኝ ጊዜ ነው። ህፃናት የሚለብሱት ልብስ ቀለምም ሆነ ለመጫወቻነት የሚሰጣቸው የቁስ አይነት ወንድ ወይም ሴት መሆናቸውን መሰረት በማድረግ በማህረሰባቸው ውስጥ የሚኖራቸውን ሚናና ማሳየት የሚገባቸውን ባህሪ መማር የሚጀምሩበት እንደሆነ ታነሳለች። (ሆልምስ፤ 2009፣ 46)።

ስርዓተ ፆታ የልጅነትን ዘመን ጨምሮ ከሚገነባባቸው መንገዶች አንዱ የአመጋገብ ስርዓተ ነው። የምግብ አጠቃቀም በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚኖረው ጠቀሜታ ከመሰረታዊ የሰው ልጆች ፍላጎት ውስጥ አንዱን ከማሟላት አኳያ ብቻ ላይታይ ይችላል። በማህበረሰቡ ውስጥ የደረጃ ልዩነት ለመፍጠርና ያንን ለማፅናት እንደመጠቀሚያነት ያገለግላል። ይህንን ሃሳብ ጉመርማን እንደሚከተለው ያጠናክረዋል።

> Recently, archaeologists have contemplated social relations and symbolism through the detailed study of food ... Typically, these are fine-grained approaches that accept the existence of economic, political, and ideological variation within societies and

even variation within households such that males may eat differently than females. (ጉመርማን፤ 1997፣ 106)

በሌላ በኩል የምግቡ አይነትና መጠንም ጭምር ስርዓተ ፆታዊ ልዩነትን መሰረት በማድረግ ሊሰራና አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል። ዊሊያም ሻክ (William Shack) በ1971 እ.አ.አ. የጉራጌን ማህበረሰብ የአመጋገብ ሁኔታ በተመለከተ Hunger, Anxiety, and Ritual በሚል ርዕስ በፃፈው ጽሑፍ የጉራጌ ወላጆች ራሳቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆቻውን የሚመግቡበት መንገድ አንድ እንዳልሆነ ይገልፃል። ወላጆች ከሴት ልጆቻው አስቀድመው ወንድ ልጆቻቸውን የሚመግቡ ሲሆን ሴት ልጆች ከመመገባቸው በፊት ለወንድሞቻቸው ምግብ ከማብሰል በተጨማሪ ምግቡን የማቅረብ ሃላፊነት እንደሚሰጣቸውና ከዚያም በኋላ ምግብ የመብላት ተራቸው ሲደርስ የሚሰጣቸው የምግብ መጠን ከወንድሞቻቸው የሚያንስ መሆኑን ይገልፃል።

መደብ፣ ዘርና የስርዓተ ፆታ ተዋረድ ከሚገለፁባቸው መንገዶች አንዱ ምግብ ላይ ያለ የመቆጣጠር ስልጣን እና ምግብ የማግኘት ዕድል መለያየት ነው። ብዙ ጥናቶች ወንዶች ከጊዜ ከሴቶች ቀድመው፣ ምርጡንና በመጠንም በዛ ያለ ምግብ እንደሚመገቡ ያሳያሉ (ኮኒሃን እና ኤስተሪክ፤ 2012፣2)። የተለያየ ምግብን የመጠቀም አካሄድ ሀብታምን ከደሀ፣ ሴትን ከወንድ መለያ ነው። (ዝኒ ከማሁ ፣ 3)

ኧርቪንግ ጎፍማን (Erving Goffman) ደግሞ ማህበራዊ ግንኙነት እኛ የምንተውንበት ድራማ ነው ይላል። የራሳችንን ሚና ብንጫወትም እንደየታዳሚው ሚናችን ሊቀያየር ይችላል ባይ ነው። ሆልምስ ጎፍማንን ጠቅሳ እንደፃፈችው‹‹ስርዓተ ፆታም ወንድነትና ሴትነት (Masculinity and Femininity) በተመለከተ በሚፃፍልን ማህበራዊ ቃለተውኔት/Social Script/ መሰረት በማህበረሰባችን ውስጥ የሚሰጠንን ሚና እንድንተውን የሚያደርገን አንዱ ሁኔታ ነው።›› (ሆልምስ፤ 2009፣ 50)

ጎፍማን እንደሚለው ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ በግንኙነቱ ውስጥ የሚሳተፈው ማን እንደሆነ፣ በግንኙነቱ ውስጥ ምን አይነት ሚና ሊኖራቸው እንደሚችልና እንዴት እንደሚሰማቸው፣ምን እንደሚጠብቁ የሚጠቁሙ ማሳያዎችን እንጠቀማለን። እነዚህ ማሳያዎች ብዙ ጊዜ ከሰዎች ጋር እንዴት እንደምንግባባና እንደምንገናኝ የሚወስኑ

ሆነው የተዋቀሩና ከቃል ይልቅ በድርጊት የሚገለፁናቸው። ለምሳሌ ሴቶች ሁልጊዜ በአካላዊ አቅም ከወንዶች ያንሳሉ ብቻ ሳይሆን ከበድ ያሉ ዕቃዎችን ለማንሳት የወንዶችን ዕርዳታ ይፈልጋሉ ብሎ መገመትና ዕርዳታ ለመስጠት መሞከር እዚህ ሐሳብ ውስጥ ተካቷል። (ዝኒ ከማሁ፣ 51)

ሆልምስ ያነሳቸው እንደ ጋርፊንክል (Garfinkle) ያሉ የሲምቦሊክ ኢንተርአክሽኒዝም ሃሳብ አቀንቃኞችን ነው። ለእነሱ የስርዓተ ፆታን ድርጊት ወይም ክዋኔ በትዕምርታዊ ግንኙነቶች ይበየናል። ጋርፊንክል ይህንን ሐሳብ ሲገልፅ ብዙ ጊዜ ሴቶች የበለጠ ሴትነታቸውን ለማጉላት በሰውነታቸው ላይ ያለውን ፀጉር በመላጨት፣ መዋቢያ ቁሶችን በመጠቀም እንዲሁም ለአለባበሳቸው ጥንቃቄ በማድረግ የበለጠ ሴታሴት ለመሆን ጥረት ሲያደርጉ ወንዶችም የሰውነት ጡንቻቸውን በማዳበር፣ እንባቸውን በአደባባይ ላለማሳየት ዋጥ በማድረግና በመሳሰሉት ወንድታቸውን ለማሳየት ይጥራሉ ሲል አካላዊ ገፅታችን ላይ የምናሳየውና ስሜታችንን የምናንፀባርቅባቸው መንገዶች የስርዓተ ፆታችን መገለጫ ትዕምርቶች ናቸው። (ሆልምስ፣ 2009፣ 49)

ምንም እንኳን የሚገነባበትና የሚሰራበት መሰረት እንደየማህበረሰቡ ባህልና እምነት የተለያየ ቢሆንም ስርዓተ ፆታን በሚመለከት መልኩ በመገንባትና በማፅናት ረገድ ዋነኛው ተዋናይ ማህበረሰቡ ራሱ እንደሆነ በተለያዩ ተመራማሪዎች የታመነበት ሲሆን ከላይ የተገለፁት ሐሳቦችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው። የስነእነስታዊያንን ንድፈ ሀሳብ መሰረት አድርጋ የስረዓተ ፆታን ማህበረ-ባህላዊ ስሪትነት በተ መለከተ አሰራሩ ላይ ጥያቄዎች የምታነሳው ጁዲዝ በትለር ናት።

> When Feminist theorists claim that Gender is culturally constructed, what is the manner or mechanism of this construction? If gender is constructed, could it be constructed differently, or does its constructdness imply some form of social determinism, foreclosing the possibility of agency and transformation? Does "construction" suggest that certain laws generate gender differences along universal axes of sexual difference?.." (በትለር፣ 1990፣ 7)

በትለር እንደምትለው ስርዓተ ፆታን ስለሚሰራው ባህል የሚኖረው አረዳድ የሚቀጥልና የማይቆም የሚመስል ባህላዊ ህግ እንደሆነ ሲሆን ልክ እንደስነተፈጥሮአዊው ፆታ ሁሉ

ስርዓተ ፆታም ዕጣ ፈንታዊና የማይለወጥ የሚመስል ይሆናል። ታዲያ በዚህ አረዳድ ዕጣ ፈንታ የሚሆነው ስነተፈጥሮ ሳይሆን ባህል ይሆናል ማለት ነው። የበትለር ሃሳብ ወንድ ወይም ሴት ሆኖ መፈጠር የምርጫ ሳይሆን የዕድል ጉዳይ ነው። ስራተፆታዊ ህጎቹ የማይቀየሩና ዘላለማዊ የሚመስሉ እንደሆኑና ስራተፆታን ለራሱ እንደሚመቸው አድርጎ በሚሰራ ባህል ውስጥ መፈጠርም እንዲሁ የዕጣ ፈንታ ጉዳይ ይሆናል።

በትለር እንዳለችው የስርዓተ ፆታ ህግጋት በአንዳንድ ማህበረሰብ ውስጥ ቀኖናዊ ሆኖ እንዲቀጥል፣ በየማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን ሚናና ተግባር ተቀባይነት እንዲኖረውና ተቀባይነቱንም እንዲቆይ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አሉት። ሂደቶቹና ውጤቶቹ በሃይማኖት፣ በህግ፣ በሳይንስ፣ በጥበብና በ ሌሎች የማህበሰረሰቡ አጠቃላይ እሴቶ ች አማካይነት ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ፀንተው እንዲቆዩ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። (ኔኖላ፤ 1993፣ 53) እነዚህ ማህበረ-ባህላዊ ተቋማት ገገርና አንዳንዱም የማይደፈሩ ተደርገው ስለሚታሰቡ በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ በተናጠልም ሆነ በጋራ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅማቸው ጠንካራ ነው።

ምንም እንኳ ብዙ ባህላዊ የማህበረሰብ ቡድኖች የስርዐተፆታን ልዩነት በማቆየት ረገድ ጥብቅ ቢሆኑም በሌሎች ማህበራዊ ቡድኖች ውስጥ ልዩነቱ እየደበዘዘ ነው። ቀደም ሲል በትለር እንደገለፀችውም ማህበራዊ ስሪት መሆናቸውና በየማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የሚያመጧቸውን ሃሳቦች መነሻ በማድረግ በጊዜ ሂደት እየተቀየሩና እየደበዘዙ የሄዱ ስርዓተ ፆታዊ ሚናዎች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ያነሳሉ። ስርዓተ ፆታ አንደኛው ባህሪ ባለበት የሚቆም ሳይሆን ሰዋዊ ጉዳይ በመሆኑ በመፈጠሩና እንደገና በመፈጠሩ ምክንያት የተለያዩ ማህበረሰቦች ለስርዓተ ፆታና ለህግጋቱ ያላቸው እሳቤና ተገገርነት እየተቀያየረ ሲመጣ ይታያል።

ይህንን ሐሳብ በተመለከተ ሆልምስ ስታነሳ ‹‹በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች በእነሱ ዘመን ሴቶች ‹እነደዚያ ያለ› ልብስ መልበስ እንደማይፈቀድላት፣ ወይም ወንዶች ሴቶችን ‹በአግባቡ› ይንከባከቡ እንደነበርና አሁን ባለው ሁኔታ ደስተኞች እንዳልሆኑና በዚህ ዘመን ስርዓተ ፆታ የሚከወንበት (doing gender) መንገድ ደስ እንደማያሰኛቸው ሊናገሩ ይችላሉ።›› (ሆልምስ፤ 2009፣ 41)።

ጥናት ባካሄድኩበት አካባቢ ስርዓተ ፆታየሚከወኑባቸው የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተቀየሩ ወይም እየተቀየሩ ያሉ አካሄዶች እንዳሉ ተመልክቻለሁ። ‹በእኛ ጊዜ› እና ‹አሁን› እያሉ የሚገልጿቸው ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ የሴቶች ጋብቻ በሚመሰርቱበት ወቅት የነበራቸውና አሁን ያላቸው የመወሰን ንን ስ ልጣን እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

3.2.4. ስርዓተ ፆታ እና ፎክሎር

በብዙ የጥናት መስኮች ውስጥ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ እንደየመስኩ አላማና የትኩረት አቅጣጫ ይቃኛል። ‹‹እንደሌሎቹ የጥናት መስኮች ሁሉ በፎክሎርም ውስጥ የስርዓተ ፆታ ጉዳይን ማንሳት የብዙ ምሁራንን ትኩረት መሳብ ከጀመረ ጥቂት አስርት አመታት የሆኑት ሲሆን ቀደም ሲልየነበረው የፎክሎር አረዳድ በዚህም መንገድ እንደገና መቃኘት እንዳለበት በተደጋጋሚ አስተያየት እየተሰጠ እንዳለ ሪስቶ ጃርቭ (Risto Jarv) ትገልፃለች። (www.folklore.ee/folklore/vol29/gender)

ፎክሎር ሰዋዊ ጉዳይ በመሆኑና የሰው ልጆች ስንል ደግሞ በአብዛኛው ሴቶችና ወንዶች በሚል የተመደቡትን ሰዎች ማለታችን እስከሆነ ድረስ የትኛውንም የፎክሎር ገፅታ ያላቸውን ጉዳዮች ስንመለከት ጉዳያቸው የሁለቱ ስርዓተ ፆታ አባላት ግንኙነት እንደሆነ አይሊ ኔኖላ (Aili Nenola) እንደሚከተለው ትገልፃለች።

> Folklore, insofar as it is about human beings, is about men and women and their relations. For example, any collection or selection of proversbs has its own section on these issues. Jokes are full of sex and gender stereotypes. Folktales, especially fairytales, have been read inorder to findout what tring boys and girls, women and men, are like in them (ኔኖላ፤1993፤50)

የሴቶች ጥናት ባለሙያዋ አይሊ ኔኖላ ‹‹Folklore and the Genderized World(1993)›› በሚለው መጣጥፏ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ስርዓተ ፆታ ያለውን ሚና ሰፋ አድርጋ ገልፃለች። ኔኖላ እንደምትለው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንዳለ ጥበባዊ፤ ትውፊታዊ ወይም ቃላዊ መግባቢያ፤ ፎክሎር የባህላዊ ሀቲት አካል ነው። ልክ እንደሌሎቹ የባህል አካላት፤ የቡድኑን ህይወትና ርዕዮተ ዓለም የሚያንፀባርቅና ተጽዕኖ የሚሳድር

ነው። የማንኛውም ተፈጥሮአዊ-ሰዋዊ (Natural Human) ቡድን ውስጥ፣ የማህበረሰቡ አባላት ‹ሴቶች› እና ‹ወንዶች› ናቸው። ይህንንም ስታስረዳ ስነተፈጥሮአዊው ፆታ እና ከፆታ ጋር የሚያያዙ ወይም የሚጫኑ ባህላዊና ማህበራዊ ገፅታዎች የያዘው ስርዓተ ፆታ፣ የግለሰቦችንና የማህበረሰቡን ህይወት የሚቀርፁ ናቸው። ስርዓተ ፆታ የማህበረሰብ ስራት በመሆኑና ተፈጥሯዊ ባለመሆኑ ቋሚ እንዳልሆነ ስትገልፅም በዘመናዊው አለም ያለው በሴቶች ላይ ያለ የደረጃ ለውጥና በወንዶችና ሴቶች መካከል ያለው ግንኙነት ለፆታና ለስርዓተ ፆታ ይሰጥ የነበረውን የቀደመ አስተሳሰብ የሚፈታተን እደሆነ ትገልፃለች(ኔኖላ፣ 1993፣ 51)። በእርግጥም በማህበረሰቡ ውስጥ ወንድነት ወይም ሴትነታቸው ጥያቄ ውስጥ ላይገባ የሴቶች የሚባሉ ሚናዎችን የሚወስዱ ወንዶች እንዲሁም የወንዶቹን የሚተገብሩ ሴቶች አሉ።

የስራተ ፆታ ጉዳይ ገንኖ ከሚወጣባቸውና፣ የማህበሩ አባላትም ጉዳዩን ከሚማሩበት ብቻም ሳይሆን ከሚሰሩበት ማህበራዊ ክንዋኔዎች ውስጥ ቃላዊ ትውፊት አንዱ ነው። ፆታና ስርዓተ ፆታ በቋንቋችን፣ በማህበራዊ መዋቅራችንና በባህላችን ውስጥ የሚፈጠሩ ናቸው። ለዚህም ነው ስርዓተ ፆታ በሀቲት ውስጥ የሚፈጠር ክስተት ነው የምንለው። (ኖኔላ ፤1993፣ 51) ኖኔላ እንደ ምሳሌ ስታነሳም በእንቆቅልሽ ውስጥ ነገሮች ወይም ክስተቶች የወንድ ወይም የሴት ስያሜ እንደሚሰጣቸው ወይም የተለያዩ እንስሳትና ዕፅዋት በቃል ግጥሞች ውስጥ የሚኖራቸውን ውክልና ማየት ይቻላል። እነዚህ የውክልና ሂደቶችና መንገዶች የፆታና ስርዓተ ፆታን ባህላዊ ትርጓሜ የምንማርበት ሂደት አካላት ናቸው። በሌላ አባባል ፆታ፣ ፣የስነልሳናዊ ቋንቋ እውነታና ትዕምርታዊ ደረጃ በባህላዊ የእርስበእርስ ግንኙነት ወቅት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ናቸው።

በተጨማሪም የፆታና የስርዓተ ፆታ ሀቲት እጅግ ወሳኝና የትርጉም ጥያቄም ጭምር ሲሆን ማህበራዊ ቦታን የሚያደራጅ መመሪያ ሆኖም እንደሚያገለግል ትገልፃለች። ይህንን ሂደት የስርዓተ ፆታ ስርዓት (System) ልንለው እንችላለን። ኖኔላ ይህ የስርዓተ ፆታ ስርዓት ታሪካዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ በሆነ መንገድ አንዱን ማህበረሰብ ከሌላው የሚለይ መሆኑን ትገልፃለች። የተለያዩ ስነሰብ ተመራማሪዎች እንደሚስማሙበት የወንድና የሴት ባህሪ፣ ብቃት እንዲሁም መገለጫዎቻቸው የሚባሉት ነገሮች ወይም ለሴትና ለወንድ የሚፈቀዱ

ነገሮች በሁሉም ቦታ አንድ አይነትና አለምአቀፋዊ አለመሆናቸውን ታስረዳለች። (ኔኖላ 1993፣ 52)

ኖኔላ የስርዓተ ፆታ ስርዓት ምን እንደሚመስል ስታስረዳም ጎንዮሻዊና ተዋረዳዊ ሆኖ ለወንዶች የሚያደላ እንደሆነ ታምናለች። ምክንያቱም የስርዓተ ፆታ ስርዓት በሌላ በኩል ስልጣንና ክብር ለወንዶችና ለሴቶች በእኩል መንገድ የማይደርስበት የሃይል ወይም የስልጣን ስርዓትም ሆኖ ያገለግላል። ስርዓቱ ወንዶች ተፅዕኖ የሚፈጥሩበት፣ ሴቶች ደግሞ ለተፅዕኖው ራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡበት ነው። ይህ ስርዓት እንደ ቤተሰብ፣ ፖለቲካ፣ ምጣኔ ሃብት ያሉ ማህበራዊ ተቋማት ጋር የሚገናኝ ነው።

የዚህን ስርዓተ ፆታ ስርዓት ዘላለማዊ አለመሆን ስታስረዳ በገሃዱ አለም ፀንቶ የሚቀር ወይም የማይነቃነቅ የስራተ ፆታ ሲስተም የለም ትላለች። ተለምዷዊ ወይም ርዕየተአለማዊ አቀራረቦችም በዚያ አቅጣጫ እየተቃኙ ያሉ ይመስላሉ። ስርዓተ ፆታ ዊ መገለጫዎችን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እውነታዎችን እንዲሁም ባህላዊ ፅንሰሃሳቦችን አልፈን የምንሄድበት ቅንብብ ተ ደርጎ መታሰ ብ ይች ላል። በተ ለይ በዘመናዊው ማህ በረሰብ ውስጥ እነዚ ህ እውነታዎች እየተነቃነቁና እየተቀየሩ ነው። (ኔኖላ፤ 1993፣53-54)

ሴቶች ከፎክሎር ጋር ያላቸውን ግንኙነትና በተለይ ከማስተላለፍ አኳያ ስታነሳ ወንዶችም ሴቶችም የባህል ፈጣሪና አስተላላፊ እንደሆኑ ብዙ ፎክሎሪስቶችና የስነፅሁፍ ባለሙያዎች ይመሰክራሉ ባይ ናት። ሴቶችን ከቃላዊ ትውፊቶች ፈጣሪነት ወይም ከዋኝነት ሚና አጥኚዎቹ አውጥተዋቸው አያውቁም። በቀደመው ዘመን የትምህርት ዕድል በስፋት ይሰጥ የነበረው ለወንዶች ስለነበር በፅሁፋዊው ባህል ቅርስ ወንዶች የተሻለ ሚና እንደደነበራቸው ገልፃ መናገር/መተረክ እና መዘመር የሰው ልጆች በተፈጥሮ የሚሰጧቸው ስጦታዎች በመሆናቸው በዚህ ረገድ የሴቶች ሚና ከፍተኛ እንደነበር ትገልፃልች። ምን፣ እንዴትና የት እንደሚናገሩና እንደሚዘምሩ የሚፈቅድላቸውና የሚያዛቸው ማህበራዊና ባህላዊ ልማድ ቢሆንም የግለሰብ ከዋኞች ላይ ትኩረት ያደረጉ ፎክሎሪስቶች ሴቶች ታላቅ ታሪክ ነጋሪ፣ ወይም ገጣሚያን፣ ወይም ዘማሪያን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ አልቻሉም። እንዲያውም በተቃራኒው ዝነኛ ከዋኞች ሆነው የሚገኙት ሴቶች ናቸው። በሌላ አባባል ከወንዶች እኩል ሴቶችም ለቃላዊ ትውፊቶች ምንጭነታው የሚመሰገኑ ናቸው። (ኔኖላ፤1993፣ 54-55)

ምዕራፍ አራት

በሶዶ ጉራጌ የሴቶች ስርዓተ ፆታዊ ሚና እና ማህበራዊ ደረጃቸው የሚገለፁባቸው ተረኮች ትንተና

በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ የሴትና የወንድ ሚና በዕለተ ተዕለት ክንውናቸው ውስጥ የሚገለፅና የሚታይ ነው። አዳዲስ የማህበሩ አባላት ከነባሮቹ የአኗኗር ዘይቤውን እየተማሩና እየሰለጠኑ እንዲያድጉ ወይም እንዲኖሩ ያደርጋል። በማህበራዊ መዋቅሩ ውስጥም ስርዓተ ፆታ አንዱ የማህበረሰብ ማህበራዊ ደረጃና ሚና የሚሰራበት መንገድ በመሆኑ ‹የወንዶች›ና ‹የሴቶች› የሚባሉ ባህሪያትና ተግባራትን ከልጅነታቸው ጀምሮ ይለማመዳሉ።

ሴት ልጅ በቤት ውስጥ ነፍስ ካወቀችበት ጊዜ አንስቶ የራሷን ቤተሰብ እስክትመሰርት ድረስ ባለው ሂደት ውስጥ ከእሷ የሚጠበቁትን ነገሮች እየተማረች ታድጋለች። በቤተሰቧ ውስጥ ካሉት ሴቶች የሚናዋን መወጣት የሚያስችሉ ክህሎቶችን እያዳበረች እንደምታድግ ተስፋ ገብረየስ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> የጉራጌ ህዝብ ለሴት ልጅ አስተዳደግ የተለየ ትኩረት በመስጠት ገና ከህፃንነትዋ ጀምሮ ወደፊት ለሚጠብቃት ከፍተኛ የቤተሰብ ሃላፊነት የሚረዳትን ሙያና ስነምግባር፣ የዕድሜዋንና የማስተዋል ዕርምጃዋን እየተከተለ ያስተምራታል፤ ያሰለጥናታል። አስር አመት እስከሆነች ድረስ የእናቷንና የታላላቆቿን አሰራር፣ የአነጋገርና የአለባበስ ስልት እየተመለከተች ታድጋለች። የስምንት አመት ልጅ እንደሆነች በጠዋት ተነስታ ፊቷን በማጠብና ልብሷን በአግባቡ በመልበስ የቤት ዕዳት በአግባቡ በመጠበቅ እንዲሁም ለምግብ ዝግጅት የሚሆኑ ዕቃዎችን አውቃ ለእናቷ በማቅረብ ትረዳለች። ለቤተሰቡ ቡና አፍልታ ስነስርዓቱንም ተከትላ ታቀርብና በመጨረሻም ስኒዎችንና ሌሎች የምግብና የመጠጥዕቃዎችን አጥባ በተወሰነላቸው ቦታዎች ታስቀምጣለች። ዕድሜዋ እየጨመረ ሄዶ የአስር አመት በላይ ስትሆን ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያለመመሪያ እራሷን ችላ በተሟላ ሁኔታ እንድታከናውን ይጠበቃል። (አፅንኦት የራሴ) .... ከዚያም ወደአቅመ ሔዋን ለመድረስ ስትቃረብ ለዕዳትዋ አጠባበቅ፣ ለፀጉርዋ አሰራር፣ ለአለባበስዋ ጌጣጌጦችን በማስመልከትም ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ዶቃዎችና ዛጎሎች በተለያየ ፊሊጥ የተሰራ ፀጉርዋን ለማጌጥና በንቅሳትም ውበትዋን ለመጠበቅ የተለየ ትኩረት ታደርጋለች። (ተስፋ፤ 1987፣ 64)

በእነዚህ የሴትነት መመዘኛዎች ውስጥ ገብታ ለማለፍ የቤት ውስጥ ሚናዋን በአግባቡ መወጣት እንዲሁም ከላይ የሚታይ ገፅታዋን ሴት ልጅ ሆና መገኘት እንደሚጠበቅባት

አድርጋ ማቅረብ አለባት። ንፅህና፣ አጊያጊያጥና የመሳሰሉት የምትለካባቸው መስፈርቶች ናቸው።

የሴቶቹን ማህበራዊ ደረጃ በአንድ በኩል በሚተረኩት ተረኮች ውስጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶቹ ራሳቸው በሚሳተፉባቸው ተረኮች ውስጥ ማየት ይቻላል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥም በዝርውም ሆነ በግጥም የተሰበሰቡት ተረኮች በአራት ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ተከፋፍለው የቀረቡ ሲሆን በትረካው ውስጥ ወይም በትረካው ፋይዳ የሴቶቹን ሚናና ደረጃ መረዳት ይቻላል። አንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ የራሱ ብቻ የሆነ የመለያ መስመር ስለሌለው ከሌላኛው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ሊቀላቀል ይችላል። ነገር ግን ዋና ትኩረቱን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸውን ርዕሰ ጉዳዮች አንድ ላይ ለማድረግ የተሞከረ ሲሆን ዝርውና ግጥማዊ ተረኮቹ እንደየርዕሰ ጉዳዩ በመሰባጠር የቀረቡ ናቸው።

4.1. ሴቶችና የቤት ውስጥ ስራዎች

እንደብዙዎቹ የኢትዮጵያ ሴቶች የሶዶ ጉራጌ ሴቶች ቤታቸው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና ቢያገቡም፣ ባያገቡም ከወንዶቹ ሚና ከፍ ያለ ነው። የቤት ውስጥ ስራን ከጠዋት እስከማታ ከመሸፈን አንስቶ የቤተሰቡን አባላት ባልም ይሁን አባት ወንድምም ይሁን ልጅ የማገዝና የመንከባከብ ሃላፊነት ይጣልባቸዋል። እንደማህበረሰቡ የስንፍናና ጉብዝና ብያኔ ሁለቱ ተቃራኒ ሴቶች (ሰነፍና ጎበዝ) የሚገመገሙትና ‹‹ሴት››ነታቸው ዕውቅና የሚሰጠው በቤት ውስጥ በሚያበረክቱት አገልግሎት አይነት፣ ብዛትና አገልግሎቱን በሚሰጡበት ብቃት ጭምር ነው። በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ ባለሙያነት የሚገለፀው በቤት ውስጥ ‹‹የሴት›› ተብለው የተቀመጡ ስራዎች ባህሉ አግባብነት አለው ብሎ ባመነበት መንገድ ማከናወን ሲቻል ነው። የምግብ አዘገጃጀት፣ የልጆች አያያዝ፣ ንፅህና አጠባበቅ እንዲሁም ሌሎች ስራዎች ላይ የምታሳየው ትጋት ከፍ ያለ ሲሆን ባለሙያ ልትባል ትችላለች። ከድርጊታቸው ጋር ተያይዞ ይገባቸዋል የሚባለውን ስያሜ እንዲያገኙ ሴቶቹ አስበውትም ሆነ ሳያስቡት በተሰመረላቸው መስመር ውስጥ ብቻ ለመመላለስ ይገደዳሉ።

የሴቶችን ስንፍና ለማንኳሰስ፣ ጉብዝናቸውን ደግሞ ለማወደስ ሁለቱን ባህሪያት የተጎናፀፉ ሴቶች የተሳሉባቸው ተረኮች አሉ።

ክስታኒኛ

ሰነፍ ምሽት በጌ ባለ
ጥሪ እንጨ በበር ባለ
ብሽ ኤምን ያልፉት ብሽ በጌ ባለ

ትርጉም
ሰነፍ ሴት ከቤት ካለ
እርጥብ እንጨት ከደጅ ካለ
ለቅሶ ለምን ይኬዳል ለቅሶ ቤት ውስጥ ካለ

ክስታኒኛ
ፈያ ምሽት በጌ ባለ
ደረቅ እንጨ በቆጥ ባለ
ፈያ አምብል በጓሯ ባለ
ሸባል ኤምን ያልፉት ሸባል በጌ ባለ

ትርጉም
መልካም ሴት ቤት ውስጥ ካለ
ደረቅ እንጨት ከቆጥ ካለ
ጥሩ ጎመን ከጓሮ ካለ
ሰርግ ለምን ይኬዳል ሰርግ ቤት ውስጥ ካለ

(አቶ ጃማ ገላን፤ ሰኔ 20/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ከሰነፍ ሴት ጋር በአንድ ቤት ውስጥ አብሮ መኖርን ከከፍተኛው የሰው ልጅ ሃዘን ጋር፣ የመልካሟንና ባለሙያዋን ሴት መኖር ደግሞ ከደስታ ቀናት እንደአንዱ እንደሚቆጥሩት በማነፃፀር ይገልፁታል። ስንፍናና ጉብዝናቸው ለቤተሰቡ የዘወትር ደስታና ሀዘን ምክንያት መሆኑ እንዲገባቸው ተደርገው ያደጉና ያንን የሚተገብሩ ሴቶች የመኖራቸውን ያህል ድርጊታቸው የሰው መሳቂያ የሚያደርጋቸውና የሰነፍ ምድብ ውስጥ የሚገቡ ሴቶችም አሉ።

4.1.1 ሴቶች በዘወትራዊ የቤት ውስጥ ስራዎች

ሴትዮዋ በእንሰት ቅጠል አይብ አስራ ቤቷ ምሰሶ ላይ ሰቅላዋለች። በአጋጣሚ የመጡ እንግዶች ቤቷ ጠላ እየጠጡ እያለ ላያቸው ላይ የአይቡ ውሃ ተንጠባጠበባቸው። ይሄኔ ‹‹ይሄ የሚንጠባጠበው ምንድነው›› ብለው ይጠይቋታል ‹‹የአይብ ውሃ ነው›› ብላ መለሰችላቸው ‹‹በምን አስረሽው ነው ውሃው እንዲህ የሚንጠባጠበው?›› ብለው ቢጠይቋት ‹‹በእንሰት

ቅጠል›› ብላ መለሰችላቸው። እነሱም መልሰው ‹‹የአንቺ አይብ፣ ለዚያውም በእንሰት ቅጠል፣ ለዚያውም ምሰሶ ላይ?›› ብለው እርስ በእርሳቸው እየተያዩ ተሳሳቁባት ይባላል።

(አቶ ጃማ ገላን፤ ሰኔ 17/2004 ዓ.ም.፤ቡዲ)

አይብ በሶዶ ጉራጌ ዋነኛ ከሚባሉት የምግብ አይነቶች አንዱ ነው። አስተሳሰሩና የሚታሰርበት ቁስ የሴቷን ስንፍናና ጉብዝና መለካት ያስችላል። አይብ ከወጣ በኋላ ፈሳሹን ለማስወገድና ደረቅ ለማድረግ መታሰር አለበት። የሚታሰረው ደግሞ በዚያ ማበረሰብ በወፍኞ[1] እንጂ በእርጥብ የእንሰት ቅጠል አይደለም። ወይም ደግሞ ይህ ተረክ በተረተረከበት አካባቢ በእንሰት ቅጠል አይታሰርም። የእንሰት ቅጠል እንደ ፕላስቲክ አይነት ስለሆነ ፈሳሹን ማውጣት የሚያስችል ቀዳዳ የለውም። በዚያ አይብ ከታሰረ ቅጠሉን የተለያዩ ቦታዎች ለመበሳሳት አይመችም። በተሰነጠቀበት በየትኛውም ቀዳዳ በኩል ያልፋል እንጂ እንደወንፊት ጥቅቃን ቀዳዳዎች እንዳሉበት ወፍኞ በደንብ የሚያንጠፈጥፍ አይሆንም። ከዚህም አልፎ የታሰረው አይብ ምሰሶ ላይ አይንጠለጠልም። ፈሳሹን መቀበል በሚችል ዕቃ ውስጥ ተደረጎ ላዩ ላይ ድንጋይ ወይም ሌላ ከበድ ያለ ነገር ይጫንበታል። ከተቻለም በመቀት እንዳይበላሽና ቅዝቃዜ እንዲያገኘው ጉድጓድ ነገር ውስጥ ይገባል። ይህ በልማድ አይብ የሚታሰርበት ስርዓት ነው። ምሰሶ ላይ ሲሰቀል የአይቡ ውሃ ወደታች ይፈሳል፤ እሳት የሚነደው ቤት ውስጥ በመሆኑም በመቀት ቶሎ ይበላሻል። እነዚህን ሁሉ ድርጊቶች ተላልፋ በራሷ መንገድ አይብ አስራያለሁ ያለች ሴት ሰነፍ የሚል ስያሜ ይሰጣታል።

ሴቶች በቤታቸው ውስጥ የሚያከናውኑትን የዕለት ተዕለት ስራ በምን መንገድ መስራት እንደሚገባቸው የተለመደ አሰራር አለ። ያንን የሳቱ ደግሞ ለአሽሙርና ስላቅ ይጋለጣሉ። በማህበረሰባቸው ዘንድ ተቀባይነት በሚያሰጠውና ማህበረሰቡ ልክ ነው ብሎ ያመነበትን መንገድ ተከትሎ መሄድ ሁሉም ሴት እንደ ሴት ተቀባይነትን ለማግኘት ወይም ደግሞ በተቃራኒው ማግኘት የሚገባትን ክብር እንድታጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል። እንደሴት ክብር ማጣት ያገባችንም ሆነ ያላገባችን ሴት በማህበራዊ ግንኙነቷ ላይ እክል ሊፈጥርባት

[1] ወፍኞ ከእንሰት ግንድ ላይ ተቀርፎ የሚወጣና ደርቆ ከወጣ በኋላ ለአይብ፣ ለቆጮና ለመሳሰሉት መጠቅለያነት የሚያገለግል ነው።

ይችላል። ይህ እክል እንዳይፈጠር ደግሞ ብዙ ሴቶች የተቻላቸውን ያህል ይጥራሉ። ተከታዩንም ተረክ እንመልከት

> ሴትዮዋ በክረምት ዝናብ እየዘነበባት ኩበት ትለቅማለች። ይህንን በአካባቢዋ የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ሲያልፉ አይተዋት ይገረማሉ። ሴትዮዋም እነዚህ ሁለት ሰዎች እያዩዋት ሲያወሩና ሲስቁ ትመለከታለች። አጠገቧ ሲደርሱም ‹ምን እየተባባላችሁ ነው የምትስቁት?› ብላ ጠየቀቻቸው። እነሱም ‹በዚህ ክረምት ዝናብ እየዘነበብሽ ኩበት ስትሰበስቢ ጊዜ እጅግ ተገርመን እሱን ነው ያወራነው› ይሏታል። ሴትዮዋም በክረምት መስራትዋን እያደነቁ መስሏት ‹የሚገርም እኮ ነው፤ እኔ እንዲህ በዚህ ብርድና ዝናብ እየሰራሁም እኮ ሰነፍ ናት እያሉ ያሙኛል› ስትል መለሰችላቸው።
>
> (አቶ ጃማ ገላን፣ ሰኔ 17/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

የሴት ልጅ እንቅስቃሴና ሃላፊነት የቤት ውስጥ ስራዎችን በመስራት ብቻ የተገደበ አይደለም። በቤት ውስጥ የሚኖራትን ሚና ለመገምገም በማህበረሰቡ ውስጥ ካለው የመዛመድና የእርስ በእርስ ግንኙነት መጥበቁ አንፃር ቀላል ቢሆንም ያንን ግምገማ የምታመልጥበት መንገድ ቢፈጠር እንኳ አደባባይ የምትወጣበትና የምትታይበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። የጉብዝናዋ ብቃት ታዲያ በምታወጣው ጉልበት መጠን ብቻ የሚለካ ላይሆን ይችላል። ምን ብዛት ያለው ኩበት፣ በአየር ሁኔታው እየተሰቃየች መሰብሰቧ ብቻ ሴትዮዋን ጎበዝ አያሰኛትም። ኩበት መሰብሰቢያ የራሱ ጊዜ አለው። በአግባቡ ደርቆ መንደድ የሚችል ኩበት የሚገኘው በበጋ ስለሆነ በአካባቢው ያሉ ሰዎች በክረምት ኩበት አይሰበስቡም። ኩበቱ እርጥብ ሲሆን ከመንደድ ይልቅ ለሴትዮዋም ሆነ ለቤተሰቧም ጠንቅ የሚሆን ጭስ ይሆናል። ምናልባትም ከሌሎች የሚመጣ ድርጊቷን የሚኮንን አስተያየት በቀጥታ አለመምጣቱ የምትሰራው ስራ ስህተት መሆኑን እንዳትረዳ ሊያደርጋት ይችላል። ነገር ግን ሀገሬው የለመደውን አሰራር መንገድ አለመከተሏ (ኩበት በበጋ መለቀሙ የራሱ የሆነ አጥጋቢ ምክንያት ስላለው) ሰነፍ አሰኝቷታል። ‹‹እንዲህም እየሰራሁ ሰነፍ ናት ይሉኛል›› የሚለው ሮሮዋ ሌሎች ስራዎቿም ከማህበረሰቡ የአሰራር ልማድ ያፈነገጡ መሆናቸውን ወይም ሴቶች መድረስ ይገባቸዋል ተብሎ የሚጠበቀው ልክ ላይ መድረስ አለመቻሏን የሚያመለክት ነው። እንድትሰራ የሚጠበቅባትን ሃላፊነት መወጣት በሚገባት ደረጃ አለመወጣቷ አለማወቋን የሚያሳይ ቢሆንም ሚናዋን እንድትወጣ የሚያስችላትን የቤት ውስጥ ሙያ ትዳር እስክምትይዝበትም ሆነ ሚናዋን መወጣት የምትችልበት የዕድሜ ደረጃ ላይ እስክትደርስ ድረስ አለመቻሏ የስንፍናዋ ውጤት እንደሆነ ይታሰባል።

4.1.2 ሴቶች በክብረ በዓላት/መስቀል

በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ ሰነፍቹን የሚጎሽሙና በነገር የሚነካኩ ተረኮች በገዘርውም በግጥምም እንዳሉ ሁሉ ጎበዞቹ ወይም ባለሙያዎቹ የሚወደሱባቸው ተረኮችም አሉ። በተለይ ደግሞ የብዙ ሴቶች ባለሙያነት የሚፈተንበት አጋጣሚ በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ በድምቀት በሚከበረው በመስቀል በአል ወቅት ነው። ይህንን የሴቶች የሙያ ብቃት ወንዶች ብቻም ሳይሆኑ ሴቶች ሴቶችን ጭምር የሚገመግሙበትና የሚመሰክሩበት አንዳንዴ ሴቶቹም ራሳቸው ራሳቸውን የሚያሞግሱበት ነው።

መስቀል ለሶዶ ጉራጌዎች ተራ በዓል አይደለም። ከብዜረሰቡ ማንነትና ህልውና ጋር አጥብቆ የተቆራኘ ነው። በዓሉ ከሃይማኖታዊ ፋይዳው ባሻገር ባህላዊ አንደምታው ሰፋ ያለ ነው። ለሴቶች ደግሞ ሃላፊነቱም ሆነ አጋጣሚው የሚፈጥረው ጉዳይ ትርጉሙን ከፍ ያደርገዋል። ያላገቡት ለትዳር ይታጩ ዘንድ መታያቸው ነው። በዓሉ ባለትዳር ሴቶች በቤታቸው ውስጥ በሚያዘጋጁት ባህላዊ ድግስ ሙያቸውን የሚያስመሰክሩበትና የሴትነታቸውን መስፈርት ማሟላታቸውን ማረጋገጫ ነው። ‹‹የመስቀል በዓል የሴት ታላቅነትና ባልቴትነት የሚታይበት ነው።›› (እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ፣ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም.፣ ቡዒ)

በተለይ ከሴቶች ሙያ ጋር በተያያዘ ከታች የተጠቀምኩባቸውን ግጥማዊ ተረኮች ያገኘሁት ከእማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ ነው። እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ የወረዳውን የሴቶች ጉዳይ ፅ/ቤት መረጃ ሊሰጡኝ ስለሚችሉ ሰዎች ባነጋገርኩበት ወቅት ትልቅ ቦታ ተሰጥቷቸው የተጠቆሙ ሴት ናቸው። እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳን ለማግኘት በቅድሚያ የሄድኩት ወደ መኖሪያ ቤታቸው ነበር። ስለምፈልገው ጉዳይ ስገልፅላቸው እንደሚተባበሩኝ የገለፁልኝ በደስታ ነበር። ተረኮቹን በሚነግሩኝ ወቅት አንዳንዶቹን ነውር ስለሆኑ፣ የባህሉን ምስል ያበላሻሉ የሚሏቸውን አንዳንድ ተረኮች መገለፅ የለባቸውም የሚል አቋም ነበራቸው።





እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ (ቡዲ)

እማሆይ ቦጋለች ስለመስቀል በዓል ሲተረኩ የዝግጅቱን ስፋትና የሚወስደውን ጊዜ በማየት የበዓሉን ታላቅነት ለመረዳት ይቻላል። የዚህ ሰፋ ያለ ጊዜና ዝግጅት አካል የሚሆኑት ሙሉ ለሙሉ ሴቶች ናቸው ማለት ይቻላል። የመዘጋጃ ጊዜዋንም ያጠበበች ሴት ከነቀፌታ አታመልጥም። ለዚህ ደግሞ የድግሷ ውጤት ሲታይ ጉብዝናዋን ለማወደስ፣ ስንፍናዋን ለማንኳሰስ የሚቀርብባት ታላቂ ግጥም ምስክር ነው።

በጣም ሰፊ ዝግጅት አድርጋ ውጤቷ ያማረላትን ሴት

ቅብኪ የግንቦተ
ገባም በጉልበተ
(እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም ቡዲ)

ትርጉም
ቅቤዋ የግንቦት
ገባ ወደጉልበት

ብለው ያሞግሷታል። መስከረም ላይ ለሚከበረው የመስቀል በዓል ባለሙያ ሴት ዝግጅት የምትጀምረው ግንቦት ላይ ነው። ቀድሞ መዘጋጀት ለጉዳዩ ያላት ከበሬታ፣ ስህተት እንዳይፈጠር ያላት ጥንቃቄ ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት የምታዘጋጀው ቅቤ ሆድ የሚሞላ ብቻ አይደለም። አቅምና ሃይል ይሰጣል፣ ጉልበት ያዳብራል።
በአጭር ጊዜ ተዘጋጅታ ያቀረበችውን ደግሞ

ቅብኪ ያምሌ ናሴ
ልብለባው ኤባሴ
ልብዲ ኤላሴ
(እማሆይ ቦጋለች ዱራሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም ቡዲ)

ትርጉም
ቅቤዋ የሐምሌና የነሐሴ
ቃር ነው የተረፈኝ
ልቤን አቃጠለኝ

ዝግጅቱ ጊዜ የወሰደ ቅቤ ጣዕሙ ለይድረስ ይድረስ ከተዘጋጀው ጋር አይወዳደርም። ይህንን ቀምሶ ማረጋገጥ ይቻላል። ለመስቀል ዝግጅት ሴቷ ቅቤ አንጥራ አይብ አስራ ማስቀመጥ ይገባታል። በዓሉን ለመታደም የመጣው ሰው ሊያንሰው አይገባም። ቅቤም ሆነ ቆጮና አይብ ካነሳት ዘፈን ይዘፈንባታል።

ቃይሲሽ ያገዱ የሰኔ ጎርጊሶ
በላትም ፈጀቶት ተባዩሂ ጉንሶ
(እማሆይ ቦጋለች ዱራሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም ቡዲ)

ትርጉም
አይብ ያሰረችው የሰኔ ጊዮርጊስ ነበር
ታዲያ ምን ያደርጋል፣ በልታ ጨረሰችው
ከልጇ ዳቦ ጋር

ምንም እንኳ የሰፋ ዝግጅት ቢኖራት ምንም ያዘጋጀችው ምግብ ጣዕም ባለሙያነቷን የሚያስመሰክር ቢሆን ለመጣው እንግዳ የማይበቃ ከሆነ ከመሰደብ አታመልጥም። ስላነሳት

ወይም ቤቷ ውስጥ ያለው የኑሮ አቅም ምን ይመስላል የሚለው ከግምት ውስጥ አይገባም። ወይም አቅም ጥያቄ እንደጥያቄ አይነሳም። ስህተቱ የእሷ ብቻ ተደርጎ ስለሚታይ ስድቡ እሷን ብቻ የሚመለከት ነው። ያዘጋጀችውን ምግብ በየቀኑ እያወጣች በልታ መጨረስ መዋረዷን የሚያሳይ ነው።

የሰኔዬ አምብል ይነቦት ግበሽ
ልብ ያለኸ ጎሽ አተድርም እገር
በረጋ እም በል ባልረጋ ውል ውል በል
ሰቢ ጥቅጥቅ ይበል ኢንኪ ፍጥጥ ይበል

(እማሆይ ቦጋለች ዱራሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም ቡዲ)

<u>ትርጉም</u>

የሰኔው ጎመን አለበት ነገር
ልብ ያለህ ወንድ ልጅ አሳድረህ እየው
ከረጋ ዝም በል ካልረጋ ዘራፍ በል
ሀገር ተሰብስቦ አይኗ ፍጥጥ ይበል።

በመስቀል ወቅት ሴቶች ባለሙያነታቸውን የሚያረጋጡ ስራዎቻቸውን ውጤት እያዩና እየቀመሱ እርስ በራሳቸው መወዳደስ ወይም ደግሞ መሰዳደብ ብቻ ሳይሆን ወንዱ የሚኖረውን ሚናም ላይ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ፤ ያወድሳሉ ወይም ይነቅፋሉ። በመስቀል ክብረ በዓል ወቅት ከሚበሉት የምግብ አይነቶች አንዱ ክትፎ ነው። ለዚህ መስሪያ የሚሆን ስጋ የሚያስገባው ወይ የሚያርደውና የሚያዘጋጀው ቤት ውስጥ ያለው ወንድ ነው።

በአንድ ወቅት አንድ አባወራ ወደቤቱ ያስገባው ስጋ በጣም ትንሽ ነበር።
ሚስቱ በዚህ በጣም ትናደድና

ደኸ ግበት ወዳኝ ኧዲ ግበት ወዳጅ
ባሞሌሂ በሰር በገሎድ አንትፋጅ

<u>ትርጉም</u>

አንተ ጉበት ወዳጅ እኔ ጉበት ወዳጅ
በአንዲት አሞሌ በተገዛው ስጋ/እንበላለን ብለን/ በቢላ እንዳንፋጅ
በማለት በአሸሙር ተቀበለችው።››

(እማሆይ ቦጋለች ዱራሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም ቡዲ)

በተረኩ ውስጥ ሴትዮዋ የምታነሳው ነገር የእሱ ወይም የእሷ ጉበት አፍቃሪነት ወይም የጉበቱ ትንሽነት አይደለም። የባሏን ስስታምነት መግለፅ ነው የፈለገችው። ገንዘብ ጨመር ቢያደርግበት በመብዛቱ ደስ የምትሰኝበት ስታቀርብም የምትሰስትበት አይሆንም ነበር። ከስጋ ጋር ተያይዞ የሚተረከው ሌላው ተረክ ደግሞ የሚከተለው ነው።

> አንዱ አባ ወራ ደግሞ ጉፋያ የሆነ ስጋ ይዞ ይገባል። ሚስቱ ደግሞ ትንሽ ሰባ ያለ ስጋ ትፈልግ ነበርና
>
> ጭሮደህ እጭነ
> ቅብዲም ነስጭነ
> ንቶናም በጨበር ደናኛ ንኘነ
>
> ትርጉም
>
> ጉፋያህን አኝክ
> ልጠጣ ቅቤዬን
> ፀሐይ ላይ ቁጭ ብለን
> እስኪ ይታይ ወዛችን
> በማለት አበሸቀችው።።

(እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ምንም እንኳ ስጋ እንደልብ በየጊዜው የሚገኝ ስላልሆነ የሚሰጠው ዋጋ ትልቅ ቢሆንም በሚገኝበት ጊዜ የሚገዛው ወይም ታርዶ የሚዘጋጀው ስጋ ጥራት በራሱ የወንዶችን ስጋ ‹‹አዋቂነት›› የሚያሳይ ነው። ጉፋያ ስጋ ከሚገዛ ወንድ እሷ ሴቷ የምታዘጋጀው ቅቤ በእጅጉ እንደሚበልጥና ይህም ደግሞ ከላይኛው ገፅታቸው ላይ ታይቶ የሚመሰከር መሆኑን ነው የምትነግረው። ስጋ መግዛት ከማያውቅ ወንድ ቅቤ ማዘጋጀት የምታውቅ ሴት ትበልጣለች እያለችው ነው።

4.2. ሴቶች እና ትዳር

ሴት ልጅ ከማግባቷ በፊት ሊኖራት የሚገባው ባህሪና ነገሮችን የምትፈፅምበት መንገድ ባህሉ ሴት ልጅ መሆን ይገባታል ብሎ ባመነበት እንዲሆን ትገደዳለች። ከዚያ መንገድ አፈንግጣ ከተገኘች ባህሉን በመገዳደሯ እንደ ‹‹ባለጌ›› ትቆጠራለች። ለትዳር የሚፈልጋት ወንድ አይኖርም። የሚከተለው ተረክ ውስጥ ያለችውን አንዲት ሴት እንመልከት።

ሰውዬው ወንድ ልጁን መዳር ይፈልግና ባለሙያ የሆነች ጥሩ ሴት እንዲፈልግለት ለአንዱ ሰው ያማክረዋል። ሰውዬውም ለትዳር የደረሰች ልጅ እንዳለቸው ይነግረውና መጥቶ እንዲያያት ይጋብዘዋል። ወንድ ልጁን መዳር የፈለገው ሰው ልጅቱን ለማየት በአሳቻ ሰዓት ቤታቸው ሲሄድ አባቷን ያጣዋል። ቤት ውስጥ አባትዬውን እየጠበቀ ሳለ ልጅቱ ቆሎ እየቆላች ነበርና ከምትቆላበት ምጣድ ላይ እየዘገነች ስትበላ ከዚያ ውሃ በጣሳ እያነሳች ስትጠጣ ያያትና በስራዋ አዝኖ

ተንጣጣ ጪልቂመ ተንጣጣ ጪልቂመ
ደኒ ይጋ ድርግመ

<u>ትርጉም</u>

እንደተንጣጣ ጉርስ
የጣሳ ውሃ ድርግም
ያ ያልነው ነገር ተወው ይቅር አልፈልግም

ብለሽ ለአባትሽ ንገሪው የሚል መልዕክት አስቀምጦለት ይሄዳል። አባትየው ከዋለበት ተመልሶ የተቀመጠለትን መልዕክት ሲያገኝ በልጁ ክፉኛ ተበሳጭቶ ‹አሰደብሽኝ› ብሎ ወቀሳት።››

(ቀኛዝማች ጫካ አሰፋ፤ ሰኔ 16/2004 ዓ.ም.፣ ፍርሽና አሮና)

በማህረሰቡ ውስጥ ሰሴት ልጅ በአብዛኛው በባል የመመረጥ እንጂ ባል የመምረጥ ዕድል ስለሌላት በወንድም ሆነ በወንድ ቤተሰብ የምትመረጠው ሴት ቤቷን በአግባቡ መያዝ የምትችል፣ ባለሙያ የሆነች ሴት ናት። ይህ እሷ ላይ ብቻ የሚቆም አይደለም። እንደዚያ ሆና ካልተገኘች ቤተሰቧንም ‹‹ማሰደብ›› ይሆናል። በተለይ እናት ሴት ልጇን በመልካም ስነምግባር የመቅረፅና የማነፅ ሃላፊነት እንዳለባት ስለሚታመን ሴት ልጇ ስትወደስም ስትኮነንም እናት ተጠያቂ ናት። እናቶች ከልጆቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት የመጥበቁ ጉዳይ ተፈጥሯዊ ቢሆንም በተለይ የእናትና ሴት ልጇ ግንኙነት ትውፊታቸውን አጥብቀው በያዙ ህብረተሰቦች ዘንድ እጅግ የጠበቀ ነው። እናቶች የሴት ልጆቻቸውን ‹‹የእናታ ልጅ››ነት ማረጋገጥ ስለሚፈልጉም በራሳቸው ልክ መቅረፅ የተለመደ ነው። ከባህል የማፈንገጥ ነፃነቱ እጅግም የሚያወላዳ ባለመሆኑ ባህሉን ተከትሎ ለመሄድና ለማቆየትም ጭምር ባህሉ ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች ሌላ ምርጫ እንዳለ ማሰብም በራሱ ላይታሰብ ይችላል። የእናትዬው ልምድና ያለፈችበት የህይወት መንገድ ሴት ልጇ እንድታልፍበት የማመቻቸት ሃላፊነት አለባት።

በተረኩ ውስጥ ያለችው ልጅ በማህበረሰቡ ውስጥ ሴት ልጅ ብታደርጋቸው ነውር ናቸው የሚባሉትን ነገሮች ነው ያደረገችው። በባህልና ወጉ ሴት ልጅ የምትመገብበት የራሱ የሆነ ስርዓት አለ። ከዚያ ስታፈነግጥ የምትታይበትና የምትመዘንበት መንገድ ለሌላው ማህበራዊ ህይወቷ እንቅፋት ሊሆንባት ይችላል። ለትዳር የሚፈልጋት አይኖርም። ለባህሏ የተገዛች፣ ሰው ፊት ስትቀርብ በማህበረሰቡ ዘንድ ‹‹ነውር›› የተባሉ ድርጊቶችን የማታደርግ ሴት ናት ለትዳር የምትታጨው። ቆሎ መብላቷና ውሃ መጠጣቷ ድርጊቷን ነውር አያደርገውም። ነገር ግን ከምትቆላበት ምጣድ ላይ እየዘገነች መብላቷ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሴት ልጅ የአመጋገብ ስርዓት ያፈነገጠ ነው። ከቆላች በኋላ በሰሃን አቅርባ ነውር አይሆንም ነበር። ይህን የአመጋገብ ስርዓት የሚስተምረው ደግሞ ቤተሰብ በመሆኑ ያንን አድርጋ ቢሆን ኖሮ ለቤተሰቧም በስርዓትና ወጉ የማሳደጉ ምስክር ነው። ቤተሰብ ‹‹አሰደብሽኝ›› ሲል ስድቡ አንቺ ጋ አያበቃም ማለቱ ነው። የእኔን ማንነትና ህልውና የሚያስነካ ድርጊት ፈፅመሻል፣ ለድርጊትሽ እኔን ተጠያቂ አድርገሽኛል ማለቱ ነው። ይህ ደግሞ በልጆች አስተዳደግ፣ ቤተሰብ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን የሚገልፅ ነው። በቤት ውስጥ ስራ የሚያስመሰግን ሙያ ብቻ ሳይሆን የሚያስመሰግን ባህሪ መገለጫ የሆኑ ድርጊቶች እንድትፈፅም ይጠበቃል። በባህል በተሳሰረና የአንድ ግለሰብም ሆነ ቤተሰብ የአኗኗር ዘዬ በባህሉ የተገዛ ሲሆን ከተሰመረለት መስመር ውጪ ሲያልፍ የባህሉ መሆኑ ይቀራል። የዚያ ባህል አካል መሆን ሲያበቃ ደግሞ በዚያ መስመር ውስጥ ከሚኖረው ሌላው አካል ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከልማዱ ይወጣል። በዚህ መሰረት የሚፈጠረው ስነልቦናዊ ጫና ቀላል አይደለም።

ትዳር መያዝ የማህበረሰቡ አባል ለሆነች ሴት ልጅ አስፈላጊ ከሆኑት የህይወት ደረጃዎች ውስጥ አንዱን እንደመውጣት የሚቆጠር ነው። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ ሴቶችም ሆነ ወንዶች ለአቅመ አዳምና ሔዋን በቅተዋል ብሎ አሻሽሎ የደነገገው እድሜ ለሁለቱም ፆታዎች 18 ዓመት ቢሆንም ከዚያ በፊት ሊዳሩ ወይም ሊታጩ ይችላሉ። በተለይ በቀደመው ባህል። የህጉን መሻሻል ተከትሎ ሁኔታዎች እየተቀየሩ ቢመጡም ማህበረሰቡ ለትዳር የሚሰጠው ዋጋ ከፍ ያለ በመሆኑና አለማግባት በተለይ ለአንዲት ሴት ልጅ ‹‹የሴት››ነት ፈተናን እንደመውደቅ ስለሚቆጠር ትዳር መያዝና ቤተሰብ መመስረት የሴት ልጆች አንዱ ህልም ነው ማለት ይቻላል።

አንድ ሃይለኛና ጦረኛ ሰው ነበር። ዘጠኝ ሚስት አግብቶ ዘጠኙም የልቡ የማይደርሱለት፣ እንዳሻው የማይታዘዙለት ነበሩና ሁሉንም ፈትቶ ወደየቤታቸው አሰናብቷቸዋል። ቆይቶ ቆይቶ አንዲት ሳታገባ አባቷ ቤት የቆየች ልጃገረድ ነበረችና እሷን አይቶ ለጋብቻ ይፈልጋታል። አባቷን ለመለመን ቤታቸው ሲሄድ ያጣዋል። ሲጠብቀው ቆይቶ ሲቀርበት ለእሷ ለራሷ ‹‹ያ ነገር ይሆነኛል...መጥቼ አይቻለሁ›› ብለሽ ለአባትሽ ንገሪ ብሎ መልዕክት ይስቀምጣል። እሷም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ልቧ ይጠረጠርና ለአባቷ መልዕክቱን ትነግራለች። ሰውዬውም ለቤተሰቧም ሽማግሌ ይልካል። አባቷም ከእናቷ ጋር በጉዳዩ ላይ ይመካከራል። ነገር ግን ‹‹ዘጠኝ ሚስት አግብቶ ወደቤታቸው ከሰደደዳቸው በኋላ የእኔን ልጅ ይፈልጋል እንዴ ትንሽ ቆይቶ እንደሌሎቹ ቢመልሳትስ?...አልሰጠውም›› ይላል። ይሄኔ ልጅቱ ታዝንና እንቅብ እየሰፋች እንደሚከተለው አንጎራጎረች።

‹‹እገሌ የባሉየ
የባሉንሽ ቢዬቡየ
የባለንቃይ
ቢቡሽ ምን ይብሉዬ
ኳሽ ምን ይብሉዬ››

<u>ትርጉም</u>


እከሌ ለተባለው
ያለውን/የጠየቀውን ቢሰጡትስ
ካልሰጡት እሱስ ምን ይለኛል?

አባቷ ይህን ሲሰማ ለልጅቱ ያዝንና ‹‹በቃ ያልከውን እሰጥሃለሁ›› ብሎ ለሰውዬው መልዕክተኛ ላከበትና ተጋቡ። ከተጋቡ በኋላ እንደልቡ መሆን የምትችል መሆኗን ለማረጋገጥ ሊፈትናት ፈለገ። መጀመሪያ ራቁትሽን ምንም ሳትለብሽ ጋያ አቀጣጥለሽ አደባባይ ሸንጎ ላይ ድረሺ አላት። ለአሽከሮቹ ለእሷ ሳትነግሯት አደባባይ ራቁቷን ከመጣች ልብስ አልብሷት አላቸው። እሷም ወደሸንጎው ራቁቷን ለመግባት ስትዘጋጅ አሽከሮቹ ልብስ አለበሷትና ገባች።
በሌላ ጊዜ ‹ማሰሮዬ ስጋ እንዳያጣ፣ እንግዳ ሲመጣብኝ፣ አሽከሮቼ ስጋ እንዳያጡ ነገር ግን ቤቴ ውስጥ አንድም ነገር እንዳይታረድ፤ ምግብ አዘጋጅተሽ ጠብቂኝ› ብሏት ሄደ። አሽከሮቹን ጠርታ በጎቹን አምጡልኝ ብላ የሁሉንም በጎች ላት እየሰነጠቀች አወጣችና ሰራች። ሲመጣ ስጋ አለ፣ በጎቹን ሲያይ አልታረዱም። የተሰጧትን ፈተናዎች ባልዋ በሚፈልገው መንገድ በማለፏ ‹‹በቃ ይህች ሴት ትክክለኛ ሚስቴ ናት›› ብሎ በሰላም አብሯት መኖር ጀመረ።››

(ቀኛዝማች ጫካ አሰፋ፣ ሰኔ 16/2004 ዓ.ም. ፍርሽና አሮና)

ምንም እንኳን ሴቶች ከሚያገቡት ሰው ጋር ተመካክሮ የመወሰን ባህል እየተለመደ ቢሆንም አሁን ድረስ የቤተሰብ ፈቃደኝነት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። የልጃቸውን ባል

መምረጥ፣ ካልሆነ ደግሞ ቢያንስ እሷ የመረጠችውን የማፅደቅ ሃላፊነት ውስጥ ደግሞ ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረው አባትዬው ነው። የእናትዬውን ሚና በተረኩ ውስጥ አናየውም። በልጆች ህይወት ውስጥ የመወሰን ከፍተኛ ሚና ያላቸው ምናልባት ብቸኞቹ ወሳኞች አባቶች ናቸው። ስለአባቶቹ የመወሰን ሚና ከፍተኛነት ስናነሳ እናትዬው የሚኖራት ሚና ሴት ልጇን ለትዳር የምትሆን አድርጎ ቀርፆ ማሳደግና ዝግጁ ማድረግ ነው።



ቀኛዝማች ጫካ አሰፋ (ፍርሽና አሮና ቀበሌ)

በላይኛው ተረክ ውስጥ የምንመለከተው ልጅቱ ሳታገባ መቆየቷ የፈጠረባት አሉታዊ ተፅዕኖ ነው። ቤተሰብ መመስረት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውንና እያንዳንዷ ሴት እንደየእድሜዋ እንድትወጣቸው የሚፈለጉትን ደረጃዎች እንደወጣች ማረጋገጫ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች እድሜዋ የሚፈቅደውን ያህል የተቀመጡላትን ደረጃዎች መውጣት ካልቻለች የመገለል ዕጣ ይደርስባታል። ፈቅዳና አምናበት ካላደረገችው ደግሞ የማህበረሰቡን ጫና መቋቋም ለአንዲት ሴት ከባድ ይሆንባታል። የመመረጥ እንጂ የመምረጥ መብቱ ብዙ ስለማይኖራት ለትዳር የሚጠይቃትን ሰው መጠበቅ ይኖርባታል። ጠያቂውን ሰው መውደድ አለመውደዷን የሚጠይቃት ሰው የለም። አባትዬው የጠያቂውን መጥፎ የሚለውን ገፅታ እያነሳ ለመከልከል ሲያንገራግር እንኳ እሷም ሆነች እናቷ ሃሳብ የመስጠት ዕድል

አልነበራቸውም። ስለዚህ ልጅት ብሶቷን በእንጉርጉሮ ነበር ስትገልፅ የነበረው፣ ለብቻዋ። ምክንያቱም ትዳር አለመያዟና ከዚህ ቀደም ለትዳር የጠየቃት ሰው አለመኖሩ፣ አሊያም ጠይቆ እንዲሁ መከልከሉ፣ ከሴቶች እኩዮቿ የበታች የመሆን ስሜት ፈጥሮባታል። ስለዚህ የምትፈልገው፣ የምትመርጠው ሰው ባይሆን እንኳ፣ ባል እስከሆነ ድረስ ማንም ሆነ ማን እሷን ለትዳር ጠይቆ የመጣን ወንድ ተቀብላ ‹‹የሴት ወግ እንዲደርሳት›› ነው የፈለገችው። ትዳሩ ከተመሰረተ በኋላ ደግሞ ትዳሩን ለማፅናት ምን ያህል ራሷን ለመስጠት እንደፈቀደችና እንደጣረችም እናያለን። ይህ ደግሞ የባሏን ፍላጎት እያሟላች፣ ጥያቄዎቹን እየመለሰች በመኖር ላይ የተመሰረተ ነው።

ሰናይት ተሰማንና ሌሎች ሴቶችን ያገኘኋቸው በሶዶ ወረዳ ደጋ ኑረና ቀበሌ ውስጥ ነው። ሰናይት በግምት ሰላሳ አመቷ ሲሆን የተዳረችው ከአስራ ሁለት ዓመታት በፊት ነው። ቡድን ተኮር ውይይቱን ካካሄዱ በኋላ ሴቶቹ ኡሳቻ[2] ለመሄድ እየተዘጋጁ ነበር። ስላገባችበት ሁኔታ ስጠይቃት የሚከተለውን ብላ ነበር።

> ላገባ ስል ባሌን አላውቀውም ነበር። ሽማግሌም ሲላክ እኔን የጠየቀኝ ማንም አልነበረም። ቤተሰቦቼ ወደው ፈቅደው ከሰጡ በኋላ እኔ ምንም ማድረግ ስለማልችል አገባሁ። ከተጋባን በኋላ ግን ለቤታችን እኩል እንሰራለን። ቤት ውስጥ አንዳንደ ነገሮች ስንወስን በጋራ ነው። እሱም ለብቻው እኔም ለብቻዬ ፍላጎቴን ብቻ ተከትዬ ያለእሱ ፈቃድ የማደርገው ነገር የለም።
>
> (ወ/ሮ ሰናይት ተሰማ፤ ግንቦት 9/2004 ዓ.ም. ኑረና)

ምንም እንኳ ጋብቻ ያለተጋቢዎች ፈቃድ መፈፀም እንደማይገባው ቢያውቁም እነሱ ባገቡበት መንገድ ሴት ልጆቻውን የሚድሩ ወላጆች አሉ። ለዚህ እንደምሳሌ የምትነሳው ወ/ሮ ሃይማኖት አልዬ ናት። ወ/ሮ ሃይማኖት ሴት ልጇን በመጪው ሚያዚያ ትድራለች። ልጇን ለመዳር የሙሽራው ወላጆች እሷንና ባለቤቷን ለምነዋቸዋል። ምንም እንኳ እሷ ያለችበትን ትዳር ‹‹ወላጆቼ የማይሆን ትዳር ውስጥ ነው የከተቱኝ›› ብትልም ልጇም በተመሳሳይ መንገድ እንድትሄድ እየፈቀደች ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቷ ‹‹የልጅ ወላጆች በልመና አላስቀምጥ አሉኝ›› ነው። ይህ ምስክርነት ያለተጋቢዎች ፈቃድ በተለይም ደግሞ

[2] ‘ኡሳቻ’ ሴቶች በቡድን ሆነው እንሰት የሚፍቁበት ስነሰርዓት ነው።

ያለ ሴቷ ፈቃድ በወላጆች ፈቃደኝነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ትዳር እንደነበርና አሁንም እንዳለ ነው።

ከትዳር ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ የወንዶች ከአንድ በላይ ሴት የማግባት ጉዳይ ነው። ምንም እንኳ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በህግ የተከለከለ ቢሆንም ወንዶቹ ከአንድ በላይ ሴት የማግባታቸው ልማድ አሁንም ድረስ አለ። በተለያዩ ምክንያቶች ሌላ ሴት ያገባሉ። «የገጠር ቤት ንብረቱን እንድትጠብቅለት ሊያገባት ይችላል፤ አባትና እናቱን እንድትጦርና እንድታገለግልለት የሚያገባትም አለች።....››› (እማሆይ ገኔ መግራ፤ ሚያዚያ 24፣ ቡዲ)። አብዛኞቹ ሴቶች ሌላ ሚስት እያለው እንደሚያገባቸው ወይም እነሱ እያሉ ሌላ ሚስት ሊያገባ መሆኑን ሊያውቁ ይችላሉ።

ቀደም ባለው ጊዜ በባልና በሚስት መካከል ግጭት ሲፈጠር ሴቶች ወደ ወላጆቻቸው ቤት ከተመለሱ ቤተሰብ በተለይ አባት መልሶ ያመጣታል እንጂ ባልዋ ይቅርታ ለመጠየቅ አይመጣም። ንብረት የመካፈልም ሆነ የመውረስ መብት ስላልነበራት በባልዋም ሆነ በቤተሰቧ ላይ ይሄ ነው የሚባል ስልጣን አልነበራትም። ይህ የሚፈጥረው ስሜት የበታች እንደሆኑ አምነው እንዲቀበሉና ወንዶቹ (ባል፣ አባት) የሚሏቸውን አሜን ብለው ለመቀበል ይገደዳሉ። ይህንን የማይቀበሉና ስሜታቸውን በአመፅ የሚገልፁ ሴቶች ግን በጭራሽ አልነበሩም ማለት አይደለም። የ80 ዓመቷ ወ/ሮ አለምነሽ በያን ተወልደው ያደጉት ቡታጀራ አካባቢ ነው። የተዳሩትም በ15 ዓመታቸው ነበር። ትዳር ስለያዙበት አጋጣሚና በትዳራቸው ውስጥ ስላጋጠሟቸው ሁኔታዎች እንደሚከተለው አጫውተውኝ ነበር።

> ባለቤቴን ካገባሁት በኋላ ወርቅ ሊያመጣ አዶላ የሚባል ቦታ ሲሄድ ብቻዬን ቤት እጠብቅ ነበር። ባለቤቴን ስለማልወደው እዚያ ብዙ ሰዎች ሞቱ ሲባል ምነው አንዱ እሱ በሆነ ብዬ እመኝ ነበር። ከሆነ ጊዜ በኋላ መጣና እንደገና ተመልሶ ሲሄድ ቤቱ ከሌለ የምጠብቀው አይኖርም፤ እኔም ወላጆቼ ጋር እመለሳለሁ ብዬ በማሰብ ቤቱን አቃጠልኩት። ከዚያም በኋላ በጣም ስለጠላሁት አንዲፈታኝ አስለምኜ በግድ ዘመዶቼ አስገድደውት በመጨረሻ ተፋታን፣ ስንፋታ ልብስም አላለበሰኝ ነበር። በኋላ አንድ ባለመሳሪያ ጀግና ነበርና እሱን አገባሁ። ከእሱ ጋር እየኖርኩ ልጆች ከወለድኩና ደክሜ ሰፍቼ አንድ ቤት በደጋ አንድ ቤት ደግሞ በቆላ ካሰራሁ በኋላ ሌላ ሚስት ሊያገባብኝ ሆነ። እኔ ሳላውቅ ከጎተራ በቆሎ አውጥቶ፣ ያረባሁትን በግ ነድቶ በመሸጥ ለእሷ ልብስ አሰፍቶ ሄደና በዚያው አደረ። ፈረስ፣ አዲስ ጥይት ገዝቶ መጣ...እኔ ሌባ ገድሎት ነው ብዬ ስሰቃይ አደርኩ። እሱ

ጠዋት አዳዲስ ነገር ይዞ መጣ። ከዚያ ከእኔ በፊት ያገባት ሚስቱ ቤተሰብ ጋር ለለቅሶ ሲሄድ እቃዎቹን ያስቀመጠበት ቦታ አዳዲስ ነገር አገኘሁ። ከዚያ ውስጡ ያለውን አዲስ ሽቶ፣ አዳዲስ ጥይት አግኝቼ እየተጠመቀ ያለ የጠላ "አተላ ውስጥ ከተትኩት። ሰው ሁሉ አንቺ ብትከለክዪው መቼም ማግባቱ አይቀርም እያለ ሲመክረኝ ጋኑን ትርክክ አድርጌ ስሰብረው ፀሐዩ ላይ ፍስስ አለ። ከዚያ ቤት ውስጥ ያሉትን እቃዎች እንዳለ ሰባበርኩት። ከእዚያ በቃ ንዴት ሊለቀኝ አለቻለም። አጎቴን እባክህ መሳሪ ስጠኝና ልግደለው እኔ ሌላ ባል ባገባ እንኳ ድካሜና ልፋቴ አይረሳኝም ብዬ ሳስቸግር ሁሉም ለልጅሽ ብለሽ እያለ ሲመክረኝ ተውኩት።....በኋላም ታርቀን እሱ በሰራሁት በአንዱ ቤት ውስጥ መኖር ጀመረ እኔም በሌላኛው ቤት እንደ ቤት ጠባቂ ሆኜ መኖር ጀመርኩ።››

(ወ/ሮ አለምነሽ በያን፣ ነሐሴ 4፣ 2004 ዓ.ም.፣ ቡሂ)

ትዳር በመመስረት ሆነ ባላቸውን በመፍታት ሂደት ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሴቶች መወሰን የማይችሉ እንደነበርና አሁንም ይህ ሁኔታ እንዳለ በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረዳት ችያለሁ። ከላይ የተገለጸው ታሪክ ባለቤት በትዳራቸው ውስጥ የሚፈጠሩትን የስሜት አለመመቸት፣ የፍላጎት አለመሟላትና ሌሎች ውጣ ውረዶች የሚፈጥሩባቸው ተፅዕኖዎች ከተቋቋሙበትና አሜን ብለው እንዲቀበሉ ካደረጓቸው ጉዳዮች አንዱ እናት መሆናቸው ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ እናቶች ከልጆቻው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እጅግ የቀረበ በመሆኑ ብዙ ሴቶች ማህበራዊ ጫናዎችን ለመቋቋም ወይም በማይመቻቸው ትዳር ውስጥም ቢሆን ለመቆየታቸው ለራሳቸው ይቅርታ ለማድረግ ይጠቀሙበታል። ከአፍሪካና ውመኒስት መገለጫዎችም አንዱ ይህ የእናትነት ጉዳይ ነው። እናትነት በማህበረሰባዊ ግንኙነትና በስርዓተ ፆታዊ ሚናዎች አማካይነት የሚያድግ ቢሆንም መሰረቱ ተፈጥሯዊ ግንኙነት በመሆኑ ይህን ሃላፊነት የሚወጡት የሚሰጣቸውን ሚና ለመወጣት ብቻ አይደለም። የመውደድና የመወደድ ሰብዓዊ ስሜታቸውን ለመወጣትም ጭምር ነው። ለዚህ ደግሞ በትዳር ውስጥ የሚፈጠርን አለመግባባት ይቋቋሙበታል።

ይሁንና ብዙዎቹ እንደተስማሙበት በማህበረ-ፖለቲካዊ ለውጦች ምክንያት አንዲት ትዳር የምትመሰርት ሴት ባሏን ቀድማ የማወቅ፣ ወይም የምታውቀውን ሰው የማግባት ሁኔታ እየተለመደ መጥቷል።

4.3. ሴቶችና ምግብ

ስርዓተ ፆታ የህብረተሰብን ታሪክ፣ ርዕዮተዓለም፣ የኢኮኖሚ ስርዓትና የፖለቲካ መዋቅራቸው ውስጥ እንደሚሰራው ሁሉ በምግብ ነክ ጉዳዮች ላይም ይሰራል። አመጋገብ በብዙ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ አንድ የባህል መገለጫ ይታያል። የማህብረሰቡ አባላት እንደየዕድሜ ደረጃቸው፣ እንደየፆታቸውና እንደየ ማህበረሰባዊ ደረጃቸው የሚመገቡት ነገርና የሚመገቡበት መንገድ ይለያያል። የአመጋገብ ስርዓቱን ሳያዛቡ ይዞ መቆየት ደግሞ ማህበራዊ ደረጃቸውን ከሚያስጠብቁባቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው። ምግብ ከመሰረታዊ የሰው ልጆች ፍላጎት አንዱ በመሆኑ ከየዕለት ህይወት ውስጥ የማይነጠል ነው። ይህም በመሆኑ ተደጋግሞ የሚከወን ስርዓት እንዲኖረው ያደርጋል። ይህንን ስርዓት ደግሞ በቀላሉ ማፍረስ አይቻልም።

አርለን ቮስኪ አቫኪአን እና ባርባራ ሃበር በአርታኢነት ባሳተሙትና ምግብ ከሴቶች ጋር ስላለው ግንኙነት የሚገልፁ ፅሁፎች ስብስብ በያዘው From Betty Crocker to Feminist Food Studies: Critical Perspectives on Woman and Food (2005) የተሰኘ መፅሀፍ መግቢያ ውስጥ ምግብን ማዕከል ያደረጉና በማህበረሰባዊ ህይወት ውስጥ ስላለው ሚና የሚገልፁ ፅሁፎችን በዋቢነት አንስተዋል። ከእነዚህም ውስጥ ምግብ በቤተሰብ ውስጥ ያለው ትርጓሜና ሴቶችን ከዚህ ትርጓሜ ጋር በማያያዝ ለቤተሰብ ህይወት መሰረት መሆናቸውን የምትገልፀው የስነሰብ ተማራማሪዋ የማርዮሪ ዴቫውልት ስራ አንዱ ነው። ዴቫውልት Feedig the Family: The Social Organization of Caring Work (1991) በሚለው መጽሐፏ በምግብ ስርዓት አማካኝነት ስርዓተ ፆታና ቤተሰባዊ ህይወት እንደሚሰራና የምግብ ዝግጅት አንድን ቤተሰብ የሚበይን መሆኑንና በዚህም ሴቶች የአንድን ቤተሰብ ህልውና መፍጠር እንደሚችሉ ትገልፃለች።ይህ ቤተሰብን የመመገብ ሂደት ቤተሰብን መስራት ቢችልም እንኳ እንደ‹ስራ› እንደማይታይና ሴቶችም ራሳቸው ብዙ ጊዜ እንደስራ እንደማይቆጥሩት ታስረዳለች። (አቫኪያን እና ሃበር፤2005፤9-10)

ሌላው በዚህ ስራ ውስጥ የተጠቀሰው የካሮል ኮኒሃን "Female Identity food and power in contemporary Florence" የተሰኘው ስራ ነው። ኮኒሃን በዚህ ስራዋ ውስጥ እንደምትገልፀው ምግብ ሴቶች ለተፅዕኖ መፍጠሪያነት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው።

(ኮኒሃን፤ 1988፣53) ከዚህም በተጨማሪ የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት በእጃቸው እንዳለና መቆጣጠር እንደሚችሉት ስልጣን እንደሚጠቀሙበትም "Women every- where .... feed their husbands and children in return for love, favors, good behavior, and the power that comes from being needed." (ኮኒሃን፤ 1988፣53) በማለት ትገልፃለች።

በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ ሴቶች ከቤተሰባቸው ጋር እያሉም ሆነ ትዳር ከመሰረቱ በኋላ ከወንዶች የትዳር አጋራቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ከሚወስኑ ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ምግብ ነው። ለማዕድ የሚሰጠው ዋጋ ብቻ ሳይሆን የማዕዱ አጠቃቀም ላይ በባልና በሚስት መካከል የሚኖረውን የደረጃ ልዩነት ያሳያል። ሴቶች በትዳር ውስጥ ከባላቸው ጋር ሲኖሩ በዕለት ከዕለት የቤት ውስጥ ስራዎች፣ ሁለቱም በሚኖራቸው ባህሪያትና በመሳሰሉት ሊጋጩ ይችላሉ። ይህ በባልም ሆነ በሚስት በኩል ሲታይ በባህሉ የተሰጣቸውን ስርዓተ ፆታዊ ሚና ለማፍረስ ሲሞክሩ የሚፈጠር ነው።

> ሰውዬው ተጨቃጫቂ ነው። ሁልጊዜ ከሚስቱ ጋር የሚገላግልና የሚያስታርቅ ሽማግሌ መሀከላቸው ሽማግሌ ይገባል። አንድ ቀን አምሾ (እንደድንች ተቀቅሎ የሚበላ የእንሰት ስር) ለመቀቀል ወደ ማሰሮ ውስጥ ስታስገባ እሷ ሳታየው እየቆጠረ ነበር። ሰባት አምሾ ቆጠረ። ተቀቅሎ ከማሰሮው ሲዘረገፍ ግን ስድስት አምሾ ነበር የወጣው። ለካ ሚስትዬው መብሰል አለመብሰሉን ለማረጋገጥ አንዱን በልታው ነበር። ያኔ ታዲያ አሁንም ቢናገር ሽማግሌ ይመጣብኛል ብሎ ስለፈራ
>
> ባወረሩም መካ ባላውረሩም መካ
> በሰባቲ መካ አቲ ይቲ ፈካ?
>
> <u>ትርጉም</u>
>
> ከተናገሩም ችግር ባይናገሩም ችግር ነው
> ከሰባቱ አምሾ አንዱ የት ሄዶ ነው?
> ብሏት ወጣ።››
>
> (እማሆይ ገኔ መግራ፤ ሰኔ 1/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ቀደም ሲል ባየናቸው ተረኮች ውስጥ ምግብ የማዘጋጀትን ሃላፊነት ሙሉ ለሙሉ የሚወስዱት ሴቶች ናቸው ማለት ይቻላል። ማጀት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚገባ ወንድ በወንዶችም ሆነ በሴቶች ዘንድ አይደነቅም። ከፍ ያለ ባለሙያነት ከሚገለፁባቸው መንገዶችም አንዱ ይኸው ምግብ የማዘጋጀት ሂደት ነው። የሙያን ጥግ ማሳያ አንዱ

መንገድ ቢሆንም በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ባለው ዘወትራዊ የማጀት ስራቸው የሙያቸው ተቋዳሾች ለወንዶች ናቸው ማለት ይቻላል። ሴቶቹ ተጨንቀው የማዘጋጀታቸውን ያህል መመገቡ ላይ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅ ያለና ከወንዶቹ ጋር የማይመጣጠን ነው።

የብዙ ተረኮችን ባህሪ ስንመለከት በባህሉ ውስጥ የተለመዱና ዘወትራዊ ተግባራት ለብቻቸው አይተረኩም። ከባህሉ ያፈነገጡትን ወይም ባልተለመደ መልኩ የሚካሄዱትን ከተለመዱት ጋር ማነፃፀር እንዲቻል በተረክ መልክ ይቀመጣሉ። ይህም ነውር ነው የሚባለውን እንዳይደረግ ለማስተማር ነው። በዚህ ተረክ ውስጥ በባህሉ የወንድ ልጅ አስተዋፅኦና ግድ የሚለው ጉዳይ የሚኖረው ከጓዳ ውጪ እንደሆነ ይታመናል። ምግብ ማዘጋጀትን የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ስራዎች የሚተዉት ለሴቷ ነው። ወንድየው የሚሰዙ ስራ ውስጥ መግባት ከዚያም አልፎ ቁጭ ብሎ የምትሰራውን ስራ ለመከታተልና ለመቆጣጠር መሞከር ወንድነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚከት ጉዳይ ነው። ‹‹የሴት›› እና ‹‹የወንድ›› የሚሉት መለያዎች የሚፈጠሩት ሚናቸውን በአግባቡ ለይተው መወጣት የሚያስችል መስመር ለማስመር ነው።

> ባልና ሚስት ሲኖሩ በሳምንት በአንደኛው የገበያ ቀን ወደ ገበያ ስትሄድ የጓዳ ቁሳቁስ የምትሸምተበትን ገንዘብ የሚሰጣት ባልዬው ነው። ታዲያ በአንደኛው ቀን እንደተለመደው ወደ ገበያ ልትሄድ ስትነሳ ገንዘብ ትጠይቀዋለች። እሱም ‹‹ለቡና ነው?›› ብሎ ሲጠይቃት ‹አይደለም› ብላ ትመልስለታለች። ‹‹ለጨው ነው ወይስ ለበርበሬ?›› ብሎ ይጠይቃታል። አሁንም ‹‹አይደለም›› ብላ ከመለሰችለት በኋላ አያይዛ ‹‹ቃይሳ ልዋጅቦ›› (አይብ ልገዛበት) ስትለው ‹‹በሻችቦ›› (ካወቅሽበት) አላት ይባላል።
>
> (ወ/ሮ ገኔ መግራ፣ ሰኔ 1/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ይህ ተረት በሁለት መንገድ ይታያል። ጥሩ አይብ ለመግዛት አለመቆየቱን በመቅመስ ወይም በማሽተት ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ ደግሞ አሰራሩም ላይ የሴቷን ሙያ የሚጠይቅ ነው። ምግብ ሲሰራ ዋነኛ የሆነው የማመጣጠን ችሎታ እዚህም ጋ ይጠየቃል። የቅቤ፣ የጨው፣ የሚ ጥሚጣና የሌሎች ቅ መማቅመሞች አገባ ብ ወይም ተ ቀላቅለው

የሚቀርቡ የምግብ አይነቶች አሰራር ለባልየው ጥያቄ ሆኖበታል። ‹‹ካወቅሽበት›› ሲላትም አገዛዙንም አሰራሩንም የምትችይ ከሆነ ማለቱ ነው ብሎ መተርጎም ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰውዬውን ሆዳምነት ይገልፃል። ገበያ ወጥቶ መገበያየትን (ገንዘብ የሚሰጣትም ባልየው በመሆኑ) ዋጋ የሚያሰጠው እንደጨውና ቡና አይነት ተጨማሪ ነገሮች ሳይሆኑ አንጀት ጠብ የሚሉ እንደ አይብ ያሉ ዋና ምግቦችን (አይብ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅና ታላቅ ምግብ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልፆአል።) መምረጡን ለመግለፅ ነው።



በብዙዎች ደጃፍ የሚገኘውና ቆጮ የሚገኝበት የእንሰት ተክል (ደጋ ኑረና)

ቀደም ባለው ዘመን በቤት ውስጥ ባለትዳር ሴት ለባሏ ያላትን ክብር ከምትገልፅባቸው መንገዶች አንዱ ለአባወራው የምታዘጋጀው ምግብ ለሌሎችም ሆነ ለራሷ ከሚዘጋጀው የተሻለ አድርጎ በማቅረብ ነው። ሁለቱ በአንድ ማዕድ ቢቀርቡም እንኳ የሚመገቡት ምግብ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ከተለመደው ስርዓት የሚያወጣ ተግባር አባወራውን የሚያስቆጣው ሊሆን ይችላል።

> አንዲ ባለትዳር ሴት በአንድ ወቅት ለባሏ ቆንጆ አይብና ቆጮ አዘጋጅታ ለእሷ ደግሞ ለእሱ ተዘጋጅቶ ያደረውን አምጥታ እንደነገሩ የተዘጋጀ ጎመን አጠገቡ አድርጋ ትበላለች። ያደረውን ቆጮ ስትበላ ያያትና
>
> ኧዲም ዳቦ ደሽም ዳቦ
> ትዳርኛ አልሻንቦ
>
> ትርጉም

እኔም ዳቦ በላሁ ዳቦ በላሽ አንቺም
ይህን ትዳራችን አላወቅንበትም

ይላታል። በኋላ ለእሱ ቆንጆ ቆጮ በሌላ በኩል ደግሞ መጥፎውንና ብዙ ጊዜ ለመብል የማይሆነውን ጋግራ በአንድ ማዕድ ላይ ግማሽ ግማሹን አድርጋ ስታቀርብ

ደሽም ስትቅን ኧዲም ስትቅን
አዳርኛ ገናም ቅጥን

ትርጉም

አንቺም ግማሽ እኔም ግማሽ
አስተዳደራችን ገና አሁን እኩል ሆነ አላት።
(እማሆይ ቦጋለች ዱራሳ፤ ሚያዚያ 30/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

የባለትዳሮቹ ዋነኛ ጉዳይ የምግብ ማነስ ወይም መቸገር አለይደለም።ወንድ መብለጡንና ከእሷ መሻሉን፣ እሷ ደግሞ ከፍ ያለውን የእሱን ደረጃ መቀበሏን ለመግለፅ የሚጠቀመበት የደረጃ መለያ ነው። እሱ የበላውን እኩል መመገብ ከ‹‹መመገብ›› ያለፈ ትርጉም ይኖረዋል። ባል በቤት ውስጥ ያለውን የበላይነትና የሚገባውን ክብር መቀናቀን ነው። ይህን ማድረግ ትዳርን ያህል ተቋም የመነቅነቅ አቅም አለው። በመሆኑም ‹‹አላወቅንበትም›› ሲል አንቺም የሚገባሽን ያህል ሚስት እኔም የሚገባኝን ያህል ባል አልሆንኩም ማለቱ ነው። ባልነቱ እና ሚስትነቷ ልክ መሆናቸው የሚረጋገጠው እሱ ከእሷ የተሻለ ወይም ደግሞ እሷ ከእሱ ጋር የማይስተካከል ምግብ መመገብ ሲችሉ ብቻ ነው።

ሰውዬው ስጋ በጣም ይወዳል ግን ያ ስራ ተሰርቶ ለሰውዬው ነው እንጂ ሚስትዬው አብራ ቀርባ አትበላም። ሌላ ምግብ አብራው ብትበላም ስጋ ሲሆን ግን አብራው አትበላም። ሰው ቤት ስትሄድም ምንም እንዳትበላ አስጠንቅቋታል። አንድ ቀን ምሳ ልታዘጋጅ ስትፈልግ ክብሪት ታጣለች። ከዚያ ከጎረቤት ለመዋስ ስትሄድ ባልና ሚስት ምሳ እየበሉ ትደርሳለች። ከዚያ ነይ ብዪ ብለው ይጋብዟታል። ባሏ አንቺ ስጋ ከበላሽ እሞታለሁ ብሏት ስለነበር እሱ ከሚሞት እኔ ስጋ ባልበላ ይሻላል ብላ የነገራትን አምና ስጋ መብላት ትታለች። ታዲያ ጎረቤቶቿ እንድትበላ ሲጋብዟት “እኔ አልበላም” ትላለች። ‹‹ለምን?›› ብለው ሲጠይቋት ‹‹እንዴ ስጋ እኮ ሴት ልጅ ከበላች ባል ይሞታል አሉ። አንቺ እንዴት ቁጭ ብለሽ ስጋ ትበያለሽ?›› ብላ ባለቤትዬዋን መልሳ ትጠይቃታለች። ‹‹ማን ነው እንደሱ ያለሽ?›› ብለው ሲጠይቋት ‹‹ባለቤቴ›› ትላለች። ‹‹እስቲ እሱ ዛሬ ይመት እንኪ ብዪ›› ብለው ይሰጧታል። እሷም በልታ ጠጥታ ወደ ቤቷ ልትመለስ ስትል ‹‹አሁን ስትገቢ አብረሽ ከሱ ጋር ማንኪያሽን ይዘሽ ብዪ›› ብለው ይመክሯታል። እሷም ምግቧን አዘጋጅታ ልትበላ ስትል ‹‹ምን ልትሆኚ

ነው?›› ብሎ ይጠይቃታል። እሷም ‹‹ምሳ ልበላ ነው›› ትለዋለች። እሱም ‹‹ሌላ ቀን በልተሽ የማታውቂውን እንዴት ዛሬ ከእኔ ጋ ቀርበሽ ስጋ ትበያለሽ?›› ይላታል። እሷም ‹‹አይ ዛሬማ እበላለሁ›› ትለዋለች። ‹‹አረ እኔ እሞትብሻለሁ?!›› ይላታል። ‹‹ሙት ከፈለክ›› ትለዋለች። እየበሉ እያለ እንደሞተ ሰው ይወድቃል። እሷም ‹‹ተነስተህ ትበላ እንደሆን ብላ በኋላ ጮኬ ሰ ው እሰበ ስባለሁ›› ስትለው ‹‹ ስጋውን መብላት ትተ ያለሽ?›› ይላታል። ‹‹አልተውም›› ትላለች። ከዛ በቃ አንደሞተ ሲሆን እሷ ጮኸችና ጎረቤት ተሰበሰበ። ከዚያ ቢሉት ቢሰሩት እንደሞተ ሰው ሆነ። ሳጥን ገዝተው አመጡና ሳጥን ውስጥ ከተቱት። ቀስ ብሎ ‹‹ትሌጊን?›› (ትተይዋለሽ)ሲላት ‹‹ተለጋ!›› (አልተውም) ትለዋለች። ከዚያ በዚህ ሁኔታ እሱም ሳይነሳ እሷም ሳትተው ሰውዬው ከእነነብሱ ተቀበረ ይባላል።

(ወ/ሮ ሃይማኖት አልዬ፣ ግንቦት 7/2004.ም. ደጋ ኑረና)

ስጋ ከፍተኛ ፕሮቲን ያለው ሲሆን በሰውነት ግንባታ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ከዚህም በተጨማሪ ስጋ በገጠሩ ማህበረሰብ ዘንድ በቀላሉ የሚገኝና ዘወትራዊ ምግብ አይደለም። እንደ ዓመታዊ ሃይማኖታዊ በዓል፣ ሰርግ፣ ተዝካር ባሉ የተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ ካልሆነ በቀላሉ አይገኝም። በተረኩ ውስጥ ስጋ የሚወደውን ሰው ስጋውን ለብቻው የመመገብ ስስት ከማየት በስተጀርባ እሷ እንዳትበላ የፈለገበትን ምክንያት የተሻለውን ከመመገብና ከዚያ ጋር ተያይዘው ከሚመጡት የአቅም፣ የጥንካሬ፣ እንዲሁም ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ወንዶች ከሚሰጣቸው ደረጃ ጋር አብሮ ሊነሳ ይችላል። ሰውዬው ሚስቱ ስጋ ስትበላ ከማየት ይልቅ ሞት ተሽሎ የተሰማው ሚስቱ ከእሱ እኩል ስጋ መብላሏ ከደረጃው ዝቅ ብሎ የመኖር ያህልና ከዚህ ደግሞ ሞት የተሻለ ክብር መስሎ ስለተሰማው ነው።

ሰውዬው ከሚስቱ ጋር ምግብ ለመብላት እንደተዘጋጁ ውሃ እንድታመጣለት ይጠይቃታል። ርቧት ስለነበር ልትነሳ ስትል ከቆጮው አንድ ግዜ ገምጣለት ውሃ ለማምጣት ትነሳለች። ይሄኔ ባልየው የገመጠችለትን ቆጮ በጣቱ ሲለካው ትልቅ ይሆናል። ከዚያም ‹‹ እንዲህ ከምትበላ ሴት ጋር ነው አብሬ የምኖረው ማለት ነው›› ብሎ ይበሳጭና ወደ ቤተሰቦቿ ሊመልሳት ይወስናል። ከዚያም በይ ተነሽ ቤተሰቦችሽ ጋ እንሂድ ይላታል። በዚህ ጊዜ ሆዷ ይጠረጥርና ይከፋታል። ከዚያ መንገድ ላይ እያሉ አንዲት ላም ሳር ስትገጥ ያገኛሉ። በዚህ ጊዜ ሚስትዬው ‹‹ውይ ይህቺ ላም እንዴት ነው የምትበላው እስኪ እንያት ትለዋች›› ለምን ሲላት ልክ እንደራበው ሰው ነውየምትበላው ሰውም መጀመሪያ ሲበላ እንዲህ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ይበርድለታል። አለችው። በዚህ ጊዜ እሱም ለካ ቅድም ርቦሽ ነው እንዲህ የበላሽው እኔ እኮ ሁልጊዜ እንዲህ የምትበይ መስሎን ቤተሰቦችሽ ጋ ልመልስሽ ነበር። በይ አሁን ወደቤታችን እንመለስ። አላትና ወደቤታቸው ተመለሱ።

(ወ/ሮ ዘነበች አሻሚ፤ ነሐሴ 15 /2004.ም.፤ አይመለል)

የምግብ መጠን ለሴትነት መስፈሪያነት ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ ነው። የምትበላው የምግብ መጠን የሚነግፀረውም ሁልጊዜ ከወንዶች ጋር ነው። የመጠኑ መብዛት እሷን ‹ሆዳም› የሚያሰኛት ቢሆን እንኳ ተመጣጣኝ መጠን ያለው ምግብ ለወንዱ እንደ ትንሽ ሊታይ ይችላል። የወንድነት መገለጫ የሆኑትን ጥንካሬ፣ የጡንቻ መፈርጠምና የመሳሰሉትን ከሚያጎለብቱ ነገሮች አንዱና ዋነኛው የአመጋገብ ሁኔታ ነው። አካላዊ አቅምና ጥንካሬ ደግሞ ስነልቦናዊ ጥንካሬን ከሚፈጠርባቸው መንገዶች አንዱ ነው። የወንዶች አካላዊ ጥንካሬ ከሴቶች መብለጥ አለበት የሚል ማህበረሰባዊ አቋም የሴቶች አቅም ከወንዶች አቅም ማነስ አለበት የሚለው ማህበራዊ አቋም አካል ነው። ‹‹አቅመ ቢስ››ን ወንድ እንደወንድ ለመቀበል የሚችገሩት ወንዶቹ ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም ጭምር ናቸው። ምክንያቱም ከወንድነት ጋር ተያይዞ የሚመጣው ስዕል ጥንካሬም ጭምር ስለሆነ ነው።

በመሆኑም ሴቶች ለባላቸው የተሻለውንና የበለጠውን የመስጠት ጉዳይ ወንዶች የተሻለውን ከመፈለጋቸው አኳያ ብቻ አይታይም። ሴቶችም ራሳቸው ለማህበራዊው አቋም የተገዛ ባል፣ አባት፣ ወንድም፣ ወንድ ልጅ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። ሴቶቹም የሚያወድሱትና ከፍ ከፍ የሚያደርጉት ወንድ ‹‹ለወንዶች›› የተባሉና አካላዊ ጥንካሬ ለሚጠይቁ ስራዎች ብቁ ሆኖ የሚገኝን ጎበዝ ገበሬ፣ ጠንካራና ሚስቱን የሚያኮራ ባል፣ ልጆቹን የሚያስከብር አባት ነው። ሴቶች የሚሰጣቸው ሚና እንዳለ ሁሉ ወንድም የሚቀበለው ማህበራዊ ግዴታ ወንድ አለ። ይንን ግዴታ ለመፈፀም ደግሞ አካላዊ ብቃት ያስፈልገዋል። አካላዊ ብቃቱን ለመገንባት ደግሞ የምግብ ሚና ከፍ ያለ ነው። በመሆኑም ሴቶች ማህበራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስችላቸውን ለማሟላት ያግዟቸዋል። በሁለቱ (በወንዶችና ሴቶች አቅም) መካከል ያለውን ልዩነት ጠብቆ ለማቆየት ወንዶች መብለጥ ያለባቸውን ያህል ሴቶች በአቅም አንሰው መገኘት አለባቸው።

4.4. ሴቶች በአደባባይ

የሴቶች ሚና በበቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከማጀት ወጣ ብለው በራሳቸው መንገድ በማህበረሰባቸው ማህበረ- ኢኮኖሚያዊ ሂደት ውስጥ አበረክታለሁ የሚሉት አስተዋፅኦ

አላቸው። ይህ አስተዋፅኦዋቸው በአብዛኛው ወንዶችን ከመደገፍ አኳያ የሚታይ ቢሆንምና ከወንዶች ጋር የመወዳደር ፍላጎት ባያሳዩም ወይም ተወዳዳሪ ሆነው ራሳቸውን ባይገምቱም ለቤታቸውና ለትዳራቸው እኩል መብትና ሃላፊነት እንዳለባቸው የሚያምኑ ሴቶች አሉ። ሴቶች ከቤት ውጪ የሚኖራቸውን ሚና ለሁለት በመክፈል ማየት ይቻላል። አንደኛው የትግል አጋርነት ሚናቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኢኮኖሚያቸውን ለመደገፍ የሚያደርጉት ጥረት ነው።

4.4.1 ሴቶችና የወንዶች አጋርነታቸው

የጉብዝናና የጀግነት ፅንሰሐሳብ በአብዛኛው ከወንዶች ጋር ሲያያዝ ቤቱን በአግባቡ የሚመራ፣ በገጠሩ አካባቢ ከሆነ ጥሩ አርሶ አደር፣ እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታ የሚፈጠርን የጋራ ጠላት መመከት የሚችል ነው። ጀግንነት ከሚፈተንባቸው አጋጣሚዎች አንዱ ግጭት ነው። ግጭቱ በአንድ ነገር ላይ ተመሳሳይ ሐሳብ ባላቸው ወይም ተቃራኒ ፍላጎት ባላቸው ሁለት አካላት መካከል የሚፈጠር ሊሆን ይችላል። መሰረቱ የጥቅም፣ የክብር፣ የይገባኛልና የመሳሰሉት ሊሆን ይችላል። በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ጎረቤቶች፣ ጎሳዎች ግጭት መፈጠሩ አዲስ ነገር አይደለም። ሶዶዎች ከጉራጌዎች ጋር ተጣምረው ‹‹ሶዶ ጉራጌ›› የሚለውን ስያሜ ከማግኘታቸው በፊት በመካከላቸው በተደጋጋሚ ግጭት ይፈጠር እንደነበር ታሪካዊ ዳራቸው ያስረዳል። በእርስ በእርስ ግንኙነት ውስጥ የሚፈጠር የጎሳ ግጭት ወይም ደግሞ እነዚህ ጎሳዎች ራሳቸው የጋራ የሚሉት ጠላት ሲኖራቸው ወንዶችም ሴቶችም ስርዓተ ያታዊ ስርዓቱ በሚፈቅድላቸው መጠን በጋራ ይከላከላሉ። አንዳንድ ጊዜ ‹‹የወንድ›› የሚባለውን የመሸፈት ሐሳብ የሚተገብሩና ስርዓቱን አፍርሰው የሚገኙ ሴቶች ይኖራሉ። ምናልባት በቁጥር ስለማይወዳደሩ ሊሆን ይችላል እንደወንዶቹ ብዙ አይወራላቸውም እንጂ ጣሊያን ኢትዮጵያ ውስጥ ለአምስት አመታት በተቀመጠበት ጊዜ በሽፍትነት ሃገራቸውን ያገለገሉና ጠላትን ሲቃወሙ የነበሩ ሴት ሽፍቶችና አርበኞች በታሪክ እንደነበሩ የሚናገሩ የማህበረሰቡ አባላት አሉ። ለምሳሌ በቡዒ ያገኘኋቸው አለቃ አበራ ደሞ በልጅነት ዘመናቸው ጣሊያን ኢትዮጵያ ውስጥ ጊዜያት ውስጥ የሚያስታውሷትን ሴት ታሪክ እንደሚከተለው ነግረውኛል።

ዘነበች የምትባል አንዲት ሴት ሀገራችን በተወረረች ጊዜ ከወንዶች ጋር አልሸፍትም ብላ ሌሎች 15 ሴቶች ይዛ ሸፍታ ነበር። ለደኃች በቀለ ወያም ጠላት የት እንደደረሰ እየተከታተሉ ይልኩ ነበር። ሃይለስላሴ ወደ ሀገር ሲመለሱ እነዚህን 15 ሴቶች ይዛ በመሄድ ተሸልማለች። ስለሴቶች ብዙም ስለማይወራ ብዙ አልተነገረላትም።

(አለቃ አበራ ደሞ፣ ሰኔ 20/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ሴቶች በቀጥታ ትግሉ ላይ ተሳትፎ ባያደርጉም እንኳ (ጦርነት ላይ ዘምተው መሳሪያ ይዘው ባይዋጉም) በጦርነት ወቅት አስፈላጊና መሰረታዊ የሆነውን የወኔ መቀስቀስና የማበረታታት ስራ ይሰራሉ። ሂዩድሰን ዊምስ እንደምትለው ከአፍሪካና ዎማኒስት መገለጫዎችአንዱ ወንዶች ለሚያደርጉ ትግል አጋር ሆኖ መቅረብ ነው። (Hudsen-weems: 1993) ትግሉ በማንነታቸው ላይ ከመጣ ውጪያዊ አካል ጋር ከሆነ ያንን በተለያዩ መንገዶች በመደገፍ አብረው መሆናቸውን ያሳያሉ። በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ የቤት ውስጥ ሃላፊነትን ከመሸከምና ማጀትን ከመቆጣጠር ባሻገር ሴቶች በአደባባይ ከሚኖራቸው ሚና አንዱ የወንዶችን ወኔ የሚቀሰቅሱ ግጥሞችን በመግጠምና በመዝፈን መግለፅ ነው። ይሁንና ከትግሉ በኋላ በሚገኘው ውጤት ዕውቅና የሚሰጠው በአብዛኛው ለወንዱ ነው።

በትግል አጋርነታቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚነሱት ሴቶች አንዷ ‹‹ቤቴ›› የምትባል ሴት ናት። ቤቴ በማህበረሰቡ ዘንድ በሁለት መልኩ ትገለፃለች። ለድርጊቷ የሚሰጠው ትርጓሜ አንድ አይነትና ወጥ አይደለም። ገሚሶቹ ጀግንነቷንና ለወንዶች የልብ ልብ ሰጥቶ ማነሳሳት የሚያስችል የግጥምና የቃላት አጠቃቀም ብቃት ያላት ሴት እንደነበረች ሲገልፁ ይህች ሴት ከወንዶች ጋር እየዋለች ማበረታቻ ዘፈኖች የምትዘፍንላቸው ነበረች። ወገኖቿን በተቃርኖ የሚመለከቱ ሌሎች ወገኖች ሲመጡ ወይ ሊመጡ ሲሉ ዘራፍ እያለች እየነካካቸው፣ እያበረታታች ስትዘፍንና ስታቅራራ ትውላለች ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ሰዎችን ከሰዎች፣ ጎሳን ከጎሳ ማጋጨት እንጂ ያን ያህል የረባ ፋይዳ አልነበራትም ሲሉ አሉታዊ አስተያየት ይሰነዝራሉ። ይህች ሴት አደረገች ከሚባሉት ወኔ ማነሳሻ አጋጣሚዎች አንዱ የሚከተለው ነው።

> አንዲት ቤቴ የምትባል ሴት ነበረች። ከወንዶች ጋር አብራ እየሄደች ትዘፍናለች፣ ዘራፍ ትላለች። የጎሳ ጥል ሲፈጠር ወይ ሁለት የማይዋደዱ አካላት ሲኖሩ እየተከታተለች አንደኛውን ለጥል ታነሳሳለች። በአንድ ወቅት ኦሮሞና ክስታኔ ተጣልተው ነበር አሉ። ገላን ኢመቶ የተባለው ጦረኛ ሰው

ከዱላ ጎሳ (የኦሮሞ ጎሳ ነው) ሚዜ ነበርና መልስ ተጠርቶ ሲበላ ዋጮዎች (የክስታኔ ጎሳ ነው) መጣ። ቤቱ እዚያ መልሱ ቦታ ነበረችና የገላን ኢመቶ መምጣት አናዷታል። እንደመደፈርም ስለቆጠረችው የዋጮን ጎበዛዝት ለማነሳሳት

ዋጮ ምን መላነ
ኢመቶ ገላነ
ዝምን ጓሮአነ
ገባም ዳቢያነ

<u>ትርጉም</u>

ዋጮ ምን ይሻላል
ገላን ኢመቶ ይሽው ከጓሮአችን

ብላ ስትዘፍን ገላን ኢመቶ ፈረሱን ጫነና የተጠራበትን መልስ ሳይበላ ጥሎ ወደ መጣበት ተመለሰ።

(አዝማች ግዛው ወ/ሰንበት፤ ሰኔ 17/2004 ዓ.ም.፣ አናቲ)

ይህ ተረክ ቦታው እየተቀያየረ ዋናው ታሪክ ግን ብዙም ሳይቀየር በተለያየ ቦታ ይተረካል።

በአንድ ወቅት በታሪክ የኦሮሞና የጉራጌ ጎሳ ግጭት ላይ በነበሩበት ወቅት አንደኛው ሁለት ሰዎች አይዋደዱም። አንደኛው ጉራጌ አገር መልስ ሊበላ መጣ። ሲመጣ ማንም አላወቀውም ቦታው ዘጌ ገቾ የሚባል የጉራጌዎች አካባቢ ነው። ቤቱ ደግሞ ይህ ሰው ከየት እንደመጣ ታውቅ ነበርና

ገቼ ምን መላነ
ኢመቶ ገላነ ወረደም ዋራነ
ዎባም አዘባነ ገባም ደገማነ

<u>ትርጉም</u>

ገቼ ምን ይሻላል ምን እንዘይድ
ኢመቶ ገላን በእንሰት በኩል አድርጎ
ሳሉናችን (እልፍኛች) ገብቷል።

ብላ ስትዘፍን አንደኛው የገቾ ሰው ፈረሱንና ጦሩን ጭኖ ኢመቶ ገላንን ማሳደድ ጀመረ።››

(እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ፤ ሰኔ 19/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ቤቱ ወኔ ለመቀስቀስ የምትዘፍንና የምትገጥመውን ያህል ስነፋንና ፈሪውንም ከመገለፍ ወደ ኋላ እንደማትል ይነገርላታል።

ቤቴ በአንድ ወቅት ሁለት የክስታኔ ጎሳዎች የኦሮሞዎን ጎሳ ለመዋጋት ወደ ጢያ ይሄዳሉ፡ በዚህ ወቅት አንድ የኦሪያ ጌታ የተባለ ሰው በጣም ይፈራል። ይሄኔ ፍርሃቱን ለመግለፅ የሚከተለውን ግጥም ገጥማበታለች።

የኦሪያን ጌታ
የተፋን አሞታ
ሰባትን ገበታ

<u>ትርጉም</u>

የኦሪያ ጌታ
የተፋው ሀሞት
ሰባት ገበቴ ነው
(አዝማች ግዛው ወ/ስንበት፣ ሰኔ 17/2005 ዓ.ም.፣ አናቲ)

ሀሞተ መራራነት፣ የኮስታራነት፣ የጀግንነት ምልክት ነው። ሀሞት የሌለው ወንድ እንደፈሪ ነው የሚቆጠረው። የኦሪያን ጌታ ‹‹ሐሞት የመትፋቱ›› ዘይቤያዊ አገላለፅ ውስጡ የሚቀር ጀግንነት አለመኖሩንና ፈሪነቱ ልክ እንደሌለው የሚያሳይ እንጂ በቀጥታ የሚተረጎም አይደቤቴለም። በማህበረሰቡ ውስጥ ሲሰጣት የነበረውን ቦታ ተስፋ ገብረየስ በ<u>አይመለል (1987)</u> መፅሀፋቸው ‹‹የቀድሞ ጀግኖች፣ ብልሆችና ሀብታሞች መታሰቢያ›› በሚል ርዕስ ስር ባስቀመጧቸው ግጥሞች ውስጥ የቤቴን ስም አንስተው የሚከተለውን አስፍረዋል።

ጀግና ታጠባብቅም ሰነፍ ትመክረ
የመሌ ትሰድብም ጀግና ታከብረ
የቤቲኛ ጀብዱ ቲየውዱም ቲፈጁ ይዝጌርን ታምረ
ቤቴ ጀግናና ና የጀግናና ውረ
(ተስፋ፤ 1987፣ 179)

<u>ትርጉም</u>

ጀግና ታበረታለች ሰነፍ ትመክራለች
ፈሪ ትሰድባለች ጀግና ታከብራለች
የቤቴን ጀብዱ አውርተው አያልቅም የእግዜር ታምር ነው
ቤቴ ወንድ ናት የጀግኖች አውራ።

ወንዶች በሴቶች ዘንድ መሞገሳቸውና መንኳሰሳቸው የሚሰጠው ዋጋ ትንሽ አይደለም። ወይ የሚያኮራ ወይም ደግሞ በሀፍረት አንገት የሚስደፋ ነው። በአንድ ወቅት ሀይለማሪያም ቦቤ ለሚባል አንድ ጦረኛ ላቅ ካለ ጥፋት ምን ያህል እንዳዳናቸው ለመግለፅ ኣንዲት ሴት አንዲህ ስትል ገጠመች።

የቦቤ ሽብርብር የዙሪያ ቅምጥል
ደኽሽ ባትነብር የጠፋአይ ኤላአ
ባሎጦምም በደብር
ባልገቦም ተግብር
(እማሆይ በጋለች ዱሬሳ፤ ሰኔ 19/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ትርጉም

የቀዬው ተወዳጅ የቦቤ ሽቅርቅር
አንተ ባትኖር ኖሮ ብዙ ይጠፋ ነበር
ከጫካም ባልወጣን
ንብረትም ይዘን ወደቤት ባልገባን

በአንድ ውጊያ ውስጥ ለተሳተፉ ሁለት ተሰማዎች አያይዛ የገጠመችም ሴት ነበረች። ተሰማ ጫሜ በጀግንነት ተዋግቶ ድል ነስቶ ሲመለስ በጉብዝናው አንጀቷን በማራሱ፣ ተሰማ ኢላ ደግሞ ሳይዋጋ ሸሽቶ በመምጣቱ በፈሪነቱ አንጀቷን በማብገኑ የሚከተሉትን ግጥሞች ገጠመችላቸው ይባላል

የጫሜዲ ቀጭን
በዋጋ ቅብ ይኖ አንጨርርም ስጭን
ኧዚ ጎዲን ይኖ አተርርም ኧጭን
ተሰማን ኢላ የሸሺ የቁጭን
(እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ፤ ሰኔ 19/2004 ዓ.ም.፣ ቡዲ)

ትርጉም

የጫሜ ሽንቃጣ
በማሰሮ ቅቤ አለ አንጠፍጥፈህ ጠጣ
ጎድንም አለልህ ጠብሰህ ነጭተህ ብላ
የሸሸው ይቆጨው ያ ተሰማ ኢላ

በጦርነት ወይም በሁለት ጎራ ተከፍሎ በሚኖር አካላዊ ውጊያን ወይም የአርበኝነትና የጦረኝነት ስሜት በሚያስፈልጉባቸው አውዶች ውስጥ ሴቶች የሚኖራቸው ሚና ለወንዶቹ አጋርነታቸውን ማሳየትና መግለፅ ነው። ከመግለጫ መንገዶቻቸው አንዱ ደግሞ ኪናዊ ብቃታቸውን ማሳየት በሚችሉበት ግጥሞቻቸው ነው። እነዚህ ግጥሞች ቃላዊ ስለሆኑ አውዳቸው እየተቀያየረ በአንድ ወቅት ማወደሻ ከነበሩ በሌላ አውድ ለሚፈጠሩ ለሌሎች ጀግኖች ማወደሻ፣ ስድቦቹም ፈሪዎችን ማኮሰሻ ሆነው ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።


4.4.2 ሴቶች፣ የቤት ውስጥ አስተዳደርና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦዋቸው

እንደብዙዎቹ አባዊ ስርዓት ገዢ በሆነባቸው ማህረበሰቦች በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ ቤቱን የማስተዳደር ሐላፊነት የአባወራው እንደሆነ ይታመናል። ‹‹የቤቱ አባት›› የሚባለው ባል ወይም አባት በቤቱ ውስጥ በሚደረጉ ማንኛውም ጉዳዮች ላይ ይሁንታው የመስጠትም ሆነ የመከልከል ስልጣን አለው። ይህ በቤት ውስጥ ያሉ የቤተሰቡን መሰረታዊ ፍላጎቶች የማሟላት ሃላፊነትንም ይጨምራል። ይሁንና ቤትን ‹‹ማስተዳደር›› ከላይ እንደሚታየው ብቻ ወንዶች የሚፈፅሙት ስራ ብቻ አይደለም። ሴቶችም ከወንዶች ያልተናነሰ ሚና እንዳላቸው በሁለት ነገሮች ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው ሴት የሌለችበት ቤተሰብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ባል ወይም አባወራ የሌለበን ቤት ነው። ሴት የሌለበት ቤተሰብ ሴት ካለችበት ቤተሰብ ጋር ሲወዳደር ህይወትን ለመምራት አስቸጋሪ ይሆናል። ወደቤት የሚመጣው ጥሬ ነገር ብቻውን ምግብ ሆኖ አይመጣም። ወንዶች የሴቶቹን ስራ የመስራት ችሎታም ሆነ ፍላጎት አይኖራቸውም። ምክንያቱም እንደሴት መታየት የሚፈልግ ወንድ የለምና። በዘመናዊው አለም እየደበዘዘ የመጣው የስርዓተ ፆታሚና በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ እንደደመቀ ይገኛል። በመሆኑም ስርዓተ ፆታዊ ህልውናውን ማስከበር የሚፈልግ ወንድ ሴት የምትሰራውን ስራ ለመስራት አይደፍርም። በመሆኑም ብዙዎቹ ሌላ ሚስት ያገባሉ። ሚስት ማግባት ፆታዊ ፍላጎትን የማሟላት ጉዳይ ብቻ አይሆንም። ቤተሰብን በመምራት ሂደት ውስጥ የሴቶች አለመኖር የሚፈጥረው ሰፊ ቀዳዳ ስላለና ያንን ቀዳዳ የምትደፍን ሴት አጋር አስፈላጊ ስለሆነች ነው።

በተቃራኒው ደግሞ ከየተለያዩ ወይም ባላቸውን በሞት ያጡ ሴቶች ህይወታቸው ችግር አይገጥመውም ማለት ባይቻልም ሌላ ባል ሳያገቡ ልጆቻቸውን ማሳደግ የሚያስችል አቅም ኖሯቸው ያንን ሐላፊነት በአግባቡ መወጣት ሲችሉ ይታያሉ። ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ለማዳበር የተለያዩ መነገዶችን በመፈለግ ቤት የማስተዳደር ሐላፊነታቸውን የሚወጡ አሉ።

ኑረና ውስጥ ባካሄድኩት ቡድን ተኮር ውይይት ውስጥ ከተሳተፉት ተወያዮች አንዷ ወ/ሮ ጂቱ ሜጫ ናት። ጂቱ ባለቤቷ ከሞተ አስራ አምስት አመት ይሆነዋል። እሱ ሲሞት ከተጋቡ አስር አመት ያህል ይሆን ነበር። በዚህ ወቅት ሶስት ልጆች የወለደች ሲሆን ልጆቿን ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶችን ታደርግ እንደነበር ትገልፃለች። ‹‹አሳቻ እሄዳለሁ፣

እሰፋለሁ....በቃ ወጥቼ ወርጄ ልጆቼን አሳደኩ..አሁን ደርሰውልኛል::›› (ወ/ሮ ጂቱ ሜጫ፤ ግንቦት 9/2004.ም. ደጋ ኑረና) በማለት ልጆቿን አባትም እናትም ሆና እንዳሳደገችና የባለቤቷ አለመኖር በእሷም በልጆቿም ላይ የፈጠረውን ጫና ለመቋቋም ጥረት ማድረጓንና ይህ ጥረቷ አሁን ፍሬ ማፍራቱን ትገልፃለች::



የቡድን ተኮር ውይይት ተሳታፊዎች በከፊል-ኑረና

ቀደም ሲል ሴቶች ወንዶች አርሰው ያመጡትን አዘጋጅቶ ከማቅረብ ያለፈ ሚና ያላቸው የማይመስለው አስተሳሰብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተቀየረ እንደመጣ ብዙዎቹ ያምናሉ:: በሶዶ ጉራጌዎች ዘንድ ሴቶች በአብዛኛው የቤት ውስጥ የገንዘብ አቅም ለመደጎም፣ አንዳንዴ ደግሞ በአጠቃላይ ቤተሰብ ለማስተዳደር ትንንሽ ቢሆንም በንግድ ይሳተፋሉ:: የሚሰሯቸውን ሰፊድ ሰፍቶ ገበያ በመውሰድ፣ በጋራ ሆነው እንስት በመፋቅ (ኡሳቻ) የሚያገኙትን ገቢ ቤተሰብ ያስተዳድሩበታል:: ቀደም ሲል የነበረው ከአንድ ሚስት በላይ የማግባት ልማድ ለወንዶቹ ባለመቅረቱ ባላቸው ሲሞት ልጆቻቸውን የማሳደግ ሙሉ ሃላፊነት የሚጣልባቸው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ የአንድ ባል ሚስቶች በአብዘኛው በቅድሚያ የሚሳተፉበት ስራ ጥቃቅን ንግድ ነው:: ባል ያላቸውም ቢሆኑ በዚህ ረገድ ከባሎቻቸው እኩል ትግል እያደረጉ እደሆኑና እንዲያውም እነሱ የበለጠ መስዋዕትነት እየከፈሉ እንደሆኑ የሚያምኑ አሉ::

> ነግጂ ቤቴን አስተዳድራለሁ። ለኑሮ ሁለታችንም እየታገልን እንኖራለን። በእግር ከኑረና ተነስተን አጨበር ሮብ ገበያ ለመድረስ አራት ሰዓት ይፈጅብናል። ለመምጣትም አራት ሰዓት ይፈጃል። እዚህ አካባቢ ሴቶች ፈረስ አንጠቀምም፣ ወንዶቹ ናቸው በፈረስ የሚሄዱት፣ ወደላይ ወደ አጨበር ያሉት ሴቶች ግን ፈረስ ይጠቀማሉ። አዚህ ስላልተለመደ በእግራችን ነው የምንሄደው።
>
> (ወ/ሮ ሃይማኖት አልዬ፣ ግንቦት 9/2004.ም. ደጋ ኑረና)

ብዙ ጊዜ በንግድ ውስጥ የሚሳተፉት ወንዶች ናቸው። ነገር ግን ሴቶቹም በራሳቸው አቅም ማድረግ የሚችሉት በመስራት የቤቱን ወጪዎች ለመሸፈን፣ የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላትም ጭምር ጥረት ያደርጋሉ። አብዛኞቹ ቤት ውስጥ ፈትለውና ሰፍተው ወደገበያ በመውጣት ይሸጣሉ። በዚህም ቤት ውስጥ የጎደለ ነገር ካለ ይሞሉበታል። ባል የሞተባቸውና ቤተሰባቸውን ለብቻቸው የሚመሩ ሴቶችም እንዲሁ ድካሙን ለብቻቸው ነው የሚሸከሙት።

ብዙዎቹ ሴቶች የወንዶች የሃይል በላይነት እንዳለ ቢያምኑም የትዳር አጋሮቻቸው ያለእነሱ ፈቃድና የሚፈፅሙት የጋራ ጉዳይ አለመኖሩንና በቤት ውስጥ በልጆቻቸው ጉዳይ፣ በቤት ንብረት መሸጥና መለወጥ ላይ ውሳኔ የመስጠትን ሃላፊነት እንደሚጋሩ የገለፁ ተወያዮች ነበሩ።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ውስጥ በሶዶ ጉራጌዎች የሚነገሩ ተረኮችን በመሰብሰብ ተረኮቹ ስለሴቶቹ ስርዓተ ፆታዊ ሚና እና ደረጃ የሚገልፁበት መንገድ ተመርምሮዋል። ይህንንም ለማወቅ የተለያዩ ዝርውም ሆኑ ግጥማዊ ተረኮች የተሰበሰቡ ሲሆን እነዚህን ተረኮች በዋናነት በሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች መሰረትነት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ታይተዋል።

የመጀመሪያው ዋና ክፍል ሴቶችን ከቤት ውስጥ ስራዎች ጋር አያይዘው የሚመለከቱ ተረኮች የተቃኙበት ነው። ሴቶች ከሚኖራቸው ማህበራዊና ስርዓተ ፆታዊ ሚናዎች አንዱ የማጀት ስራ ቢሆንም ይህ ሚና ተቀባይነት የሚኖረው እንደብዙዎቹ ባህሎች በማህበረሰቡ የባለሙያነት መስፈር ተለክቶ ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሴቶች በትዳር ውስጥ ከትዳር አጋራቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚዳስስ ነው። ማህበረሰቡ ለትዳር የሚሰጠውን ቦታና ማግባት ወይም አለማግባት በሴቶች ላይ የሚፈጥረውን ስነልቦናዊ ተፅዕኖ እንዲሁም የዚህ ተፅዕኖ ውጤት በትዳር ውስጥ የሚፈጥረውን መልካምም ይሁን መልካም ያልሆነ አጋጣሚ ያሳየ ነው። በሶስተኛው ክፍል ደግሞ ሴቶችና ምግብን በተመለከተ የተተረኩ ተረኮች የቀረቡበት ነው። ምግብ የሰው ልጆችን ተፈጥሯዊ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ማህበራዊ ደረጃና ስርዓተ ፆታዊ ሚናን መለያ ሆኖ እንደሚያገለግል ተረኮቹ ያሳያሉ። በአራተኛው ክፍል ሴቶች ከቤት ውጪ በሚኖራቸው ማህበራዊ ተሳትፎ አማካይነት በአንድ በኩል የጋራ ጠላት ሲመጣባቸው ወኔ በመቀስቀስና በማበረታታት፣ በሌላ በኩል ከቤት ውጪ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የቤት ውስጥ አስተዳደር ላይ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበት መንገድ ተመልክቷል።

ከላይ የተነሱት ዋና ዋና ነጥቦች በተነሱባቸው ተረኮች ትንታኔ ውስጥ የሚከተሉት ጉዳዮች ጎልተው ወጥተው ተገኝተዋል።

ከተረኮቹና ከትንታኔዎቹ መረዳት እንደሚቻለው የወንዶች ተፅዕኖ ፈጣሪነት በጉልህ የሚታይ ጉዳይ ቢሆንም ሴቶቹ ሚናቸውን አሜን ብሎ በመቀበል፣ ይህንንም ሚና ለሴት ልጆቻቸው ለማስተላለፍ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚነገሩት ቃላዊ ተረኮችን የሚጠቀሙ

ሲሆን ተረኮቹ ማህበረሰቡ ልክ ነው ብሎ ባስቀመጠው የስርዓተ ፆታ ህግና ስርዓት ውስጥ ለሁለቱ ፆታዎች የተሰመሩ ድንበሮች እንዳይጣሱ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ከሚናቸው የሚያፈነግጡ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን በተለያዩ ማህበራዊ ስምምነቶች የመቅጣት ልማድ እንዳለ ማየት ይቻላል። ለምሳሌ ሴቶችን ለጋብቻ አለመጠየቅ፣ ወይም ደግሞ የባለሙያነትን መስፈርት ካላሟሉ የመሰደብ፣ የመናቅና የመሳሰሉት ቅጣቶች ሊደርሱባቸው ይችላል።

በቃል የሚነገሩ ተረኮች ውስጥ ሴቶች ራሳቸውን አወዳድረው ከወንዶች መብለጣቸውን የሚገልፁባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉም በትንታኔው ውስጥ ማየት ተችሏል።

በማህበረሰቡ ውስጥ የሴቶች ፆታዊ ሚና በሁለት መንገዶች ሊታይ ይችላል። የመጀመሪያው በማህበረሰቡ ውስጥ ራሱን የቻለ ሚና ያላቸው ሲሆን ሚናቸው ሌሎቹን የመደገፍና የተጣመመ የማቃናት ብቻ አይደለም። ራሱን ችሎ በራሱ የሚቆም ነው። ለዚህም ሴቶችንና የሚጫወቱትን ሚና ማንሳት ወይም እንዳይኖሩ ማድረግ ቢቻል ማህበራዊ ስርዓቱ የሚናጋና በጭራሽ መስራት የማይችል እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የወንዶች ተፅዕኖ ፈጣሪነት ባይካድም ይህንን ተፅዕኖ በውድም ይሁን በግድ ተቀብለውትና ወደውት የሚኖሩ ይመስላል። ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ለዚህ ሚናቸው ዕውቅና የመስጠቱ ጉዳይ ገና ተገቢው ቦታ የደረሰ አለመሆኑ ነው። ዕውቅና አልተሰጠውም ማለት ግን ሚናቸው ህልውና የለውም ማለት አይደለም።

በተጨባጭ በሚታየው በታሪካዊና ባህላዊ የማህበረሰቡ ዳራ ሴቶች ከፍ ያለ ሚና ይጫወታሉ። ይህንን ሚና የላቀ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚያስችልና ያንን ዕውቅና እንዲኖረው የሚያደርግ አቅም ግን አልተፈጠረላቸውም ማለት ይቻላል። ሴቶች ሲጋፈጡት የኖሩት ቶሎ ቤተሰብ የመመስረት ልማድ እየደበዘዘ፣ መጨረሻው ምንም ይሁን ምን ቤተሰብ ሴቶችን ወደ ትምህርት ቤት የመላክ አዝማሚያ እያደገ በመምጣቱ ምክንያት ሴቶች አለምን የሚያዩበት መንገድ ቀስ በቀስ እየተቀየረ የመጣ ይመስላል።

ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁነቶች ከዘመናዊነትና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዘው የሚታዩ የመረጃ ፍሰቶች በፈጠነ መንገድም ባይሆን ቀስ በቀስ አዳዲስ አስተሳሰቦች እየገቡ ይመስላል። በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ባህል ተለዋዋጭ በመሆኑ ከማህበረሰብ ዕድገት

ጋር ተያይዘው በሚመጡ በእነዚህ አዳዲስ አስተሰቦች እሴቱን የማያስቱና የማያጠፉ ነገር ግን ሲጋፈጧቸው የኖሩትን ተግዳሮቶች የሚያቀሉ አድርጎ መጠቀም አስፈላጊ ነው። ሴቶችን ከአስራ ስምንት አመት በፊት ያለመዳር ህግ፣ ሴቶችን የንብረት ወራሽነትና ባለቤት መሆን የሚያስችል መብት፣ የሞባይልና መሰል ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚነት፣ በገበያ፣ በክብረበዓላትና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ከከተማ ሰዎች ጋር የሚኖር የመረጃ ልውውጥ ለውጡን እየፈጠሩ ካሉ እውነታዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የተነሱት ሴቶች ጉዳዮች በተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች መመርመር ቢችሉ ለየዕውቀት ዘርፎቻቸው ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ የሚል እምነት አለኝ። የአካባቢውን ባህል መግለፅ የሚያስችል ሀገር በቀል ዕውቀት የያዙ ሴቶችን ዕውቀት መሰብሰብና ዕውቀቶቹ ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ማያት የሚያስችል፣ በታሪክ አጋጣሚ የሚነሱ ሴቶችን ጉዳይ ከእውነታና ከታሪክ አኳያ መቃኘት የሚያስችል፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ከኢኮኖሚ አኳያ ስላላቸው አስተዋፅኦ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን መሰረት የሚያደርግ፣ በስነሰብዕ፣ በታሪክና በመሳሰሉት የትምህርት ዘርፎች ጥናት ቢካሄድ ስለማህበረሰቡ፣ በተለይም ስለሴቶቹ የበለጠ ማወቅ ያስችላል የሚል እምነት አለኝ።

ዋቢ ጽሑፎች

የአማርኛ ዋቢ ጽሑፎች

መስፍን መሰለ፤ ስለሴቶች በተቃርኖ የሚነገሩ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች››፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ 1992፣ (ገፅ 1-17)።

ሽመልሽ ግዛው፤ ‹‹የሲዳማ ሴቶች ማህራዊ ቦታና ስነቃል ችሎታ ከእሹሩሩ ግጥሞች አኳያ››። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥና ተቋም፣ 1992፣ (ገፅ 82-103)።

ተስፋ ገብረየስ፤ *አይመለል፡ ጉራጌ(ሶዶ ጎርደና) ሕዝብ አጭር የታሪክ ማስታወሻ*፤ ወርቁ ተስፋ፣ (አዘጋጅ)፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1987።

ታዬ (አለቃ)፤ *የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ*፤7ኛ ዕትም፣ አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ 1964።

ቴዎድሮስ ገብሬ፤ *በይነዲስፕሊናዊ የስነፅሑፍ ንባብ*፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001።

የሶዶ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት፤ የሶዶ ወረዳ ስነህዝ ቡክሌት፣ 2004።

የእንግሊዝኛ ዋቢ ጽሑፎች

Abrams, M.H. A Glossary of Literary Terms. 7th ed. USA: Earl McPeek, 1999.

Abreham Alemu. “Oral narrative as ideological weapon for subordinating women: the case of Jimma”. Journal of African Cultural Studies. 2007, Volume 19, No. 1, pp. 55–79.

Alexander-Floyd, Nikol G. and Evelyn M. Simien. “Revisiting "What's in a Name?": Exploring the Contours of Africana Womanist Thought”. Frontiers: A Journal of Women Studies, Vol. 27, No. 1, pp. 67-89, 2006.

Avakian, Arlene Voski and Barbara Herb. *From Crocker to feminist Food Studies.* (ed), University of Massachusetts Press, 2005.

Bahiru Zewde, "The Aymelele Gurage in the nineteen Century: A political History". Trans African Journal of History, Nairobi, vol.2 no. 2, 55-68, 1972.

Birhanu Bekele. "The portrayal of Women in Folktales and Popular Saying of the Oromo of East Wellega". Department of Foreign Languages and Literature, Addis Ababa University. Partial Fulfillment of M.A Degree. 2008.

Blum-Kulka, Shoshana. " 'You Gotta Know How to Tell a Story': Telling, Tales, and Tellers in American and Israeli Narrative Events at Dinner ". Language in Society, Vol. 22, No. 3, pp. 361-402, 1993.

Butler, Judith. *Gender Trouble: Feminism and the Subversion of Identity*. Routledge, New York and London. 1990.

Counihan, Carole M. "Female Identity food and power in contemporary Florence". The George Washington University Institute for Ethnographic Research, Anthropological Quarterly, Vol. 61, No. 2, pp. 51-62,1988.

---------- and Steven L. Kaplan(Ed.). *Food and Gender: Identity and Power.* Taylor & Francis e-Library, Ajanta Offset, 2005.

Ephrem Belete. "The Syllable of Kistane: A Moraic Approach". Addis Ababa University, School of Social Scince and Humanity, Department of Lingustics, 2011.

Fellman, Jack. "Gurage: The Last Straw". The Journal of Modern African Studies, Vol. 31, No. 4, pp 673-674, 1993.

Gumerman, George. "Food and Complex Societies". Journal of Archaeological Method and Theory, VoL 4, No. 2, 1997.

Herman, Luc and Bart Veraeveck (Trans). *Handbook of Narrative Analysis.* University of Nebraska, Thomson-Shore, Inc.,2005.

Holmes, Mary. *Gender and Everyday Life: the New Sociology*. Routledge Tylor and

Francis Group, Great Britain, 2009.

Hooks, Bell. 1999. "Ain't She Still a Woman?" Shambhala Sun, 1999. [Online Edition]

Hudson-Weems, Clenora. "Africana Womanism: The Flip Side of a Coin". The Western Journal of Black Studies Vol. 25, No. 3, pp 137-144, 2001.

J. Stephens, Ronald, Maureen Keaveny and Venetria K. Patton. " 'Come Colour My Rainbow': Themes of Africana Womanism in the Poetic Vision of Audrey Kathryn Bullett", Journal of Black Studies, Vol. 32, No. 4, pp. 464-479, 2002

Nenola, Aili. "Folklore and the Genderized World". Turku, Nordic Frontiers, pp 49-62 1993.

Phillips, Layli.(Ed.) *The Womanist Reader*. New York London, Taylor & Fancis Group, 2006.

Revised Family Code. Federal Negarit Gazzeta of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Extra Ordinary Issue. no. 1/2000, Addis Ababa, 2000.

Sena Gonfa. "The Image of Women in the Proverbs and Sayings of the Oromo: the Case of West Arsi Zone". Department of Foreign Languages and Literature, Addis Ababa University, Partial Fulfillment of M.A. Degree, 2008.

Shack, A. William. "Hunger, Anxiety, and Ritual: Deprivation and Spirit Possession Among the Gurage of Ethiopia". Man, New Series, Vol. 6, No. 1, pp. 30-43, 1971.

Shimelis Bonsa. "A history of Kistane migration to 1974" Azania: Archaeological Research in Africa, 36-37:1, 172-186, 2001.

Simien, Evelyn. "Race, Gender, and Linked Fate." The Western Journal of Black Studies Vol. 35, No.5, pp 529-550, 2005.

Tigist Berhe. Pronominal Empty Categories of Kistaninna: A Minimalist

Approach." A.A.U, Institute of Language Studies, Department of Lingustics, 2008

Udry, J. Richard, "Demography", Population Association of America Vol.31, No.4, pp 561-573, 1994.

Westfield, N.L *Dear sisters: A womanist practice of hospitality*. United States of America: the Pilgrim Press, 1993.

Williams, S.A. *Some Implications of Womanist theory*. New York: Meridian press, 1990.

www.folklore.ee/folklore/vol29/gender

www.csa.gov.et

www.guragezone.gov.et

አባሪዎች

ከሶዶ ወረዳ የተሰበሰቡ ዝርውና ቃላዊ ተረኮች

1. ሰነፍ ምሽት በጌ ባለ
   ጥሪ እንጨ በበር ባለ
   ብሽ ኤምን ያልፉት ብሽ በጌ ባለ

2. ፈያ ምሽት በጌ ባለ
   ደረቅ እንጨ በቆጥ ባለ
   ፈያ አምብል በጓሯ ባለ
   ሸባል ኤምን ያልፉት ሸባል በጌ ባለ

3. ‹‹ሴትዮዋ በእንሰት ቅጠል አይብ አስራ ቤቷ ምሰሶ ላይ ሰቅላዋለች። በአጋጣሚ የመጡ እንግዶች ቤቷ ጠላ እየጠጡ እያለ ላያቸው ላይ የአይቡ ውሃ ተንጠባጠበባቸው። ይሄኔ ‹‹ይሄ የሚንጠባጠበው ምንድነው›› ብለው ይጠይቋታል ‹‹የአይብ ውሃ ነው›› ብላ መለሰችላቸው ‹‹በምን አስረሽው ነው ውሃው እንዲህ የሚንጠባጠበው?›› ብለው ቢጠይቋት ‹‹በእንሰት ቅጠል›› ብላ መለሰችላቸው። እነሱም መልሰው ‹‹የአንቺ አይብ፣ ለዚያውም በእንሰት ቅጠል፣ ለዚያውም ምሰሶ ላይ?›› ብለው እርስ በእርሳቸው እየተያዩ ተሳሳቁባት ይባላል።››

4. ‹‹ ሴትዮዋ በክረምት ዝናብ እየዘነበባት ኩበት ትሰበስባለች። ይህንን በአካባቢዋ የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ሲያልፉ አይተዋት ይገረማሉ። ሴትዮዋም እነዚህ ሁለት ሰዎች እያዩዋት ሲያወሩና ሲስቁ ትመለከታለች። አጠገቧ ሲደርሱም ‹ምን እየተባባላችሁ ነው የምትስቁት?› ብላ ጠየቀቻቸው። እነሱም ‹በዚህ ክረምት ዝናብ እየዘነበብሽ ኩበት ስትሰበስቢ ጊዜ እጅግ ተገርመን እሱን ነው ያወራነው› ይሏታል። ሴትዮዋም በክረምት መስራትዋን እያደነቁ መስሏት ‹የሚገርም እኮ ነው፤ እኔ እንዲህ በዚህ ብርድና ዝናብ እየሰራሁም እኮ ሰነፍ ናት እያሉ ያሙኛል› ስትል መለሰችላቸው።››

5. ቅብኪ የግንቦተ
   ገባም በጉልበተ

6. ቅብኪ ያምሌ ናሴ
   ልብለባው ኤባሴ
   ልብዲ ኤላሴ

7. ቃይሲሽ ያገዱ የሰኔ ጎርጊሰ
   በላትም ፈጆቶት ተባዩሂ ጉንሰ

8. የሰኔዩ አምብል ይነቦት ግበሽ
   ልብ ያለኸ ጎሽ አተድርም እገር
   በረጋ እም በል ባልረጋ ውል ውል በል
   ሰቢ ጥቅጥቅ ይበል ኢንኪ ፍጥጥ ዩበል

9. በአንድ ወቅት አንድ አባወራ ወደቤቱ ያስገባው ስጋ በጣም ትንሽ ነበር። ሚስቱ በዚህ በጣም ትናደድና

ደኽ ግበት ወዳኝ ኧዲ ግበት ወዳጅ
ባሞሌሂ በሰር በገሎድ አንትፋጅ

በማለት በአሽሙር ተቀበለችው።

10. አንዱ አባ ወራ ደግሞ ጉፋያ የሆነ ስጋ ይዞ ይገባል። ሚስቱ ደግሞ ትንሽ ሰባ ያለ ስጋ ትፈልግ ነበርና

ጭሮደህ እጭነ
ቅብዲም ነስጭነ
ንቶናም በጨበር ደናኛ ንኸነ

11. ሰውዬው ወንድ ልጁን መዳር ይፈልግና ባለሙያ የሆነች ጥሩ ሴት እንዲፈልግለት ለአንዱ ሰው ያማክረዋል። ሰውዬውም ለትዳር የደረሰች ልጅ እንዳለቸው ይነግረውና መጥቶ እንዲያያት ይጋብዘዋል። ወንድ ልጁን መዳር የፈለገው ሰው ልጅቱን ለማየት በአሳቻ ሰዓት ቤታቸው ሲሄድ አባቷን ያጣዋል። ቤት ውስጥ አባትዬውን እየጠበቀ ሳለ ልጅቱ ቆሎ እየቆላች ነበርና ከምትቆላበት ምጣድ ላይ እየዘገነች ስትበላ ከዚያ ውሃ በጣሳ እያነሳች ስትጠጣ ያያትና በስራዋ አዘኖ

ተንጣጣ ጪልቂመ ተንጣጣ ጪልቂመ
ደኒ ይጋ ድርግመ

ብለሽ ለአባትሽ ንገሪው የሚል መልዕክት አስቀምጦለት ይሄዳል። አባትየው ከዋለበት ተመልሶ የተቀመጠለትን መልዕክት ሲያገኝ በልጁ ክፉኛ ተበሳጭቶ ‹አሰደብሽኝ› ብሎ ወቀሳት።››

12. አንድ ሃይለኛና ጦረኛ ሰው ነበር። ዘጠኝ ሚስት አግብቶ ዘጠኙም የልቡ የማይደርሱለት፣ እንዳሻው የማይታዘዙለት ነበሩና ሁሉንም ፈትቶ ወደየቤታቸው አሰናብቷቸዋል። ቆይቶ ቆይቶ አንዲት ሳታገባ አባቷ ቤት የቆየች ልጃገረድ ነበረችና እሷን አይቶ ለጋብቻ ይፈልጋታል። አባቷን ለመለመን ቤታቸው ሲሄድ ያጣዋ። ሲጠብቀው ቆይቶ ሲቀርበት ለእሷ ለራሷ ‹‹ያ ነገር ይሆነኛል...መጥቼ አይቻለሁ›› ብለሽ ለአባትሽ ንገሪ ብሎ መልዕክት ይስቀምጣል። እሷም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ልቧ ይጠረጠርና ለአባቷ መልዕክቱን ትነግራለች። ሰውዬውም ለቤተሰቧም ሽማግሌ ይልካል። አባቷም ከእናቷ ጋር በጉዳዩ ላይ ይመካከራል። ነገር ግን ‹‹ዘጠኝ ሚስት አግብቶ ወደቤታቸው ከሰደደዳቸው በኋላ የእኔን ልጅ ይፈልጋል እንዴ ትንሽ ቆይቶ እንደሌሎቹ ቢመልሳትስ?...አልሰጠውም›› ይላል። ይሄኔ ልጅቱ ታዝንና እንቅብ እየሰፋች እንደሚከተለው አንጎራጎረች።

እገሌ የባሉየ
የባሉንሽ ቢዬቡየ
የባለንቃይ
ቢቡሽ ምን ይብሉዬ
ኳሽ ምን ይብሉዬ

አባቷ ይህን ሲሰማ ለልጅቱ ያዝንና ‹‹በቃ ያልከውን እሰጥሃለሁ›› ብሎ ለሰውዬው መልዕክተኛ ላከበትና ተጋቡ። ከተጋቡ በኋላ እንደልቡ መሆን የምትችል መሆኗን ለማረጋገጥ ሊፈትናት ፈለገ። መጀመሪያ ራቁትሽን ምንም ሳትለብሽ ጋያ አቀጣጥለሽ አደባባይ ሽንጎ ላይ ድረሺ አላት። ለአሽከሮቹ ለእሷ ሳትነግሯት አደባባይ ራቁቷን ከመጣች ልብስ አልብሷት አላቸው። እሷም ወደሽንጎው ራቁቷን ለመግባት ስትዘጋጅ አሽከሮቹ ልብስ አለበሷትና ገባች።

በሌላ ጊዜ ‹ማሰሮዬ ስጋ እንዳያጣ፣ እንግዳ ሲመጣብኝ፣ አሽከሮቼ ስጋ እንዳያጡ ነገር ግን ቤቴ ውስጥ አንድም ነገር እንዳይታረድ፤ ምግብ አዘጋጅተሽ ጠብቂኝ› ብሏት ሄደ። አሽከሮቹን ጠርታ በጎቹን አምጡልኝ ብላ የሁሉንም በጎች ላት እየሰነጠቀች አወጣችና ሰራች። ሲመጣ ስጋ አለ፣ በጎቹን ሲያይ አልታረዱም። የተሰጧትን ፈተናዎች ባልዋ በሚፈልገው መንገድ በማለፏ ‹‹በቃ ይህች ሴት ትክክለኛ ሚስቴ ናት›› ብሎ በሰላም አብሯት መኖር ጀመረ።

13. ላገባ ስል ባሌን አላውቀውም ነበር። ሽማግሌም ሲላክ እኔን የጠየቀኝ ማንም አልነበረም። ቤተሰቦቼ ወደው ፈቅደው ከሰጡ በኋላ እኔ ምንም ማድረግ ስለማልችል አገባሁ። ከተጋባን በኋላ ግን ለቤታችን እኩል እንሰራለን። ቤት ወስጥ አንዳንደ ነገሮች ስንወስን በጋራ ነው። እሱም ለብቻው እኔም ለብቻዬ ፍላጎቴን ብቻ ተከትዬ ያለእሱ ፈቃድ የማደርገው ነገር የለም።››

14. ባለቤቴን ካገባሁት በኋላ ወርቅ ሊያመጣ አዶላ የሚባል ቦታ ሲሄድ ብቻዬን ቤት እጠብቅ ነበር። ባለቤቴን ስለማልወደው እዚያ ብዙ ሰዎች ሞቱ ሲባል ምነው አንዱ እሱ በሆነ ብዬ እመኝ ነበር። ከሆነ ጊዜ በኋላ መጣና እንደገና ተመልሶ ሲሄድ ቤቱ ከሌለ የምጠብቀው አይኖርም፤ እኔም ወላጆቼ ጋር እመለሳለሁ ብዬ በማሰብ ቤቱን አቃጠልኩት። ከዚያም በኋላ በጣም ስለጠላሁት አንዲፈታኝ አስለምኜ በግድ ዘመዶቼ አስገድደውት በመጨረሻ ተፋታን፣ ስንፋታ ልብስም አላለበሰኝ ነበር። በኋላ አንድ ባለመሳሪያ ጀግና ነበርና እሱን አገባሁ። ከእሱ ጋር እየኖርኩ ልጆች ከወለድኩና ደክሜ ለፍቼ አንድ ቤት በደጋ አንድ ቤት ደግሞ በቆላ ካሰራሁ በኋላ ሌላ ሚስት ሊያገባብኝ ሆነ። እኔ ሳላውቅ ከጎተራ በቆሎ አውጥቶ፣ ያረባሁትን በግ ነድቶ በመሸጥ ለእሷ ልብስ አሰፍቶ ሄደና በዚያው አደረ። ፈረስ፣ አዲስ ጥይት ገዝቶ መጣ...እኔ ሌባ ገድሎት ነው ብዬ ስሰቃይ አደርኩ። እሱ ጠዋት አዳዲስ ነገር ይዞ መጣ። ከዚያ ከእኔ በፊት ያገባት ሚስቱ ቤተሰብ ጋር ለለቅሶ ሲሄድ እቃዎቹን ያስቀመጠበት ቦታ አዳዲስ ነገር አገኘሁ። ከዚያ ውስጡ ያለውን አዲስ ሽቶ፣ አዳዲስ ጥይት አግኝቼ እየተጠመቀ ያለ የጠላ “አተላ ውስጥ ከተትኩት። ሰው ሁሉ አንቺ ብትከለክዪው መቼም ማማባቱ አይቀርም እያለ ሲመክረኝ ጋኑን ትርክክ አድርጌ ስሰብረው ፀሐዩ ላይ ፍስስ አለ። ከዚያ ቤት ውስጥ ያሉትን እቃዎች እንዳለ ሰባበርኩት። ከእዚያ በቃ ንዴት ሊለቀኝ አለቻለም። አጎቴን እባክህ መሳሪ ስጠኝና ልግደለው እኔ ሌላ ባል ባገባ እንኳ ድካሜና ልፋቴ አይረሳኝም

ብዬ ሳስቸግር ሁሉም ለልጅሽ ብለሽ እያለ ሲመክረኝ ተውኩት።....በኋላም ታርቀን እሱ በሰራሁት በአንዱ ቤት ውስጥ መኖር ጀመረ እኔም በሌላኛው ቤት እንደ ቤት ጠባቂ ሆኜ መኖር ጀመርኩ።

15. ሰውዬው ተጨቃጫቂ ነው። ሁልጊዜ ከሚስቱ ጋር የሚገላግልና የሚያስታርቅ ሽማግሌ መሀከላቸው ሽማግሌ ይገባል። አንድ ቀን አምቾ (እንደድንች ተቀቅሎ የሚበላ የእንስት ስር) ለመቀቀል ወደ ማሰሮ ውስጥ ስታስገባ እሷ ሳታየው እየቆጠረ ነበር። ሰባት አምቾ ቆጠረ። ተቀቅሎ ከማሰሮው ሲዘረገፍ ግን ስድስት አምቾ ነበር የወጣው። ለካ ሚስትዬው መብሰል አለመብሰሉን ለማረጋገጥ አንዱን በልታው ነበር። ያኔ ታዲያ አሁንም ቢናገር ሽማግሌ ይመጣብኛል ብሎ ስለፈራ

ባወረሩም መካ ባላውረሩም መካ
በሰባቲ መካ አቲ ይቲ ፈካ?

ብሏት ወጣ።

16. ባልና ሚስት ሲኖሩ በሳምንት በአንደኛው የገበያ ቀን ወደ ገበያ ስትሄድ የጓዳ ቁሳቁስ የምትሸምተበትን ገንዘብ የሚሰጣት ባልዬው ነው። ታዲያ በአንደኛው ቀን እንደተለመደው ወደ ገበያ ልትሄድ ስትነሳ ገንዘብ ትጠይቀዋለች። እሱም ‹‹ለቡና ነው?›› ብሎ ሲጠይቃት ብላ ትመልስለታለች። ‹‹ለጨው ነው ወይስ በርበሬ?›› ብሎ ይጠይቃታል። አሁንም ‹‹አይደለም›› ብላ ከመለሰችለት በኋላ አያይዛ ‹‹ቃይሳ ልዋጅቦ›› (አይብ ልገዛበት) ስትለው ‹‹በሻችቦ›› (ካወቅሽበት) አላት ይባላል።

17. ‹‹አንዷ ባለትዳር ሴት በአንድ ወቅት ለባሏ ቆንጆ አይብና ቆጮ አዘጋጅታ ለእሷ ደግሞ ለእሱ ተዘጋጅቶ ያደረውን አምጥታ እንደነገሩ የተዘጋጀ ጎመን አጠገቡ አድርጋ ትበላለች። ያደረውን ቆጮ ስትበላ ያያትና

ኧዲም ዳቦ ደሽም ዳቦ
ትዳርኛ አልሻንቦ

ይላታል። በኋላ ለእሱ ቆንጆ ቆጮ በሌላ በኩል ደግሞ መጥፎውንና ብዙ ጊዜ ለመብል የማይሆነውን ጋግራ በአንድ ማዕድ ላይ ግማሽ ግማሹን አድርጋ ስታቀርብ

ደሽም ስትቅን ኧዲም ስትቅን
አዳርኛ ገናም ቅጥን

አላት።

18. ሰውዬው ስጋ በጣም ይወዳል ግን ያ ስራ ተሰርቶ ለሰውዬው ነው እንጂ ሚስትዬው አብራ ቀርባ አትበላም። ሌላ ምግብ አብራው ብትበላም ስጋ ሲሆን ግን አብራው አትበላም። ነገር ግን ሰው ቤት ምንም አስጠንቅቋታል። አንድ ቀን ምሳ ልታዘጋጅ ስትፈልግ ክብሪት ታጣለች። ከዚያ ከጎረቤት ለመዋስ ስትሄድ ባልና ሚስት ቀርበው ምሳ እየበሉ ትደርሳለች። ከዚያ ነይ ብዬ ብለው ይጋሟታል። ባሏ አንዚ ስጋ ከበላሽ እሞታለሁ ብሏታል። ሰለዚህ አረ አኔ አልበላም ትላለች። እሱ ከሚሞት እኔ ስጋ ባልበላ ይሻላል ብላ አምናበት ትታዋለች። ከዚያ አረ እኔ አልበላም ትላለች። ለምን ሲሏት እንዴ ስጋ እኮ ሴት ልጅ ከበላች ባል ይሞታል አሉ። አንቺ እንዴት ቁጭ ብለሽ ስጋ ትበያለሽ ብላ ባለቤትዬዋን ትጠይቃታለች። ማን ነው እንደሱ ያለሽ ብለው ሲጠይቋት

ባለቤቴ ትላለች። እስቲ እሱ ዛሬ ይሙት እንኪ ብዬ ብዬ ብለው ይሰጧታል። እሷም በልታ ጠጥታ ወደ ቤቷ ተመለሰች። አሁን ስትገቢ አብረሽ ከሱ ጋር ማንኪያሽን ይዘሽ ብዬ ብለው ይመክሯታል። እሷም ምግቧን አዘጋጅታ ልትበላ ስትል ምን ልትሆኚ ነው ብሎ ይጠይቃታል። እሷም ምሳ ልበላ ነው ትለዋለች። እሱም ሌላ ቀን በልተሽ የማታውቂውን እንዴት ዛሬ ከእኔ ጋ ቀርበሽ ትበያለሽ ይላታል። እሷም አይ ዛሬማ እበላለሁ፡ ትለዋለች። አረ እኔ እሞትብሻለሁ፡ ይላታል ሙት ከፈለክ ትለዋለች። እየበሉ እያለ እንደሞተ ሰው የወድቃል። እሷም ተነስተህ ትበላ እንደሆን ብላ በኋላ ጮኬ ሰው እሰበስባለሁ ስትለው ትተይዋለሽ ይላታል አልተውም ትላለች። ከዛ በቃ አንደሞተ ሲሆን እሷ ጮኸችና ጎረቤት ተሰበሰበ። ከዚያ ቢሉት ቢሰሩት እንደሞተ ሰው ሆነ። ሳጥን ገዝተው አመጡና ሳጥን ውስጥ ከተቱት። ቀስ ብሎ ትሌጊን (ትተይዋለሽ)ሲላት ተለጋ (አልተውም) ትለዋለች። ከዚያ በዚህ ሁኔታ እሱም ሳይነሳ እሷም ሳትተው ሰውዬው ከእነነብሱ ተቀበረ ይባላል።

19. ሰውዬው ከሚስቱ ጋር ምግብ ለመብላት እንደተዘጋጁ ውሃ እንድታመጣለት ይጠይቃታል። ርቧት ስለነበር ልትነሳ ስትል ከቆጮው አንድ ግዜ ገምጣለት ውሃ ለማምጣት ትነሳለች። ይሄኔ ባልየው የገመጠችለትን ቆጮ በጣቱ ሲለካው ትልቅ ይሆናል። ከዚያም ‹‹ እንዲህ ከምትበላ ሴት ጋር ነው አብሬ የምኖረው ማለት ነው›› ብሎ ይበሳጭና ለቤተሰቦቿ ሊመልሳት ይወስናል። ከዚያም በይ ተነሽ ቤተሰቦችሽ ጋ እንሂድ ይላታል። በዚህ ጊዜ ሆዷ ይተረጥርና ይከፈታል። ከዚያ መንገድ ላይ እያሉ አንዲት ላም ሳር ስትገጥ ያገኛሉ። በዚህ ጊዜ ሚስትዬው ‹‹ውይ ይህቺ ላም እንዴት ነው የምትበላው እስኪ እንያት ትለዋች›› ለምን ሲላት ልክ እንደራበው ሰው ነውየምትበላው ሰውም መጀመሪያ ሲበላ እንዲህ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ይበርድለታል። አለችው። በዚህ ጊዜ እሱም ለካ ቅድም ርቦሽ ነው እንዲህ የበላሽው እኔ እኮ ሁልጊዜ እንዲህ የምትበይ መስሎን ቤተሰቦችሽ ጋ ልመልስሽ ነበር። በይ አሁን ወደቤታችን እንመለስ። አላትና ወደቤታቸው ተመለሱ።

20. ዘነበች የምትባል አንዲት ሴት ሀገራችን በተወረረች ጊዜ ከወንዶች ጋር አልሸፍትም ብላ ሌሎች 15 ሴቶች ይዛ ሸፍታ ነበር። ለደኛች በቀለ ወያም ጠላት የት እንደደረሰ እየተከታተሉ ይልኩ ነበር። ሃይለስላሴ ወደ ሀገር ሲመለሱ እነዚህን 15 ሴቶች ይዛ በመሄድ ተሸልማለች። ስለሴቶች ብዙም ስለማይወራ ብዙ አልተነገረላትም።

21. አንዲት ቤቴ የምትባል ሴት ነበረች። ከወንዶች ጋር አብራ እየሄደች ትዘፍናለች፣ ዘራፍ ትላለች። የጎሳ ጥል ሲፈጠር ወይ ሁለት የማይዋደዱ አካላት ሲኖሩ እየተከታተለች አንደኛውን ለጥል ታነሳሳለች። በአንድ ወቅት ኦሮሞና ክስታኔ ተጣልተው ነበር አሉ። ነው። ገላን ኢመቶ የተባለው ጦረኛ ሰው ከዱላ ጎሳ (የኦሮሞ ጎሳ ነው) ሚዜ ነበርና መልስ ተጠርቶ ሲበላ ዋጮች (የክስታኔ ጎሳ ነው) መጣ። ቤቴ እዚያ መልሱ ቦታ ነበረችና የገላን ኢመቶ መምጣት አናዷታል። እንደመደፈርም ስለቆጠረችው የዋጮን ጎበዛዝት ለማነሳሳት

ዋጮ ምን መላነ
ኢመቶ ገላነ
ዝምን ጓሮአነ
ገባም ዳቢያነ

ብላ ስትዘፍን ገላን ኢመቶ ፈረሱን ጫነና የተጠራበትን መልስ ሳይበላ ጥሎ ወደ መጣበት ተመለሰ።››

22. በአንድ ወቅት በታሪክ የኦሮሞና የጉራጌ ጎሳ ግጭት ላይ በነበሩበት ወቅት አንደኛው ሁለት ሰዎች አይዋደዱም። አንደኛው ጉራጌ አገር መልስ ሊበላ መጣ። ሲመጣ ማንም አላወቀውም ቦታው ዘጌ ገቾ የሚባል የጉራጌዎች አካባቢ ነው። ቤቱ ደግሞ ይህ ሰው ከየት እንደመጣ ታውቅ ነበርና

ገቼ ምን መላነ
ኢመቶ ገላነ ወረደም ዋራነ
ዎባም አዘባነ ገባም ደገማነ

ብላ ስትዘፍን አንደኛው የገቾ ሰው ፈረሱንና ጦሩን ጭኖ ኢመቶ ገላንን ማሳደድ ጀመረ።››

23. ቤቱ በአንድ ወቅት ሁለት የክስታኔ ጎሳዎች የኦሮሞዎን ጎሳ ለመዋጋት ወደ ጢያ ይሄዳሉ፤ በዚህ ወቅት አንድ የኦሪያ ጌታ የተባለ ሰው በጣም ይፈራል። ይሄኔ ፍርሃቱን ለመግለፅ የሚከተለውን ግጥም ገጥማበታለች።

የኦሪያን ጌታ
የተፋን አሞታ
ሰባትን ገበታ

24. የቦቤ ሽብርብር የዙሪያ ቅምጥል
ደኽሽ ባትነብር የጠፋአይ ኤላአ
ባሎጦምም በደብር
ባልገቦም ተግብር

25. የጫሜዲ ቀጭን
በዋጋ ቅብ ይኖ አንጨርርም ስጭን
ኧዚ ጎዲን ይኖ አተርርም ኧጭን
ተሰማን ኢላ የሸሸ የቁጭን

26. ነግጁ ቤቴን አስተዳድራለሁ። ለኑሮ ሁለታችንም እየታገልን እንኖራለን። በእግር ከኑረና ተነስተን አጨበር ሮብ ገበያ ለመድረስ አራት ሰዓት ይፈጅብናል። ለመምጣትም አራት ሰዓት ይፈጃል። እዚህ አካባቢ ሴቶች ፈረስ አንጠቀምም፣ ወንዶቹ ናቸው በፈረስ የሚሄዱት፣ ወደላይ ወደ አጨበር ያሉት ሴቶች ግን ፈረስ ይጠቀማሉ። አዚህ ስላልተለመደ በእግራችን ነው የምንሄደው።

የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር

የመረጃ ሰጪ ስም	ዕድሜ	ቦታ
እማሆይ ቦጋለች ዱሬሳ	-	ቡዲ
ወ/ሮ ኩሉሃገር ደያሶ	35	ኑረና
ወ/ሮ ሃይማኖት አልዬ	42	ኑረና
ወ/ሮ ሰናይት ተሰማ	30	ቡዲ
እማሆይ ገኔ መግራ -	-	ቡዲ
ወ/ሮ ይፍቱ ቲክሴ	-	ቡዲ
አዝማች ከተማ	-	ቡዲ
አቶ አበጋዝ ጉግሳ	-	ቡዲ
አዝማች ግዛው ወ/ሰንበት ፡	66	አናቲ
አዝማች ጫካ አሰፋ	66	ፍርሸና አሮና
አለቃ አበራ ዶሞ	-	ትውልድና ዕድገት አይመለል፤ ኑሮ ቡዲ
ወ/ሮ አለምነሽ በያን	-	ቡዲ
ወ/ሮ ጂቱ መጫ	40	ኑረና
ወ/ሮ ዘነበች አሻሚ	-	አይመለል
ወ/ሮ አበራሽ ደበላ	35	ኑረና
ወ/ሮ ዘርጊ ማሞ	50	ኑረና
ወ/ሮ መለሱ ተካ	30	ኑረና
አረጋሽ ገብሬ	በግምት 60	ኑረና